# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 136 ጥር 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









## “የባህር በር ስምምነቱ በዲፕሎማሲው ዘርፍ የተመዘገበ ትልቅ ውጤት ነው”

- አቶ ጥላሁን ከበደ
 የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

ገጽ 4






## «አውደ ርዕዩ አዳዲስ የኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲዎችን ለመተግበር የሚረዱ ሃሳቦችን ለማመንጨት ያግዛል»

- ዮሐንስ አያሌው(ዶ/ር)
 የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት

ገጽ 4



## «ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉምን ኢትዮጵያዊያን የሃሳብና የአመለካከት ውክልናን አካቶ ይካሄዳል»

- ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)
 የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉምን ኢትዮጵያዊያን የሃሳብና የአመለካከት ውክልናን አካቶ ይካሄዳል ሲሉ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ዮናስ አዳዬ (ዶ/ር)

«ሀገራዊ ምክክሩ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## የዓባይ ግድብ - ተጨማሪ ሲሳይ

**ተስፋ ፈሩ**

**ዜና ትንታኔ**

የዓባይ ግድብ የሚያርፍበት ቦታ የውሃውን ይዞታ ጨምሮ አንድ ሺህ 740 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ይሸፍናል። ግድቡ የሚይዘው 74 ቢሊዮን ሜትር ኩብ ውሃ ወደ ኋላ 246 ኪሎ ሜትር ይረዝማል። በዚህም እያንዳንዳቸው ከአምስት ሔክታር በላይ ስፋት ያላቸው 70 ደሴቶች የሚፈጠሩ ሲሆን፤ ትልቁ ደሴት ሁለት ሺህ 800 ሔክታር ስፋት እንደሚኖረው መረጃዎች ያመለክታሉ።

በርካታ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦችን አቅፋ ብትይዝም ከቱሪዝም ዘርፍ እምብዛም ተጠቃሚ ላልሆነችው ኢትዮጵያ፣ በአፍሪካ ግዙፍ የኃይል ማመንጫ የሆነው የዓባይ ግድብ ይዞት የሚመጣው ሲሳይ ምን ይሆናል?

በአዲስ አባባ ዩኒቨርሲቲ የውሃ መሐንዲሱ ፕሮፌሰር አድማሱ ገበየሁ የዓባይ ግድብ ለኢትዮጵያና ጎረቤት ሀገራት የኃይል ምንጭ ከመሆኑ ባለፈ ለምሥራቅ አፍሪካም ሆነ ራቅ ላሉ ሀገራት ዜጎች አጓጊ የቱሪስት መዳረሻ በመሆኑ ከዚህ በኋላ ከፍተኛ የቱሪስት ማዕከል እንደሚሆን ይናገራሉ።

በአሜሪካና ካናዳ በአካል ተገኝተው የተመለከቷቸው የቱሪስቶች መናኸሪያ የሆኑ መሰል ግድቦች እንዳሉ የገለጹት ፕሮፌሰሩ፤ “ለኢትዮጵያ ትልቅ ገጽታ የሚፈጥርና

የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











# ዘንድሮ የሚተከሉ አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን የቡና ችግኞች ፈልተዋል

## - 117ሺ ሄክታር በላይ የቡና ማሳ በመጎንደል ሂደት ላይ ነው

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- እስካሁን አንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን የቡና ችግኞች መፍላቱንና ከ 117 ሺ ሄክታር በላይ የቡና ማሳ በመጎንደል ላይ እንደሚገኝ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የቡና፣ ሻይና ቅመማ ቅመም ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ፍቃዱ ደፈረስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለስልጣኑ የቡና ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡ እስካሁን አንድ ነጥብ ሰባት ቢሊዮን የቡና ችግኝ ፈልቷል፡፡

የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ለቡና ተክል ትኩረት ሰጥቷል ያሉት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ዘመቻው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በየዓመቱ ከአንድ ነጥብ 25 እስከ አንድ ነጥብ 39 ቢሊዮን የቡና ችግኞች መተከላቸውን ገልጸዋል፡፡

አቶ ፍቃዱ በተያዘው ዓመትም አንድ ነጥብ 59 ቢሊዮን የቡና ችግኞችን ለማፍላት ታቅዶ እስከሁን ወደ አንድ ነጥብ 75 ቢሊዮን ችግኝ ማፍላት መቻሉን ጠቅሰዋል ፡፡

የቡና ምርታማነትን ለማሳደግ ምንም የቡና ዛፍ በሌለባቸው ቦታዎች ላይ በርካታ አዳዲስ የቡና ተክሎችን መዘጋጀታቸውን የገለጹት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ ለፈሉት የቡና ችግኞች የሚሆን የጉድጓድ ቁፈራ ሥራም ተጀምሯል ብለዋል፡፡

ሌላኛው የቡና ዛፍ እያረጀ ሲመጣ ምርታማነቱ የሚቀንስ በመሆኑ ዛፉን በመጎንደልና ነቅሎ በአዲስ በመተካት የቡና ምርትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በዘንድሮ ዓመትም በ117 ሺህ 460 ሄክታር ማሳ ላይ የሚገኝ ያረጀ የቡና ዛፍ ለመጎንደልና ነቅሎ በአዲስ ለመተካት ታቅዶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

መሪ ሥራ አስፈጻሚው አርሶ አደሮች ያረጁ ቡናዎችን በመጎንደል አልያም ነቅሎ በአዲስ በመተካት ምርታማነትን ማሳደግ እንዳለባቸው ጠቅሰው፣ እያንዳንዱ የቡና ጉንደላ በሚከናወንበት ወቅት የባለሙያዎች ክትትልና ድጋፍ እንደሚደረግም ገልጸዋል ፡፡

የአየር ንብረትን ለውጥን ለመከላከል አርሶ አደሩ ያረጁ የቡና ዛፎች ሲጎነደሉ ሌሎች የጥላ ዛፍ እንደሚተከሉም ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ582 ሺህ 448 ሄክታር በላይ ማሳ ላይ የሚገኝ ያረጀ የቡና ዛፍ የመጎንደልና ነቅሎ በአዲስ የመተካት ሥራ መሥራቱን አቶ ፍቃዱ ገልጸዋል፡፡

# በክልሉ የመማሪያ መጽሐፍትን ለእያንዳንዱ ተማሪ ለማዳረስ ሁለት ዓመት ይፈጃል

## - እስካሁን 20 ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች ተሰራጭቷል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል የመማሪያ መጽሐፍትን ለእያንዳንዱ ተማሪ ለማዳረስ ሁለት ዓመት ሊፈጅ እንደሚችል የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ፡፡ እስካሁን 20 ሚሊዮን የመማሪያ መጽሐፍት ለተማሪዎች መሰራጨቱ ተጠቁሟል፡፡



ቶላ በሪሶ (ዶ/ር)

የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ኃላፊ ቶላ በሪሶ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤የመማሪያ መጽሐፍትን ለሁሉም ተማሪዎች ማዳረስ አለመቻሉ በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ በክልሉ የመማሪያ መጽሐፍትን ለእያንዳንዱ ተማሪ ለማዳረስ ሁለት ዓመት ሊፈጅ ይችላል፡፡

በኦሮሚያ ክልል በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አምስት ሚሊዮን፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አንድ ሚሊዮን 54 ሺህ ፤በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ደግሞ አንድ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ተማሪዎች ይገኛሉ ያሉት ኃላፊው፤በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሚገኙ ተማሪዎች መጽሐፍትን የሚያቀርበው የክልሉ ትምህርት ቢሮ ሲሆን ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደግሞ መጽሐፍትን የማቅረብ ኃላፊነቱ የትምህርት ሚኒስቴር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በዚህም ትምህርት ሚኒስቴር በክልሉ ከዘጠነኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ላሉ ተማሪዎች 14 ሚሊዮን መጽሐፍትን ማቅረብ የሚኖርበት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ለክልሉ ማድረስ የቻለው 5 ሚሊዮን (35 ነጥብ 7 በመቶ) መጽሐፍትን ብቻ መሆኑን ኃላፊው ተናግረዋል፡፡

ትምህርት ሚኒስቴር የተቀረውን መጽሐፍትን ደረጃ በደረጃ እያተመ ለማቅረብ ቃል መግባቱን የገለጹት ኃላፊው፤ ሚኒስቴሩ ያቀረበውን መጽሐፍት የክልሉ ትምህርት ቢሮ ለተማሪዎቹ ማሰራጨቱን ተናግረዋል፡፡

ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ መጽሐፍት ማዳረስ ቢቻልም ሌሎቹ ክፍሎች ላይ ግን ከፍተኛ ችግር አለ ብለዋል፡፡

የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መጽሐፍትን አትሞ የሚያሰራጨው የክልሉ ትምህርት ቢሮ መሆኑን ገልጸው፤ ለእነዚህ ትምህርት ቤቶች 36 ሚሊዮን መጽሐፍት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ቢሮው እስካሁን ድረስ አትሞ ማሰራጨት የቻለው 15 ሚሊዮን መጽሐፍትን መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

በክልሉ መጽሐፍትን ለእያንዳንዱ ተማሪ ለማድረስ ከዚህ በኋላ ሁለት ዓመት እንደሚፈጅ በክልሉ የትምህርት ትራንስፎርሜሽን መተንበዩን የገለጹት ኃላፊው፤ በዚህ ዓመት ግን አንድ መጽሐፍ ለሁለት ተማሪ ለማድረስ እቅድ መያዙን አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜም ኢንተርኔት ማግኘት የሚችሉ ተማሪዎች መጽሐፉን ከቢሮው ድረ ገጽ አውርደው እንደሚጠቀሙና ይህንን ማግኘት የማይችሉ ተማሪዎች ደግሞ በመምህራኖቻቸው በኩል የሚያገኙበት እንዲሁም አቅም ያላቸው ትምህርት ቤቶች የተወሰኑ መጽሐፍቶችን እያተሙ ለተማሪዎቻቸው የሚያደርሱበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

ኃላፊው «መጽሐፍ በተማሪዎች እጅ ላይ አለመገኘቱ በትምህርታቸው ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ከባድ መሆኑን ብንረዳም ማተሚያ ግብአቶች ከውጭ ለማስገባት የውጭ ምንዛሬ እጥረት በመኖሩ ከአቅም በላይ ሆኖብናል» ሲሉ የችግሩን መንስኤ አብራርተዋል፡፡



# አውደ ርዕዩ የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት ያግዛል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ካቶሊክ ገዳማት ጥምረት ፕሮጀክት የተዘጋጀው አውደ ርዕይ በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግር ለመፍታት የሚያግዝ መሆኑ ተገለጸ፡፡

በአዲስ አበባ ካቶሊካዊ ገዳማት ጥምረት ፕሮጀክት “ክህሎትን እና እድሎችን ማገናኘት “በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዘርፎች የሰለጠኑ ወጣቶችን ከአሰሪዎች ጋር የሚያገናኝ አውደ ርዕይ በትናንትናው እለት ተከፍቷል፡፡

የፕሮጀክቱ ዋና አስተባባሪ አቶ ሰለሞን ደጀኔ በአውደ ርዕዩ መክፈቻ ላይ እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ካቶሊካዊ ገዳማት ጥምረት ፕሮጀክት የተዘጋጀው አውደ ርእይ ሥራ አጥ ወጣቶችን ከአሰሪዎች ጋር በማገናኘት በሀገሪቱ የሚስተዋለውን የሥራ አጥነት ለመፍታት ያግዛል፡፡

አውደ ርዕዩ በአዲስ አበባ የሚገኙ የቴክኒክና ሙና ትምህርት ስልጠና ተመራቂዎችን የሥራ ፍለጋ ክህሎት ለማሳደግ ያለመ መሆኑን ገልጸው፤አውደ ርዕዩ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት የሰለጠኑ ወጣቶች ከአሰሪዎች ጋር ለማገናኘት የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

ወጣቶችን ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በማገናኘት ከቀጣሪዎቹ ጋር የሚተዋወቁበት ፣መረጃ የሚለዋወጡበት እንዲሁም የሥራ ዕድል የሚያገኙበት መድረክ መሆኑን አስገዝበዋል፡፡

አቶ ሰለሞን በአውደ ርዕዩ 50 ተቋማትን በማሳተፍ እስከ 3ሺህ ማህበረሰብ ክፍል ይጎበኛል ተብሎ እንደታቀደ አስታውቀው ፤ ወጣቶችን የሥራ እድል ተጠቃሚ ከማድረግና ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባለፈ ሌሎች ተዛማጅ ጠቀሜታዎች እንደሚኖሩት ገልጸዋል፡፡

የአዲስ አበባ የካቶሊክ ገዳማት ጥምረት ፕሮጀክት የወጣቶችን ህይወት በመለወጥ ሂደት ውስጥ የሥራ አጥነት ችግርን ለመፍታት በትኩረት እየሰራ ነው ያሉት አቶ ሰለሞን ፤በዚህም ይህ አውደ ርዕይ በፕሮጀክቱ ከሚተገበሩ ስራዎች አንዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ከስድስት የካቶሊክ ጉባኤዎች በጋራ በመሆን የሚከናወን ሲሆን በተለይም ተፈናቃዮች፣ ከስደት ተመላሾች፣ ስደተኞችን እና ተጋላጭ ግለሰቦችን ህይወት ለመቀየር የሚሰራ ነው ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከሶስት ዓመታት በፊት የተጀመረ ሲሆን፤ አንድ ነጥብ 9 ሚሊዮን ዶላር እየተተገበረ መሆኑን አመልክተው፤ በጤና እንክብካቤ፣ በመጠለያ አቅርቦት ፣በሙያ ስልጠና እና በቅጥር ተነሳሽነት የግለሰቦች ሁለንተናዊ ደህንነት ላይ በማተኮር ለህብረተሰቡ እድገት የሚሰራ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ከ አንድ ሺህ 800 በላይ ተጠቃሚዎችን ማሰልጠን የተቻለ ሲሆን፤ ፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች መካከል 70 በመቶ የሥራ እድል ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አስታውቀዋል፡፡



አቶ ሰለሞን ደጀኔ

የወጣቶችን የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ እና ቀጣይነት ያለው ኑሮ ለመፍጠር በቀጣይም በስፋት እንደሚሰራ ገልጸው፤ በሶስት ዓመት ውስጥ 10 ሺህ ለሚሆኑ ማህበረሰቦች የሥራ እድል ለማመቻቸት ታቅዶ እንደሚሰራም ተናግረዋል፡፡

ከመርሀ ግብሩ ላይ ከሥራ እድሎች በተጨማሪ ኤግዚቢሽንና የፓናል ውይይቶች የሚቀርብ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን፤ ይህም በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተመራቂዎችን ከአሰሪዎች ጋር ስልታዊ አጋርነታቸውን ለማፍራትና ዘላቂ አስተዋጾ ለማድረግ እድል እንደሚኖረው ገልጸዋል፡፡


አቶ ሰብሃዲን ሱልጣን

# በመዲናዋ ከ96 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ በበጀት ዓመቱ ስድስት ወራት ከ96 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠሩን የአዲስ አበባ ሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የሥራ ስምሪት ማስፋፊያ ዳይሬክተር አቶ ሰብሃዲን ሱልጣን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በ2016 በጀት ዓመት ለ300 ሺህ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለፉት ስድስት ወራት ከ96 ሺህ በላይ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል መፍጠር ተችሏል።

በስድስት ወራትም 150 ሺህ የሥራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ 96 ሺህ 504 ዜጎች የሥራ እድል የተፈጠረ መሆኑን ገልጸው። ይህም የግማሽ ዓመት እቅዱን 64 በመቶ ማሳካት መቻሉን አስታውቀዋል።

የሥራ እድል ከተፈጠረላቸው ውስጥ 74 በመቶ ወይም 74 ሺህ 146 ወጣቶች ሲሆኑ፣ 48 ሺህ 700 ሴቶች፣ 9 ሺህ 648 ምሩቃን መሆናቸውን አስታውቀው፤ ከተፈጠረው የሥራ እድል 49 በመቶ በአገልግሎት፣ 21 በመቶ በማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም 15 በመቶ በንግድ ዘርፍ የተፈጠረ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ሰብሃዲን እንደገለጹት፤ 180 ሺህ የሥራ ፈላጊ ለመመዝገብ ታቅዶ 161 ሺህ 068 መመዝገብ ተችሏል። ከተመዘገቡትም 103 ሺህ በላይ የሚሆኑት ወጣት ሲሆኑ፤ 87 ሺህ በላይ ሴቶች ናቸው።

በግማሽ ዓመት ውስጥ ሁለት ሺህ አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች እና 10ሺህ አንቀሳቃሾችን ለማደራጀት ታቅዶ፤ ሁለት ሺህ 842 አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች እና 12ሺህ 053 አንቀሳቃሾች ለማደራጀት ተችሏል። ይህም ከእቅድ በላይ የተሳካ መሆኑን አስታውቀዋል።

በስድስት ወራት ውስጥ ለዜጎች የሥራ እድል የሚፈጠርባቸው አማራጭ የሥራ እድል ጸጋዎችን ከመለየት አንጻር በ9 ሺህ ተቋማት 180 ሺህ ጸጋዎችን ለመለየት ታቅዶ 180 ሺህ 503 ጸጋዎችን መለየት ተችሏል።

ቢሮው በተጨማሪም ለ43 የአገር ውስጥ አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ አዲስ ፍቃድ ለመስጠት ታቅዶ ለ52 የሥራ እና ሰራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ ፍቃድ ተሰጥቷል። እንዲሁም ለ154 ነባር ኤጀንሲዎች እድሳት ለማድረግ ታቅዶ ለ72 ኤጀንሲዎች እድሳት ተደርጓል ብለዋል።

ክትትል እና ቁጥጥር ከማድረግ አንጻር ለ344 ኤጀንሲዎች ክትትል እና ቁጥጥር ማድረግ መቻሉን ገልጸው፤ የ7 ኤጀንሲዎች ብቃት የተሰረዘ መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ሰብሃዲን የወጣቶች የሥራ ማማረጥና የደሞዝ አለመስማማት ምክንያት ወደሥራ ያለመግባት ብሎም በአጭር ጊዜ ሥራ ብዙ ገንዘብ የማግኘት የአመለካከት ክፍተት እየጨመረ መምጣት ተግዳሮት እንደሆነ አስታውቀው፤ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች ጋር በጋራ በመሆን የአመለካከት ስልጠና እንደሚሰጥና ለውጦች እንደሚስተዋሉ ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በጋራ በመሆን የሥራ እድል እንዲያመቻቹና የደሞዝ ማሻሻያ እንዲያደርጉ ይሰራል። እንዲሁም ከ15 ሺህ በላይ ወጣቶችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የብቃት የሥራ ላይ ልምምድ ፕሮግራም በማዘጋጀት ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

# ጅማ በ18 ወራት 15 ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ ኢንቨስተሮችን አስተናግዳለች

## - 200 ሄክታር መሬት ለኢንቨስትመንት ተዘጋጅቷል

**ውብሸት ሰንደቁ**

ጅማ፡- በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን የጅማ ከተማ አስተዳደር በ18 ወራት ውስጥ 120 ኢንቨስተሮችን መሳብ መቻሉን አስታወቀ።

የጅማ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ ነጅብ አባራያ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ከተማዋ ባለፉት 18 ወራት 120 የተመረጡ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን መሳብ ችላለች።

አቶ ነጅብ እንደገለጹት፤ የጅማ ከተማ ለኢንቨስትመንት ስበት ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥራለች። ለኢንዱስትሪዎች የሚሆኑ በርካታ ግብዓቶችና የአሠራር ሥርዓትም ተዘርግቷል።

የቡና፣ የማር፣ የፍራፍሬ፣ የበቆሎ፣ የሩዝ እና ሌሎች በርካታ የኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶች አሉ ያሉት ከንቲባው፤ በተለይ በአካባቢው የማዕድን ምርት መኖሩ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ምቹ ሁኔታ መፍጠሩን አብራርተዋል። ይህ መሆኑ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መልካም አጋጣሚ መሆኑንም ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከኢንዱስትሪዎች ባለፈ ለሆቴል ዘርፍ አልሚዎች ዕድሎች መመቻቸታቸውን የተናገሩት ከንቲባው፤ በአጠቃላይ በሁሉም ዘርፎች ኢንቨስት ለሚያደርጉ ባለሀብቶች በከተማዋ ሰላምና መረጋጋት መኖሩ እና የአካባቢው የአየር ንብረት ጥሩ መሆኑ ጅማ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እንድትሆን ያስችላታል ተብሏል።


ፎቶ ሀዲስ አብርሀ
አቶ ነጅብ አባራያ

በዚህም ባለፈው አንድ ዓመት ከስድስት ወር 15 ቢሊዮን ብር ያስመዘገቡ 120 የተመረጡ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ወደ ጅማ ገብተዋል፤ ከአዳዲሶቹ ኢንቨስትመንቶቸ መካከል ሆቴሎች፣ ሪል ስቴቶች፣ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም የቡና፣ የማርና የፍራፍሬ ማቀነባበሪያዎች እንደሚገኙም አብራርተዋል።

እንደ ከንቲባው ገለፃ፤ ከ120ዎቹ ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች 94 ያህሉ ሥራ ጀምረዋል። ፕሮጀክቶቹ በሀገር ውስጥ እና ውጪ ባለሀብቶች የሚገነቡ ናቸው።

በሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከሚገነቡ የሆቴል ዘርፍ ኢንቨስትመንቶች ኃይሌ ሪዞርት አንዱ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ሪዞርቱ በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን አስታውቀዋል። ይህም በጅማ ከተማ የሆቴልና የኮንፈረንስ ቱሪዝም ላይ የራሱ አወንታዊ አስተዋጽኦ ይኖረዋል ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የቡና ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአራት ወራት ውስጥ ተገንብቶ ወደ ሥራ መግባቱን አንስተው፤ ይህ ድርጅት በአንድ ጊዜ እስከ ሦስት ሺህ ኩንታል ኤክስፖርት የማድረግ አቅማ ያለው መሆኑን ተናግረዋል።

የጅማ ከተማ ከዚህ በላይ ኢንቨስተሮችን ለመቀበል መዘጋጀቷን የተናገሩት አቶ ነጅብ፤ በተለያዩ ዘርፎች ለሚሰማሩ ለሀገር ውስጥና ለውጪ ባለሀብቶች 200 ሄክታር መሬት ዝግጁ ተደርጓል ብለዋል።

የተዘጋጀው የኢንቨስትመንት መሬት የሆቴል እና ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን፣ የፍራፍሬና ቡና ዕሴት ለመጨመር እንዲሁም የማር እና ሌሎች ማቀነባበሪያ ዘርፍ የሚሠሩትን ሥራዎች ታሳቢ ያደረጉ ናቸው ነው ያሉት።

በከተማዋ የሌማት ቱሩፋት እና የከተማ ግብርና ዘርፍ ላይ በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ከንቲባው ተናግረዋል።

በማር፣ ወተት፣ ዶሮና እንቁላል እንዲሁም የጓሮ አትክልት የከተማው ነዋሪ እየተሳተፉ መሆኑን ጠቅሰዋል።

ከዚህ በፊት ከተሞች ምርት ተቀባይ እንጂ አምርቶ ተመጋቢ አልነበረም ያሉት ኃላፊው፤ በአሁኑ ጊዜ ከተሜው ማምረት በመጀመሩ ነባሩን የተቀባይነት አስተሳሰብ መስበር ተችሏል ብለዋል።

# በዘንድሮው ተፋሰስ ልማት በክልሉ ከ126 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ይለማል

**አምሳሉ ፈለቀ**

አዲስ አበባ፡- በሲዳማ ክልል በዘንድሮው የተፋሰስ ልማት ሥራ የአፈር ለምነትና ደህንነትን የሚያስጠብቁ ተግባራት በማከናወን ከ126 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት ለማልማት ታቅዶ ወደ ሥራ መገባቱን የክልሉ እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ አስታወቀ።

የተፋሰስ ልማት ሥራው ከአካባቢ ጥበቃ ባሻገር የአፈር ለምነትን የሚያስጠብቁና አሲዳማነት ለመከላከል የሚረዱ ሥራዎች እንደሚከናወኑም ተጠቁሟል።

የሲዳማ ክልል እርሻና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ ምክትልና የተፈጥሮ ሀብትና መሬት አስተዳደር ዘርፍ ኃላፊ የሆኑት አቶ ፍቅረኢየሱስ አሸናፊ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ በ646 ንዑስ ተፋሰሶች ላይ በሚከናወነው የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራ 126 ሺህ 500 ሄክታር በላይ መሬት ይለማል።

ዘንድሮ ከሚለሙት ንዑስ ተፋሰሶች 546ቱ ነባር ሲሆኑ 100 የሚሆኑት ደግሞ አዳዲስ ተፋሰሶች እንደሆኑም ተናግረዋል።

የአፈር ለምነት የሚጨምሩ የተለያዩ የእርከን ሥራዎች፣ ውሃ የማቀብና የመከለል ሥራ እንዲሁም በደጋማው አካባቢ የጠረጴዛማ እርከን ሥራዎች እንደሚከናወን የተናገሩት አቶ ፍቅረኢየሱስ፤ በቀጣይ ለሰላሳ ቀናት በሚከናወነው በዚሁ ሥራ ከ1 ነጥብ 7 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ይሳተፋልም ብለዋል።

በክልሉ ቡና አብቃይ በሆኑ ወረዳዎችም 70 በመቶ የተፋሰስ ልማት ሥራው በቡና ማሳ ላይ የሚሠራ ሲሆን፤ ይህም ተፈጥሯዊ



አቶ ፍቅረኢየሱስ አሸናፊ

ኮምፖስት የማዘጋጀት፡ ያረጁና ምርት የማይሰጡ የቡና ዛፎችን የመጎንደልና ነቀላ ሥራ በማከናወን በአዳዲስ የቡና ችግኞች የመተካት እንዲሁም ለቡና ምርታማነት የሚያገለግሉ ፓኬጆች ላይ ትኩረት ተሠጥቶ እንደሚሠራም ነው ያስረዱት።

በክልሉ በመጪው ክረምት በ32 ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የሚተከሉ 300 ሚሊዮን በላይ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው ችግኞች የማዘጋጀት ሥራው እየተከናወነ ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥ 4 ሚሊዮን የሚሆነው የፍራፍሬ ችግኝ እንደሆነም ኃላፊው ነግረውናል።

በተጨማሪም መሬቱን በኖራና በተፈጥሮ ማዳበሪያ በማከም አሲዳማነት እንዳይስፋፋ የማድረግና የአፈር ለምነት የመጠበቅ ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘም በክልሉ የባሕርዛፍ ተክል በስፋት እንደሚገኝና ይህም ምርታማነት ላይ ትልቅ ጉዳት በማድረሱና የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ሂደት ላይ እንቅፋት እየሆነ በመምጣቱ በሕብረተሰቡ ጥያቄ መሰረት በባለሙያዎች ጥናት ከተደረገ በኋላ አዋጅ በማዘጋጀት በክልሉ ምክር ቤት እንዲጸድቅ ተደርጎ በአሁኑ ወቅት ከአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራው ጋር የባሕር ዛፍ ተክልን ከእርሻ መሬትና ከወንዝ ዳርቻ ነቅሎ የመቀነስ ሥራ መጀመሩን ጠቁመዋል።

በክልሉ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑ ሥራዎች የአፈር መሸርሸርን በመከላከል፣ የአየር ንብረት በመጠበቅና ምርታማነትን በመጨመር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታ ማበርከቱን ተናግረዋል።

በየዓመቱ የሚከናወነው የተፋሰስ ልማት ሥራ ምርትና ምርታማነት በማሳደግና በረሃማነትን በመከላከል ከፍተኛ ድርሻ እያበረከተ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በዚህም ለአብነት የሚጠቀሱና ለሌሎችም አካባቢዎች መልካም ተሞክሮ የሚሆኑ የለሙና ጥብቅ አካባቢዎች እንዳሉም ያስረዳሉ።

የተፋሰስ ልማት ሥራው በክረምት ወራት ለሚከናወነው የአረንጓዴ አሻራ ልማት መሰረት የሚጥል በመሆኑም የችግኝ ጣቢያዎቹን የመለየት፡ ችግኞችን ለተከላ ወደተመረጡ ስፍራዎች የማዘወርና እንክብካቤ ሥራዎች ከዚሁ ሥራ ጋር ተቀናጅቶ እንደሚከናወን ነው የጠቆሙት።

የዘንድሮው የተፋሰስ ልማት ሥራ "የተፋሰስ ልማት ለተቀናጀ አፈር ጥበቃና ደህንነት" በሚል መሪ ቃል በክልሉ ሎካ አባያ ወረዳ ጂርማንቾ ቀበሌ ባለፈው ሰኞ ክልል አቀፍ የተቀናጀ ተፋሰስ ልማት ሥራው በይፋ መጀመሩ ይታወሳል።



## «አውደ ርዕዩ አዳዲስ የኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲዎችን ስመተግበር የሚረዱ ሃሳቦችን ስማመንጨት ያግዛል»

- ዮሐንስ አያሌው(ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

አዲስ አበባ፡- ከጥንት እስከ አሁን ያለውን የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ እንቅስቃሴን የሚያሳየው አውደ ርዕይ አዳዲስ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲዎችን ለመተግበር የሚረዱ ሃሳቦችን ለማመንጨት ያግዛል ሲሉ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዮሐንስ አያሌው(ዶ/ር) ገለጹ።

የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች "ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን" በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀው የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ ሰሞኑን ጎብኝተዋል።

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዮሐንስ አያሌው(ዶ/ር) በወቅቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ አውደ ርዕዩ አዳዲስ ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲዎች ሃሳቦች እንዲፈጠሩ የሚያግዝ ነው።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ከሚጎለብቱባቸው መንገዶች መካከል ጠንካራ ሕዝብና ጽኑ የዲፕሎማሲ አቋም መፍጠር አንዱ ነው ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ ከዚህ አንጻር አውደ ርዕዩ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃ በመስጠት አዳዲስ ሃሳቦችን ለማፍለቅ የሚረዳ መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች ለውጭ ኢንቨስትመንት ተመራጭ ሀገር በመሆኗ ኢኮኖሚ ዲፕሎማሲውን ይበልጥ ለማጠናከር የአውደ ርዕዩ መዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ ከሁሉም አቅጣጫ የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ የዲፕሎማሲው ሚና ቀላል የሚባል አይደለም። በዲፕሎማሲ ዘርፍ በሚከናወኑ ሥራዎች ኢትዮጵያ በአፍሪካ የውጭ ኢንቨስትመንት መዳረሻ መሆኗ እያደገ መጥቷል።

ባለሀብቶች ኢንቨስት በሚያደርጉበት ቦታ ላይ የፖሊሲ ጥንካሬ እንዲሁም የሀገርን ጥንታዊነት መሰረት ያደርጋሉ ያሉት ዶክተር ዮሐንስ፤ አውደ ርዕዩ በዕውቀት ላይ የተመሰረተ መረጃ ከመስጠት ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው አመላክተዋል።

አውደ ርዕዩ በተለይ የአፍሪካ ሕብረት ስብሰባ በተቃረበበት ጊዜ መከናወኑ የሀገሪቱ የዲፕሎማሲ ታሪክና ጽኑ አቋም የበለጠ እንዲተዋወቅ የሚረዳ መሆኑን ያመለከቱት ዶክተር ዮሐንስ፤ የአፍሪካ ዲፕሎማቶች ኢትዮጵያ የዘርፉ ማዕከል ሆና የቆየች ሀገር መሆኗን በአውደ ርዕዩ ሲመለከቱ ከሀገራችን ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጠናከር ፍላጎት ያድርባቸዋል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ዮሐንስ ገለጻ፤ አውደ ርዕዩ ስለኢትዮጵያ ይበልጥ በማወቅ ሁሉም ዜጋ ለሀገሩ አምባሳደር ሆኖ እንዲሰራ መነቃቃትን የሚፈጥር ነው።

አውደ ርዕዩ ኢትዮጵያ በአፍሪካ የዲፕሎማሲ መድረኮች ፈር ቀዳጅ የሆነች ሀገር ስለመሆኗ መገንዘብ የሚቻልበት ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ ይህም በዓለም መድረክ ትልቅ ተዓማኒነትን መጎናጸፍ አስችሏታል ብለዋል።

ዶክተር ዮሐንስ እንዳመለከቱት፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መስክ ብሔራዊ ጥቅሟን እያስከበረች ከጎረቤቶቿ ጋር መልካም ግንኙነት ለመመስረት ጥረት አድርጋለች። ይህን ጥረቷን በኢኮኖሚያዊ ዲፕሎማሲ ይበልጥ ማሳደግ ይገባል ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# "የባህር በር ስምምነቱ በዲፕሎማሲው ዘርፍ የተመዘገበ ትልቅ ውጤት ነው"

- አቶ ጥላሁን ከበደ
የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የባህር በር የመጠቀም ስምምነት በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲ ላይ የተመዘገበ ትልቅ ውጤት ነው ሲሉ የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ጥላሁን ከበደ ተናገሩ።

ርዕሰ መስተዳድሩ አቶ ጥላሁን ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ስምምነቱ የጋራ ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጥ፣የሁለቱ ሀገር ሕዝቦችን ወዳጅነትን የሚያሳድግ ነው።ይህ ስምምነትም ኢትዮጵያ በጠንካራ የውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲዋ የተገኘ ትልቅ ስኬት ነው።

ኢትዮጵያ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ተወዳዳሪ ለመሆን እና ሉዓላዊነቷን ለማስጠበቅ በእጅጉ የባህር በር ያስፈልጋታል ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ እንደ ትልቅ የሕዝብ ቁጥር እንዳለው ሀገር የሕዝቡን ፍላጎት ለማሳካት የባህር በር እጅግ አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የባህር በር የመጠቀም ስምምነት ለኢትዮጵያ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ባሻገር ደህንነትን የማስጠበቅ ትልቅ ጥቅም እንዳለው የተናገሩት አቶ ጥላሁን፤ ወደ ውጭ የሚላኩ እና የሚገቡ ምርቶችን በነጻነት ለማጓጓዝ የሚያስችል ትልቅ አቅም ለመፍጠርም እጅግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ባለፉት 30 ዓመታት የወደብ ጉዳይ በአመራር ደረጃ አጀንዳ ሆኖ አያውቅም ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፣ የተደረገው ስምምነት ከፍተኛ አመራሩ ምን ያህል በሳል እና ጠንካራ እንደሆነ ማሳያ መሆኑን ገልጸዋል። ስምምነቱ በፖለቲካዊ ፣ ማህበራዊ እና በኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት የተሳካ አካሄድ የተኬደበት መሆኑንም አመልክተዋል።

የባህር በር በሊዝ ለማግኘት ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው ስምምነት የትኛውንም ሀገር ቅር የሚያሰኝ እንዳልሆነ ተናግረው፤ በምሥራቅ አፍሪካ ያሉ ሀገራት ጠንካራ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ትስስር ያላቸው እንዲሆኑ ስምምነቱ እንደሚጠቅም ጠቁመዋል።

ሀገራቱ ራሳቸውን ችለው ተጽዕኖ ፈጣሪ እንዲሆኑም ኢትዮጵያ ያደረገችው ስምምነት ጠቃሚ እንጂ ማንንም የሚጎዳ እንዳልሆነ ገልጸዋል።

ለዓመታት ያለ ወደብ ለቆየች ሀገር እና ሕዝብ የባህር በር ስምምነቱን ስኬታማ ላደረጉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) እና በጋራ ለሠሩ አመራሮች ትልቅ አክብሮት አለኝ ያሉት አቶ ጥላሁን፤ መላው ኢትዮጵያዊያን ይህንን ሃሳብ በመደገፍ ስምምነቱ ውጤታማ እንዲሆን ከመንግሥት ጎን እንዲቆሙ ጥሪ አቅርበዋል።

# «ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉምን ኢትዮጵያዊያን ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ገለጹ። ከዋናው ሀገራዊ ምክክር በፊት በክልል ደረጃ ሀገራዊ ምክክር በቅርቡ እንደሚጀመርም ተገልጿል።

የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽነር ዶክተር ዮናስ አዳዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉምን ኢትዮጵያዊያን የሃሳብና የአመለካከት ውክልና አካቶ ይካሄዳል።

ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የሃሳብና የአመለካከት ውክልና የሚኖርበት ነው ያሉት ዶክተር ዮናስ ፤የኮሚሽኑ ዋና ዓላማ የሃሳብ ብዝሀነትን በማስተናገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገራዊ መግባባትን ማምጣት ነው ብለዋል።

የታጠቁ አካላት በሚገኙባቸው አካባቢዎች የሃሳብ፣ የአመለካከት ውክልና እንዲያገኙ እንደሚደረግ የገለጹት ኮሚሽነሩ፣ በተለይም በአማራና ኦሮሚያ ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች አንጻራዊ ሰላም በሚገኝበት ጊዜ ምክክሩ እንደሚካሄድ ነው የገለጹት።

በአሁኑ ጊዜ በክልል ደረጃ ምክክር ለማድረግ ከአማራና ትግራይ ክልሎች በስተቀር የተሳታፊ ልየታ መጠናቀቁን ጠቅሰው፤ በክልል ደረጃ የሚያካሄደው ሀገራዊ ምክክር በቅርቡ መካሄድ እንደሚጀምርም ተናግረዋል።

በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ጋር በተደረገ ውይይት ጠቃሚ ግብዓቶች መገኘታቸውን ገልጸው፤ በአፍሪካና መካከለኛው ምሥራቅ፣ በአውሮፓ፣ በእስያና ፓስፊክ፣አውስትራሊያና ዩዚላንድን ጨምሮ፣ካናዳና፣አሜሪካ፣ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጋር የተሳካ ውይይት መደረጉን አስረድተዋል።

ወደ ዋናው ሀገራዊ ምክር ለመግባት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የማካተት ሥራ እየተሰራ መሆኑን በመግለጽ፤ በቀጣይ በዌስ ኮስት አካባቢ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ጋር ውይይት ይካሄዳል ብለዋል።

በበይነ መረብ አማካኝነት በተካሄደው ውይይት ጠቃሚ ግብዓቶች መገኘታቸውን ገልጸው፤ በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያዊን ምክክሩን ለመደገፍና ለመሳተፍ የተዘጋጁ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በኮሚሽኑ በኩል ሕዝብን በማወያየት ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚመጣበትን ሁኔታ ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑን አመልክተው፤ በተለይም ተግዳሮቶችን በመቋቋም ከሕዝብ፣መንግሥትን ጨምሮ፣ከፖለቲካ ፓርቲዎችና፣ከሲቪክ ማህበራት ጋር እንደሚሰሩ ጠቁመዋል።

በተለያዩ አካባቢዎች የሚታዩ ችግሮችን በመነጋገር፣በመመካከር፣ በጥበብና ፣በትዕግስት መፍታት እንደሚቻል የገለጹት ኮሚሽነሩ፤ የምክክሩ ሂደት ባልተጀመረባቸው አካባቢዎች ላይ የሰላም ሁኔታ መሬት እንደያዘ የሚካሄድ ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም ከሲቪክ ማህበራት፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ጋር ጠቃሚ የሆነ ውይይት ማካሄዳቸውን ጠቅሰው፤ ሁሉን አቀፍና ውጤታማ የሆነ ምክክር ለማካሄድ እየተሰራ መሆኑንም ገልጸዋል።

# የዓባይ ግድብ - ተጨማሪ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ከፍተኛ ገበያ የሚያስገኝ የቱሪስት መስህብ ነው ብዬ አምናለሁ። ምስክርነቱን የምሰጠው በውሃ ሀብት መሐንዲስነቴ ነው። ይህን የግድቡን ሌላ ኃይል ከአሁኑ ቀድምን ተረድተን ልንዘጋጅበትና ልንጠብቀው ይገባል" ብለዋል።

የዓባይ ግድብ በተለይም ነፋሻ አየር በሌላቸው አረብ ሀገራት ላሉ ዜጎች በቅርብ ርቀት የሚያገኙት ገነት እንደሚሆን አመላክተው፤ ጎብኚዎች ግድቡ ላይ በሚኖር ሙዚየም የተሰራበትን ሂደትና ታሪኩን በተንቀሳቃሽ ምስልና በድምጽ የሚከታተሉበትና በግድቡ ምክንያት በተፈጠረው ሃይቅ ላይ በሚገኙ ደሴቶች በጀልባዎች እየተዘዋወሩ ዓለማቸውን የሚቀጩበትን እድል ያገኛሉ ነው ያሉት።

እንደ ዓባይ ግድብ አይነት ግዙፍ የግድብ ግንባታ የራሱን ከተሞች ይፈጥራል፤ ፈጥሯልም የሚሉት የውሃ መሐንዲሱ፤ ብልጥ የሆኑ ኢንቨስተሮች በአካባቢው ቦታ ወስደው ለማልማት ማሰብ አለባቸው ሲሉ ይመክራሉ።

አክለውም ግድቡ ለውጭ ሀገራት ዜጎች ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያንም ትልቅ መዳረሻ መሆኑን ጠቁመው፤ ሁላችንም ሄደን ለመጎብኘት መዘጋጀት አለብን፤ ቢያንስ አንድ ቀን እንጎበኘዋለን ብለን ልናስብ ይገባናል ብለዋል።

በተለያዩ ዓለም አቀፍ ሚዲያዎች ላይ በመቅረብ በዓባይ ግድብ ዙሪያ የኢትዮጵያን አቋም በመግለጽ የሚታወቁት የፖለቲካ ሳይንስ ተመራማሪው ሙሳ ሼኮ በበኩላቸው፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) ግድቡ ባስገኘው ትልቅ ሰው ሰራሽ ሀይቅ ውስጥ የተፈጠሩት ከ70 በላይ ደሴቶች ለቱሪዝም ሥራ እንዲውሉ ትኩረት ተሰጥቶ እንደሚሰራ መግለጻቸውን አውስተው፣ ውሃው ከሚሰጠው ከፍተኛ የዓሳ ምርት ጋር ተደምሮ አካባቢው ከፍተኛ ቱሪስት የሚጎርፍበት አለም አቀፍ የቱሪስት መስዕብ እንዲሆን ታስቦ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ይገልጻሉ።

ግድቡ በቱሪስት መዳረሻነትም ኃይል በማመንጨት ከሚያስገኘው የማይተናነስ ገቢ የሚፈጥር እንዲሆን የብዙ አካላትን ርብርብ የሚጠይቅ ትልቅ ሥራ እንደሚፈልግ የጠቆሙት አቶ ሙሳ፤ ቱሪዝም ኢትዮጵያ እስካሁን በቅጡ ያልተጠቀመችበት ዘርፍ ነው። ኬንያ እና ግብጽን ብንመለከት ትልቁን የውጭ ምንዛሬ የሚያገኙበትና ክምችታቸውን የሚያሳድጉት ለም አቀፍ ጎብኚዎችን በመሳብ ነው። ሁለቱ ሀገራት የእኛን ሀገር ያህል የቱሪሰት መስህብ የላቸውም። ነገር ግን ትኩረት ሰጥተው ያሏቸውን መዳረሻዎች ለማልማት ጠንክረው በመስራታቸው ከፍተኛ የቱሪስት ፍሰት እያስተናገዱ መሆኑን ገልጸዋል።

የዓባይ ግድብ ኢትዮጵያውያንን አንድ ያደረገ ታሪካዊ ፕሮጀክት መሆኑንና ቦንድ ከመግዛት ጀምሮ በተለያዩ ሥራዎች ግድቡ ላይ አሻራውን ያላኖረ ሰው እንደሌለ አውስተው፤ ይህ ፕሮጀክት የተለፋለትን ያህል ሁለንተናዊ ውጤቱ ማስገኘት አለበት ብለዋል።

ኢትዮጵያ በሺዎች የሚቆጠሩ የቱሪስት መስህቦች ያሏት ሀገር መሆኗን ጠቅሰውም፤ "የዓባይ ግድብ እነዚህ መስህቦች ላይ ተጨምሯል። ግድቡን ወደ ዋነኛ የቱሪስት መስህብነት የመቀየር ኃላፊነት አለብን" ሲሉ አሳስበዋል።

የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኢንስቲትዩት የስልጠና ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሀብታሙ ክብረት የዓባይ ግድብ የሚገኝበት አካባቢ ትልቅ የቱሪስት መዳረሻ እንደሚሆን በማሰብ ተቋማቸው በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከሚገኙ አካባቢዎች የአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅን በመምረጥ የቱሪዝም ዘርፉ የሚፈልገውን የሰው ኃይል በዋነኝነት ከአካባቢው ለማፍራት እንዲቻል ድጋፍ እያደረገ እንደሚገኝ ይናገራሉ።

እንደ ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ኢንስቲትዩት የሰው ኃይል መፍጠር እንዲችል በሥራ ላይ ስልጠና፣ ወርክ ሾፕ በማደራጀት፣ በመምህራን ልማት እና አጠቃላይ በሆነ የማማከር ሂደት ለአሶሳ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ እገዛ እያደረገ ነው።

የውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር የዓባይ ግድብን ማዕከል ያደረገ አዲስ ከተማ በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ እንደሚመሰረትና ለሚመሰረተው አዲስ ከተማ የሀብት ምንጭ የሚሆነው ከግድቡ ጀርባ የሚታቆረው ውሃ መሆኑን መግለጹ ይታወሳል።

ከዓባይ ግድብ የኃይል አቅርቦት ከማግኘት ባሻገር ትልቅ የቱሪስት መዳረሻ እንዲሆን ታስቦ እየተደረገ ያለው ዝግጅት ተጠናክሮ ከቀጠለ የቱሪዝሙን ዘርፍ በማነቃቃት ኢትዮጵያ ለኢኮኖሚዋ ተጨማሪ የጀርባ አጥንት የምታገኝበት ጊዜ ቅርብ ይሆናል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ቀኑ ለአርብቶ አደሩ መጪው ዘመን ምቹ መደላድልን ይፈጥራል!

በአርብቶ አደሮች መኖሪያነት ተጠቃሽ ከሆኑ የዓለም አካባቢዎች የአፍሪካ ቀንድ (ምሥራቅ አፍሪካ) አካባቢ አንዱ ነው። ኢትዮጵያን ጨምሮ በአካባቢው የሚገኙት ሶማሊያ፣ ኤርትራ፣ ኬንያ፣ ሶማሌ ላንድ ጅቡቲና ደቡብ ሱዳን የአያሌ አርብቶ አደሮች መኖሪያ ናቸው።

የአርብቶ አደርነት ሕይወት በአብዛኛው በእንስሳት እርባታ ላይ የተመሠረተ፤ ሁሌም ቢሆን ከውሃና ከግጦሽ ሳር ፍለጋ ጋር በተያያዘ እንቅስቃሴ የሚበዛበት ነው፤ በዚህ የተነሳም በሀገራቱ አርብቶ አደር ማኅበረሰብ መካከል ያሉ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮች ከድንበር መስመር ያልፋሉ።

በተለይም የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች ከአንድ ቤተሰብ የሚቀዱና፤ ማኅበራዊ ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ መሠረታቸውም አንድ ሊባል የሚችልም ነው፡፡ ዕጣ ፈንታቸው በብዙ መልኩ የተሳሰረ መሆኑም የአንድ ቤተሰብ አባል ያህል ሆነው የሚታዩበትን እውነታ ፈጥሯል። ይህም ሁኔታ አሁናዊ ብቻ ሳይሆን ቀጣይ ዕጣ ፈንታቸው በብዙ መልኩ የተሳሰረ እንዲሆንም አድርጎታል።

የቅኝ ግዛት የሴራ አስተሳሰብ እነዚህ ሕዝቦች በተለያዩ የድንበር መስመሮች ተከፋፍለው እንዲኖሩ ቢያስገድዳቸውም፤ ተጨባጭ የዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ግን ከድንበር መስመሮች በዘለለ፤ በወንድማማችነት መንፈስ ዘመናትን መሻገር የቻለና ዛሬም ቤተሰብ ሆነው እንዲኖሩ ያደረጋቸውም ነው።

የአርብቶ አደሮቹ ሁለንተናዊ የሕይወት መስተጋብር፤ ቀጣይ ዕጣ ፈንታቸውን በጋራ ለመቅረጽ እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ቢወሰድም፤ ዓለም እየተመራችበት ባለችው የሴራ ፖለቲካ መንገድ የተነሳ መልካም አጋጣሚውን ወደ ተጨባጭ እውነታ መቀየር ሳይቻል ዘመናት አልፈዋል፤ አካባቢው በዚህ መልካም አጋጣሚ ተጠቃሚ መሆን ሲገባው፣ ከዚህ ይልቅ የግጭት ማዕከል ለመሆን ተገዷል።

በዚህም የአካባቢው አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች የብዙ የተፈጥሮ ጸጋዎች ባለቤት ቢሆኑም ፤ ለከፋ ድህነትና ኋላ ቀርነት፤ ከዚህ ለሚመነጭ ስደት ተዳርገዋል፤ አካባቢው በአየር ንብረት ለውጥ የተነሳ በድርቅ በተደጋጋሚ የሚመታ መሆኑም ሌላው የአካባቢው ፈተና ሆኗል፤ ይህ ሁሉ ችግር አርብቶ አደሮቹ ሕይወታቸውን በጠባቂነት እንዲያሳልፉ ፣ አንገት የሚያስደፋ ሕይወት እንዲመሩ ተገደዋል።

የአርብቶ አደሮቹ አሰፋፈርም ሆነ፤ ድንበር ተሻጋሪ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብራቸው ፤ስለጋራ ዕጣ ፈንታቸው ቁጭ ብለው መወያየት እንዲችሉ፤ ለጋራ ፍላጎቶቻቸው እውን መሆን ትኩረት ሰጥተው በጋራ የሚሠሩበትን መንገድ እንዲቀይሱ፣ የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የሚወስኑበትን የተሻለ ዕድል መፍጠር የሚያስችላቸው አልሆነም፡፡

ከዚህ አንጻር ከጥር 17 እስከ ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም በሚሊኒየም አዳራሽ ‹‹አርብቶ አደርነት የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ- ቀለም›› በሚል መሪ ሃሳብ የሚካሄደው 19ኛው የአርብቶ አደሮች ቀን በዓል ፋይዳው ከፍተኛ ይሆናል፤ የቀጣናው አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች ነገዎቻቸውን ብሩህ ለማድረግ የሚወያዩበትን የተሻለ ዕድል ይፈጥራል።

የአካባቢው ሀገራት አርብቶ አደሮችን ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ትስስር ከማጠናከር ጎን ለጎን የጋራ በሆኑ እንደ ድርቅ፤ የጎርፍ አደጋ እንዲሁም ኮንትሮባንድ ንግድ በመሳሰሉ ችግሮች ዙሪያ በጋራ በመምከር መፍትሔ ለማመላከት፤ በልማት አማራጮች ላይ ይበልጥ ተቀራርበው እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርም ይረዳቸዋል።

ልምድና ተሞክሮቻቸውን በመለዋወጥ የንግድ ትስስራቸውን ይበልጥ እንዲያሳድጉ፣በጋራ ችግሮቻቸው ዙሪያ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያገለብቱ፣ ከሁሉም በላይ ዘላቂ በሆኑ የጋራ ተጠቃሚነት ጉዳዮች ላይ በመሥራት የተሻሉ ነገዎችን ለመፍጠር ትልቅ አቅም እንደሚሆናቸው ይታመናል።

በተለይም የተፈጥሮ ጸጋዎቻቸውን አቀናጅተው፤ ካሉበት እና ለረጅም ዘመን አብሯቸው ከዘለቀው ድህነትና ኋላቀርነት የሚወጡበትን ስትራቴጂክ እሳቤ በመፍጠር ዘመኑን የሚመጥን ማኅበራዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብር መፍጠር የሚያስችላቸውን፤ በዚህም መጪውን ዘመናቸውን ለራሳቸውና ለመጪዎቹ ትውልዶች ብሩህ አድርገው ማስረከብ የሚያስችላቸውን ተግባር ከወዲሁ ማከናወን ለመጀመር ምቹ መደላድልንም ይፈጥርላቸዋል።

ከዚህም ባለፈ የቀጣናውን ሀገራት ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ትስስር ይበልጥ ማጠናከር የሚያስችል፣ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ እንደ ሀገር ሰጥቶ በመቀበል መርህ ከአካባቢው ሀገራት ጋር አብሮ ለማደግ በጀመረችው የልማት ስትራቴጂ ዙሪያ ለዋና ባለጉዳዮቹ የጠራ መረጃ ለማስተላለፍ ትልቅ መድረክ ሆኖ ሊያገለግልም ይችላል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## «ቢበርም ነብር ነው!»

ስሜነህ ደስታ

ግብጽ ከሕዳሴ ግድብ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተለያዩ ጊዜያት ለድርድርና ለውይይት የማያመች የተምታታ ባህርይ እያሳየች ያለችውን ሁኔታ ስመለከት፤ በተደጋጋሚ የተደረጉ የሦስትዮሽ ድርድሮች ያለስምምነት መበተናቸውን ሳስታውስ፤ በአንድ ወቅት አንድ ወዳጄ የነገረኝ ታሪክ ትውስ ይለኛል። ታሪኩ የሚጀምረውም ሆነ የሚጠናቀቀው በአንድ የእንስሶች ፓርክ ውስጥ ሁለት ሰዎች ቆመው በሚያደርጉት ክርክር ነው።

ታሪኩ እነሆ! ከዕለታት በአንዱ ቀን፣ ሁለት ሰዎች ፓርክ እየጎበኙ ሳለ የአንድ ዛፍ አስተዳደግ ማርኳቸው ያደንቃሉ። አድናቆታቸውን እየገለጹ ባሉበት ጊዜ፣ አንደኛው የዛፉ ዝርያ ምን እንደሚባልና በሚያዩት መልኩ ቁመቱ ለማደግ የሚወስድበት ዓመት ስንት እንደሚሆን በመተንተን ያስረዳል። በመቀጠልም በዛፉ ላይ ቆሞ የሚታየው የአዕዋፍ ዝርያ እንደሆነ ይናገራል።

ሁለተኛው ተመልካች ስለዛፉ ዝርያ የዕጽዋት ዕውቀት ስለሌለኝ አላውቅም፤ ከፊት ለፊታችን ትንሽ ራቅ ብሎ የሚገኘው ዛፍ ላይ ተኝቶ ያለው ግን የአዕዋፍ ዝርያ ሳይሆን የዱር እንስሳ የሆነው ነብር ነው ይለዋል። የመጀመሪያውም ተናጋሪ የእሱ ትክክል መሆኑን ለማሳመን የመከራከሪያ ሃሳቡን ያጠናክርልኛል ያለውን ከነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ለማስረዳት፣ ራቅ ስላለ አልታይህ ብሎ ይሆናል እንጂ ከታች መቁጠር ስንጀምር ሦስተኛው ቅርንጫፍ ላይ ያለው መንቁሩ ነው እየውልህ ሲያንቀሳቅሰው አለው።

ሁለተኛውም፣ እንዲያውም ሦስተኛው ቅርንጫፍ ላይ ያለው አሁን እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው የነብሩ ጥፍር ነው፤ ከጥፍሩ አጠገብ ያለው ጭራው አይታይህም ወይ? በማለት ይጠይቀዋል። ጥያቄውን ሲመልስለት ጭራ ያልከው የአዕዋፉ ክንፍ ነው፤ እንዲያውም ሊበር ነው በማለት በአሸናፊነት መንፈስ መለሰለት። ይህ ይሁን እንጂ የሚከራከሩበት አካል ሳይንቀሳቀስ ብዙ ጊዜ ዛፉ ላይ ስላሳለፈ ክርክራቸው መቋጫ አላገኘም።

እንዲህ እንዲህ እያሉ የራሳቸውን የመከራከሪያና የማሳመኛ ሃሳብ እያነሱ ሲነጋገሩ ከቆዩ በኋላ፣ በመጨረሻ ዛፉ ላይ ያለው አዕዋፍ ነው በሚል ሲከራከር የቆየው ሰው ክርክራቸው መቋጫ እንዲያገኝ በሚል የሚያስማማ ያለውን የተለየ ሃሳብ ያነሳል። ይኸውም፣ ዛፉን ድንጋይ ልወርውርና ልምታው። አዕዋፍ ከሆነ ደንግጦ ይበራል፤ ነብር ከሆነ ይዘላል። በዚህ ትስማማለህ ወይ? በማለት ያመጣውን ሃሳብ በማድነቅ ይጠይቀዋል።

ዛፉ ላይ ያለው ነብር ነው በሚል የሚከራከረው ደግሞ ድንጋይ እስከመወርወር የሚያደርስ አይደለም፤ በግልጽ በሚታይ ሁኔታ ዛፉ ላይ ያለው ነብር ነው በማለት የመጀመሪያውን ሃሳብ ያጠናክራል።

በመጨረሻ በስንት ክርክር ድንጋይ ተወርውሮ ፍተሻ ማድረጉ ላይ ስምምነት ይደርሳሉ። ከዚያም ድንጋይ ይወርወር ብሎ ሃሳብ ያቀረበው በተከታታይ ድንጋይ ወደ ዛፉ ይወረውራል። ሲከራከሩበት የነበረውም አካል ተነስቶ ይበራል።

በዚህ ጊዜ አዕዋፍ ነው ያለው ክርክሩን አሸንፌአለሁ በሚል፣ በኩራት ይኸው በረረ፤ ነበር አይደለም ሲለው፤ ያኛው ደግሞ ቢበርም ነብር ነው፤ እዘላለሁ ብሎ ነው የበረረው! በማለት ቀደም ሲል የያዘውን አቋም እንደማይለቅ አሳወቀው።

የሁለቱ ሰዎች ክርክር በየትኛውም መመዘኛ መቋጫ እንደማያገኝ ‹‹ቢበርም ነብር ነው፤ እዘላለሁ ብሎ ነው የበረረው! ›› የሚለው አባባል ያመላክታል። ምናልባት መቋጫ የሚያገኘው አዕዋፍ ነው ያለው ልክነው ቢበርም ነብር ነው የሚለውን ሃሳብ ከተቀበለ ነው።

ሱዳን በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ በሚደረግ ድርድር የራሷን ጥቅም ከማስጠበቅ አንጻር ይህ ነው የሚባል ጉልህ እንቅስቃሴ እያደረገች እንዳልሆነ ጉዳዩን በጥልቀት የሚከታተሉ ምሁራንና ተንታኞች ሲናገሩ ይደመጣል። ስለሆነም ከላይ የቀረበው ታሪክ ሱዳንን አይመለከትም። ግብጾች ግን በፖለቲካዊ ምክንያት በሕዳሴ ግድብ ዙሪያ ስምምነት ተደርጎ እንዲቋጭ የሚፈልጉ አይመስሉም፤ የዓባይ ጉዳይ ዘላለማዊ የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ እንዲቀጥል ይፈልጋሉ።

ዓባይ ለግብጽ ሕዝብ ሁሉ ነገራቸው ነው። ይህን የሚያውቁት የግብጽ ፖለቲከኞች ጠንከር ያሉበት ወቅት ሲመስላቸው እንዲሁም የሀገራቸውን ሕዝብ ድጋፍና የሕዝቡን የልብ ትርታ ያነሳሱ ሲመስላቸው ድርድሩን የሚያደናቅፍ ተግባር ያከናውናሉ። ከድርድሩ ወጥተናል፣ አልተስማማንም፣ ወዘተ. በማለት ይናገራሉ። ኢትዮጵያ አየል ብላ መታየት ጀምራለች ባሉበት ጊዜ ደግሞ በዓባይ ጉዳይ ለመደራደር ፍላጎት ያሳያሉ።

ግብጾች እንዲህ ያለ ወጣ ገባ ሃሳብ ይዘው ሲንቀሳቀሱ ግድቡ ተገንብቶ አጠቃላይ አፈጻጸሙ ከ94 በመቶ በላይ ደርሷል። አፈጻጸሙ እዚህ ደረጃ እንዳይደርስ ግብጽ ያልቆፈረችው መሬት፣ ያልቧጠጠችው ዳገት የለም። ነገር ግን በኢትዮጵያውያን የተባበረ ጥረት ግድቡ አሁን ላለበት ደረጃ ደርሷል። በአራት ዙር የውሃ ሙሌት 44 ቢሊዮን ሜትር ኪዩብ ለመያዝ ተችሏል።

ኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብን 4ኛ ዙር የውሃ ሙሌት መጠናቀቁን ካሳወቀች በኋላ የግብጽ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በማኅበራዊ ትስስር ገጹ መግለጫ አውጥቷል። በመግለጫው፣ ከተፋሰሱ ሀገራት ጋር ስምምነት ላይ ሳይደረስ የሕዳሴ ግድብ የውሃ ሙሌት መቀጥል በ2015 የተፈረመውን የመርህ ስምምነት እና ዓለም አቀፍ ሕግን የሚጥስ ነው ብላለች። ኢትዮጵያም በሕዳሴው ግድብ ውሃ ለመያዝ ማንንም ፈቃድ የመጠየቅ ግዴታ እንደሌለባት አሳውቃለች።

ግብጽ በቅኝ ገዥዋቸዋ በ1959 የተፈረመውና፣ የአብዛኛውን የውሃውን ድርሻ የሚሰጣትን የቅኝ ግዛት ስምምነት ሙጥኝ ብላ «ታሪካዊ» ተጠቃሚነት በሚል መርህ የወንዙን ውሃ ሙሉ በሙሉ በበላይነት ለብቻዋ የመጠቀም ፍላጎት አላት። ስምምነቱ ኢትዮጵያን ያላካተተ ከመሆኑ በተጨማሪ ግብጽ 55.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውሃን እንዲሁም ሱዳን 18.5 ቢሊዮን ኪዩቢክ ውሃን እንድታገኝና 86 በመቶ የናይልን ውሃ የምትገብረውን ኢትዮጵያ ያለ ውሃ የሚያስቀር አግላይና ኢፍትሃዊ ነው። ግብጽ ድርድሩን ምክንያት በማድረግ ይህንን ስምምነት ኢትዮጵያ እንድትቀበል ጫና እያደረገች ነው። ይህ ደግሞ በማንኛውም ሁኔታ ተቀባይነት የሚያገኝ ሃሳብ አይደለም።

ኢትዮጵያ የተለያዩ ጫናዎችን በመቋቋም እንዲሁም አስቸጋሪ ሁኔታዎችን በማለፍ ግድቡ ካለበት ደረጃ እንዲደርስ አድርጋለች። አሁን ግድቡ ተገንብቷል፤ ውሃ ይዟል። ስለሆነም ራሱን ይጠብቃል። ግድቡ መገንባት የለበትም፤ እናፈርሰዋለን የሚሉ ዛቻዎች አሁን ዋጋ የላቸውም። ግብጽ በተቻላት መጠን ሁሉ ለራሷ ደህንነት ስትል ግድቡን ለመጠበቅ የራሷን አስተዋጽኦ ከማድረግ ታፈገፍጋለች ብሎ ማሰብ ይከብዳል። አሁን ኢትዮጵያ ማድረግ ያለባት የተለያዩ ጫጫታዎች ቢኖሩም የራሷን የቤት ሥራ መሥራት ነው።

ሰሞኑን ኢትዮጵያ፣ ግብጽ እና ሱዳን በአዲስ አበባ ሲያደርጉት የነበረው የሕዳሴ ግድብ የሦስትዮሽ ድርድር ያለ ስምምነት ተጠናቋል። ድርድሩ ያተኮረው በሕዳሴ ግድብ ውሃ አሞላል እንዲሁም ዓመታዊ የሥራ ሂደትን የተመለከተ መመሪያ ላይ ነበር። ግብጽ በምትከተለው እና ሙጥኝ ብላ በያዘችው የቅኝ ግዛት ዘመን አስተሳሰብ ምክንያት ጉዳዩ ፈር ሳይዝ ቀርቷል።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ኢትዮጵያ የዓባይን ውሃ በፍትሐዊ እና ምክንያታዊ በሆነ መርህ ላይ በመመስረት የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት የምታደርገውን ጥረት እንደምትቀጥል አሳውቋል። በግብጽ በኩል ግን የቅኝ ግዛት አስተሳሰቧን በማጠናከር « ቢበርም ነብር ነው፤ እዘላለሁ ብሎ ነው የበረረው! » የሚለውን አቋሟን እንደያዘች ነው ።

የሕዳሴ ግድብን በተመለከተ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከዚህ በፊት እንዳደረግነው በመተባበር ፍጻሜውን እንዲያገኝ እስካደረግን ድረስ ግብጽ በድርድሩ ለመቀጠል ፍላጎት አለማሳየቷ ሊያሳስበን አይገባም። የእኛ መተባበርና መጠንከር ወደ ድርድሩ እንድትመጣ የሚያደርጋት አንዱ ገፊ ምክንያት ይሆናል። ወደፊት ደግሞ የእኛን አንድነት በማየት « ቢበርም ነብር ነው፤ እዘላለሁ ብሎ ነው የበረረው! » የሚለውን አቋሟን በመቀየር ለእውነተኛ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት ለመተባበር መትጋቷ አይቀርም።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እያደቀቀ ያለው ኮንትሮባንድ

የሕገ ወጥ ንግድ ወይም የኮንትሮባንድ ዜናዎች የመንግሥትም ሆኑ የግል ብዙኃን መገናኛዎች የየዕለት የዜና ማሟሻ ከሆኑ ሰነባበቱ። ወርቅ፣ ቡና፣ ሳፋየር፣ የውጭ ምንዛሬ፣ የቅባት እህል፣ ጫት፣ መጠጥ፣ እህልና ጥራጥሬ፣ የቁም እንስሳት፣ ዓሣ፣ ነዳጅ፣ ወዘተረፈ ምን አለፋችሁ ወደ ውጭ በኮንትሮባንድ የማይወጣም ሆነ የማይገባ ነገር የለም ማለት ይቻላል። የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች፣ የውጭ ምንዛሬ፣ ብረት፣ የጦር መሣሪያ፣ የእጅ ስልኮች፣ ጨርቃጨርቅ፣ የተለያዩ ሸቀጦች፣ ትንባሆ፣ መድኃኒት፣ ወዘተረፈ በተለያየ መንገድ በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር ይገባሉ።

ይህ ደግሞ ኢኮኖሚውን ከመሠረቱ እንደ ምስጥ እየበላውና እየቦረቦረው ነው። ሕጋዊ ነጋዴዎችን ከገበያ እያስወጣ፤ ፋብሪካዎች በሕገ ወጥ መንገድ ከሚገቡ ምርቶች ጋር መወዳደር ስላልቻሉ እየተዘጉ ስለሆነ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሠራተኞች እየተሰናበቱ ይገኛል። የጨርቃጨርቅና የብረት ፋብሪካዎች ለሕገ ወጥ ንግዱ ቀድመው መሰዊያው ቀርበው እየተሰዉ ነው። በውጭ ምንዛሬ እጦት፤ በጦርነትና በጸጥታ ችግር አሳሩን እየበላ ባለ ኢኮኖሚ በአናቱ ሕገ ወጥ ንግድ ተጨምሮ ክፉኛ እየደቆሰው ይገኛል። ይህ ትናንት የተጀመረ ሳይሆን ባለፉት አመታት እንደ አዲስ እየገነገነ የመጣ ሕገ ወጥነት ነው።

በየዓመቱ ከአራት ቢሊዮን ዶላር የውጭ ምንዛሬ እንደሚሸሽ በተባበሩት መንግሥታት ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፎር አፍሪካ መረጃ ያሳያል። ይህም ከሀገሪቷ የሚወጡት ምርቶች ሊያስገኙት ይችሉ ከነበረው ገቢ ጋር ተዳምሮ ሀገሪቷ የምታጣው የውጭ ምንዛሬ ቀላል እንደማይሆን ያሳያል። በተጨማሪ ብሔራዊ ባንክን ጨምሮ ከተለያዩ ተቋማት የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ የኮንትሮባንድ መስፋፋት ለትይዩ የውጭ ምንዛሬ ገበያው ማደግ አንድ ምክንያት ሲሆን የብር ዋጋ እንዲዳከም አድርጓል።

በአሁኑ ሰዓት 1 ዶላር እስከ 40 ብር ድረስ ለመመንዘሩ እንደ ዋነኛ ምክንያት ይጠቀሳል። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ከፍተኛ መጠን ያላቸውን ፍላጎቶቻቸውን ከውጭ ሀገራት በሚያስገቡት ምርቶች ለሚያሟሉ ሀገራት፤ የውጭ ምንዛሬ ያለው አስፈላጊነት ከምንም በላይ ነው። በተለይም መሠረተ ልማት ግንባታ ለማካሔድና ወሳኝ የሆኑ የካፒታል ዕቃዎችን ለማስገባት እንዲሁም ዕዳዎችን ለመክፈል የውጭ ምንዛሬ አስፈላጊነቱን ከፍ ያደርገዋል።

ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሀገሪቷ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ መጠን መጨመር የመንግሥት ዋነኛ ግብ ቢሆንም ላለፉት አሥርት ዓመታት ማሳካት ግን አልተቻለም። ለአብነት የማዕድን ዘርፉን መጥቀስ ይቻላል። ከ650 ሚሊዮን ዶላር የውጪ ንግድ ገቢ ያስገኘው የማዕድን ዘርፍ በ2011 በጀት ዓመት ወደ 44 ሚሊዮን ዶላር መውረዱ በማዕድን ሚኒስቴር ይፋ መደረጉ ይታወሳል። ከትግራይ ክልል በባህላዊ መንገድ ተመርቶ ይቀርብ የነበረ ወርቅ ሙሉ በሙሉ መቋረጡን ያስታውሷል።

ለገቢው መቀነስ ዋነኛ ምክንያት ተደርጎ የተጠቀሰው የኮንትሮባንድ ንግድ መስፋፋት ሲሆን ችግሩ በየጊዜው እየተባባሰ ነው። በአንድ ወቅት የንግድና ኢንዱስትሪ ቋሚ ኮሚቴ ወደ ሱማሌ ክልል ጉብኝት ባደረገ ወቅት በየቀኑ ከ1 ሺህ 600 በላይ የቁም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ በሱማሌ ክልል በኩል ከሀገር እንደሚወጣ አስታውቆ ነበር። በተጨማሪም ዋሴ ብርሃኑ (ዶ/ር) የተባሉ የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ባደረጉት ጥናት ኬንያ ድንበር አካባቢ ባሉ አንዳንድ ከተሞች ወደ ውጭ የሚላኩ ከብቶች 70 በመቶ የሚሆኑት በሕገወጥ መንገድ ከሀገር እንደሚወጡ፤ የጉምሩክ ኮሚሽን መረጃ እንደሚያሳየው ከሆነ ደግሞ ከ2011 ዓ.ም በነበሩ አምስት ዓመታት ውስጥ ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ የሚገመት የኮንትሮባንድ ዕቃዎች በመንግሥት መያዛቸውን አዲስ ማለዳ ጋዜጣ አውስታለች።

በሕገወጥ የንግድና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ያተኮረውና የኢኮኖሚኒስት መጽሔት አካል በሆነው ዘ ኢኮኖሚስት ኢንጀሊጀንስ ዩኒት የተሰኘው ተቋም በኩል ከሦስት አመት በፊት የተካሄደ ጉባዔ ላይ በረዳት ፕሮፌሰር ፈንታ ማንደፍሮ በቀረበ ጥናት፤ በኢትዮጵያ በሁሉም የንግድ መስኮች ከሚታየው እንቅስቃሴ 40 በመቶው በሕገወጥ ንግድ መስክ የሚመደብ ነው ሲሉ መግለጻቸው አይዘነጋም። በተለይም በጨርቃ ጨርቅና አልባሳት መስክ፣ በመድኃኒትና በትንባሆ ምርቶች ላይ የሚታየው ሕገወጥ የሀገር ውስጥ ንግድ ከፍተኛ ደረጃ የያዘ ነው።

ከዚህም ውስጥ የጨርቃ ጨርቅ ዘርፉ የ48 በመቶ የሀገር ውስጥ ሕገወጥ ንግድ ድርሻ እንደያዘ ሲገለጽ፣ ትንባሆ የ45 በመቶ እንዲሁም የመድኃኒት ዘርፉ 30 በመቶ የሕገወጥ ንግድ የተስፋፋበት እንደሆነ ረዳት ፕሮፌሰሩ አቅርበዋል። በጥናቱ መሠረት የአምስት ዓመታት ዋጋው እንደተሰላ አብራርተው፣ እ.ኤ.አ. ከ2013 እስከ 2017/18 ባለው ጊዜ ውስጥ የ18 ቢሊዮን ብር ዋጋ ያለው ሕገወጥ የገቢ ንግድ እንደተመዘገበ ግምታዊ የጥናት ውጤቶች እንደሚያሳዩ ገልጸዋል። መንግሥት በበኩሉ በጨርቃ ጨርቅ ዘርፉ ብቻ የዘጠኝ ቢሊዮን ብር ገቢ ማጣቱን፣ እ.ኤ.አ. ከ2015 እስከ 2016 በነበረው ጊዜ ውስጥም ከ17 ሺህ በላይ የሥራ ዕድል መታጣቱ እንደሚገመት ረዳት ፕሮፌሰር ፈንታ አስታውቀዋል።

በኢትዮጵያ እየተስፋፋ ለመጣው የሕገወጥ ንግድ እንቅስቃሴ ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች አስተዋጽኦ አድርገዋል ያሉት ረዳት ፕሮፌሰሩ፣ በመደበኛውና በኢመደበኛው ንግድ መስክ የተሰማሩ ነጋዴዎች ትክክለኛውን ምርት ከተጭበረበረውና ሕገወጥ ከሆነው በመቀላቀል የሚፈጽሙት ማጭበርበር አንደኛው ለሕገወጥ ንግድ መስፋፋት መንስዔ እንደሆነ አብራርተዋል።

ከዚህ ባሻገር በደኅንነትና በፀጥታ ሠራተኞች ብሎም፣ በጉምሩክ ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ከለላ እየተሰጣቸው በወታደራዊ አጀብ ጭምር ታግዘው የሚገቡ የሕገወጥ ምርቶችም በሀገሪቱ እየተስፋፋ ለመጣው የሕገወጥ ንግድና እንቅስቃሴ ወቀሳ ከሚቀርብባቸው መካከል እንደሚመደቡ ተጠቅሷል። ይህ ሁሉ አሁንም ድረስ መሠረታዊ ችግር ሆኖ ከሚገኘው የሙስና ተግባር ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያን ከምንጊዜውም ይልቅ ተጋላጭ እያደረጋት እንደመጣ ረዳት ፕሮፌሰር ፈንታ ገልጸዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ እንደተናሩት፣ በሕገወጥ ንግድ አማካይነት ከኢትዮጵያ ወደ ጎረቤት ሀገሮች ከሚጓዙት ሸቀጦች ውስጥ ቡና፣ የቅባት እህሎች፣ የቁም እንስሳት፣ ወርቅ፣ ሳፋየርና ሌሎችም በገፍ እየወጡ ነው። በመሆኑም የድንበር ንግድን በሕጋዊ መንገድ ለማካሄድ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ስምምነት ማድረግ አንዱ መፍትሔ እንደሆነ፣ የንግድ ሸቀጦችን የሚያጓጉዙ ተሸከርካሪዎችን በዲጂታል መንገድ መከታተል የሚቻልበት የኤሌክትሮኒክ ሥርዓት መዘርጋት ከጠቀሷቸው ውስጥ ይገኙበታል።

ግሎባል ፋይናንሺያል ኢንተግሪቲ የተሰኘው ዓለም አቀፉ የፋይናንስ ግልጽነት ተቋም ከሚያወጣቸው መረጃዎች እንደሚታየው፣ እ.ኤ.አ. ከ2005 እስከ 2014 ባለው ጊዜ ውስጥ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ1.2 ቢሊዮን እስከ 1.5 ቢሊዮን ዶላር በሕገወጥ ንግድ ብሎም በተጭበረበረ የንግድ ሰነድ አማካይነት ወደ ውጭ ሲሸሽባት ቆይቷል። ይህ አኃዝ በአሁኑ ወቅት ከዚህም በላይ እየጨመረ እንደሚመጣ ይታመናል። የተጠቀሰው አኃዝ በየዓመቱ የኢኮኖሚዋን 2.2 በመቶ ድርሻ እንደሚይዝ ሲገለጽ፣ የዓለም ባንክና በተመድ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን በተለያየ ወቅት በተጭበረበሩ የንግድ ሥራዎች፣ ስምምነቶችና ሰነዶች በተለይም ገቢና ወጪን በማዛባት (ወጪን በማናርና ገቢን በማሳነስ) የሚፈጸሙ የንግድ ወንጀሎች እየተበራከቱ እንደመጡ በተለያየ ጊዜ ያወጧቸው ሪፖርቶች ይጠቁማሉ።

በኢትዮጵያ በተለያዩ መንገዶች የሚካሄዱ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ እየጎዳውና ችግሩም አሳሳቢ ደረጃ ላይ እየደረሰ መሆኑ በዚያ ሰሞን በተካሄደ ውይይት እንደገና ተገልጿል። ከሕገወጥ ንግድና ተያያዥ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ሰሞኑን በተካሄደ የውይይት መድረክ ላይ እንደተገለጸው የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሕገወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎች ሀገሪቱን ኢንዱስትሪ አልባ ወደ ማድረግ እያሸጋገረ መሆኑን ጭምር የሚያመለክት ነው። በውይይት መድረኩ ተናጋሪ ከነበሩ ባለሙያዎች መካከል አንዱ የሆኑት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የንግድ ግንኙነትና ስምምነት ዳይሬክተር አቶ ሙሴ ምንዳዬ ከገቢና ወጪ ንግድ ጋር የተያዘው ሕገወጥ ንግድ አሳሳቢ የሚባል መሆኑን ጠቁመዋል።

የችግሩን ግዝፈት ለማመልከት ምሳሌ ያደረጉት የቁም ከብት የወጪ ንግድን ነው። ሁለት ሚሊዮን የሚሆን የቀንድ ከብት በሕጋዊ መንገድ ኤክስፖርት ከተደረገ 20 ሚሊዮን የሚሆነው በሕገወጥ መንገድ እንደሚሄድ ጥናቶች የሚያመለክቱ መሆኑን ገልጸዋል። ከቀንድ ከብት ሌላ የጥራጥሬ ምርቶችም በሕገወጥ መንገድ ከሀገር እየወጡ ሲሆን፣ በገቢ ምርቶች ረገድም አብዛኞቹ የኢንዱስትሪ ምርቶች በሕገወጥ መንገድ ወደ ሀገር እንደሚገቡ፣ በዚህም ሳቢያ የሀገር ውስጥ አምራቾች እየተጎዱ እንደሆነ አቶ ሙሴ ጠቁመዋል።

በመሆኑም ችግሩ አሳሳቢና ፈጣን መፍትሔ የሚያሻው መሆኑን አስረድተዋል። በመድረኩ ሌላ ተናጋሪ የነበሩት የማክሮ ኢኮኖሚው ባለሙያው አቶ አሚን አብደላ በበኩላቸው ሕገወጥ ንግድ የተለያዩ መገለጫዎች ያሉት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀገሪቷ በሕገወጥ መንገድ በሚደረጉ ንግዶችና በገንዘብ ዝውውር ያጣችው የሀብት መጠን ከዓመት ዓመት እያደገ መምጣቱን ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ በአምስት ዓመታት ውስጥ ብቻ 70 ቢሊዮን ዶላር በደረሰኝ ማጭበርበር እንደምታጣ ጥናቶች ያመላክታሉ ያሉት አቶ አሚን ይህም ከገቢና ወጪ ንግድ ሒደት ጋር ተያይዞ ዋጋን አሳንሶና ከፍ አድርጎ በማቅረብ በሚፈጸም ማጭበርበርና ገንዘብን በሕገወጥ መንገድ ከሀገር በማሸሽ (በካፒታል ፍላይት) የሚታጣ እንደሆነ አመልክተዋል። ይህ ብቻ ሳይሆን የሳይበር (የበይነመረብ) ግብይትን በመጠቀም መንግሥት የማያውቃቸው ንግዶች እየተካሄዱ መሆኑን የተናገሩት የማክሮ ኢኮኖሚ ባለሙያው፣ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ተደማምረው በአሁኑ ወቅት የሕገወጥ ንግዱ በሕጋዊ መንገድ ከሚካሄደው እየበለጠ መሄዱን ጠቁመዋል።

በተለይ በኮንትሮባንድ የሚገባውና የሚወጣው ብዛት ያለው ሲሆን በአንፃሩ ተያዘ የሚባለው ግን አነስተኛ መሆኑንም አስረድተዋል። የኮንትሮባንድ ንግድን የሚመለከት ጥናት ለማድረግ በተንቀሳቀሱበት ወቅት ቁጥጥሩ ጥቃቅን ጉዳዮች ላይ እንደሚያተኩር፣ ሦስት አራት ሻሚዝ ደርበው ለማለፍ በሚሞክሩት ላይ የሚበረታ መሆኑን እንዳስተዋሉ ተናግረዋል። በኮንቴነር የሚተላለፈውን ዋናውን የኮንትሮባንድ ንግድ ትኩረት እንዳላገኘና የኮንትሮባንድ ቁጥጥር ሥራው ችግር ያለበት መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የአፍሪካ ነፃ የንግድ ቀጣናና ኮሜሳ ውስጥ ብትገባ የሀገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ይጎዳሉ የሚል ሥጋት እንደነበራቸው መለስ ብለው ያስታወሱት አቶ አሚን፣ አሁን ግን ኢትዮጵያን ኢንዱስትሪ አልባ ሊያደርጋት የሚችለው ትልቁ ሥጋት ኮንትሮባንድ እንደሆነ በመግለጽ የችግሩን አሳሳቢነት አመላክተዋል። የኢትዮጵያ ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪዎች ከውጭ በሚገቡ ተመሳሳይ ምርቶች ጋር መወዳደር አቅቷቸው እየተዘጉ መሆኑን ያስረዱት አቶ አሚን ኮንትሮባንድ በሁሉም ዘርፍ እየተስፋፋ መሄዱ በግልጽ እየታየ እንደሆነ ተናግረዋል።

ኮንትሮባንድ ከኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችና ከመሳሰሉት አልፎ ወሳኝ የሚባሉ መድኃኒቶች ሳይቀር በኮንትሮባንድ እየገቡ መሆኑ ችግሩን ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ሁለንተናዊ እያደረገው እንደሆነ፣ ጉዳቱም ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ወደ ማዳረስ እየተሸጋገረ መሆኑን አመልክተዋል። አሁን ላይ በሕጋዊ መንገድ ከሚላከው የወጪ ንግድ ምርት ይልቅ በተለይ በአንዳንድ ዘርፍ ላይ በሕገወጥ መንገድ የሚገባው እየባሰ መምጣቱ ትልቅ ችግር መሆኑን የገለጹት አቶ አሚን፣ ይህም ሰዎች ሕጋዊ ሥነ ሥርዓትን ከመከተል ወደ ሕገወጥነት እያመዘኑ መሆኑን እንደሚያሳይ ገልጸዋል።

በተለያዩ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆኖ የሚያመርተው የሀገር ውስጥ አምራች በኮንትሮባንድ በሚገባውና በተሻለ ጥራትና በዝቅተኛ ዋጋ መሀል ከተማ ላይ እየተሸጠ በሚገኘው ምርት እየተንኮታኮተ መሆኑንም ጠቅሰዋል። የሀገር ውስጥ አምራች ጉዳት ውስጥ እየወደቀ ከሆነ በሀገራዊ ኢኮኖሚው ላይም እያረፈ ያለው ተፅዕኖ ቀላል አይደለም ማለት እንደሆነ፣ በዚህ ሒደት መንግሥት ከፍተኛ የሚባል የታክስ ገቢ እያጣ መሆኑን ባለሙያው በማብራሪያቸው አመልክተዋል።

የሕገወጥ መንገድ እንቅስቃሴ ሌላው መገለጫ ገንዘብ ከሀገር ማሸሽ (ካፒታል ፍላይት) እንደሆነ የጠቀሱት አቶ አሚን የኢትዮጵያ ካፒታል ፍላይት ከአፍሪካ ከፍተኛው የሚባል ደረጃ ላይ መድረሱንም ጠቁመዋል። ለዚህም በባንክና በጥቁር ገበያው መካከል ያለው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ልዩነት አንዱ ማሳያ መሆኑን ተናግረዋል። ሌላው ለሕገወጥ ንግድ መስፋፋት በዕቃዎች ላይ የሚጣሉ ከፍተኛ የታሪፍ ጫናዎች እንደሆኑ የተናገሩት አቶ ዮሐንስ፣ ይህ ጫና ሕገወጥና ኢሞራላዊ ነጋዴዎችን ወደ ኮንትሮባንድ ንግድ እንዲገቡ የሚገፉቸው መሆኑን ገልጸዋል።

አቶ ሙሴ በበኩላቸው ለሕገወጥ ንግድ መስፋፋት በዋነኝነት የሚጠቀሰው በድንበሮች አካባቢ ያለው የማኔጅመንት ችግር እንደሆነ ይገልጻሉ። ‹‹እውነት ለመናገር በጣም በሙስና የተዘፈቀ የጠረፍ አካባቢ አስተዳደር ነው ያለን። ይህ ትልቅ ችግር ነው፤›› በማለት ይህንን መፍታት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሻሎም ! አሜን።

# ወቅታዊ

# ‹‹ድርቅን በዘላቂነት ለመከላከል የአርብቶአደሩን አደጋ የመቋቋም አቅም ማሳደግ ይጠይቃል››

**ዶክተር እንድሪያስ ጌታ**
**የመስኖና ቆላማ ሚኒስትር ዴኤታ**



ፎቶ፦ ገባቦ ገብሬ

ማህሌት አብዱል

**ኢትዮጵያ ከ60 በመቶ በላይ የሚሆነው መሬቷ ቆላማና እርጥበት አጠር ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በተደጋጋሚ ለድርቅ አደጋ ተጋላጭ ናት። በአንፃሩ ደግሞ ሰፊ የከርሰ ምድርና ገፀ ምድር ውሃ ሀብት ያለው በዚሁ አካባቢ ነው። ይሁንና ያለውን የውሃ ሀብት በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል ባለመቻሉና በቂ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ሥራ ባለመከናወኑ ኑሮውን እንስሳት እርባታ ላይ ያደረገው አርብቶአደር ተከታታይነት ባለው ድርቅ የመጋለጥ አደጋ ተጋርጦበታል።**

**ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግሥት በአካባቢው ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብት አቅም ጥቅም ላይ በማዋል የአርብቶአደሩን የአደጋ ስጋት ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችሉ በርካታ ፕሮጀክቶችን ቀርፃ እየሠራ ይገኛል። ከእነዚህም መካከል የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት እንዲሁም የመኖ ልማት ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም የእንስሳትን ጤና የሚያስጠብቁ የጤና ማዕከላትን ከመገንባት ባለፈ የጤና ባለሙያዎችን በስፋት በማሠልጠንና ግብዓቶችን ተደራሽ ለማድረግ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታች የሚባል ነው።**

**ከዚህ በተጓዳኝም ከምትዋሰናቸው ጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን ዲፕሎማሲ ግንኙነት በማጠናከር የእንስሳት ግብይቱን የማዘመን፤ የግብይት ማዕከላትን የመገንባትና ሕገወጥ ንግድን ለመከላከል የተጀመሩት ሥራዎችም ይበል የሚያሰኙ ናቸው።**

**በአጠቃላይ የመስኖና ቆላማ ሚኒስቴር የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል እያከናወናቸው ባሉ ተግባራትና ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶአደሮችን በሚያሳትፈው 19ኛው የአርብቶአደሮች በዓል ዙሪያ ከመስኖና ቆላማ ሚኒስትር ዴኤታ ከዶክተር እንድሪያስ ጌታ ጋር ያደረግነው ቃለምልልስ እንደሚከተለው ይቀርባል።**

**አዲስ ዘመን፡- የመስኖና ቆላማ ሚኒስቴር ከተቋቋመበት ዓላማ አንፃር ምን ያህል ተልዕኮውን አሳክቷል ተብሎ ይታመናል?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** እንደሚታወቀው የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር በ2014 ዓ.ም በአስፈፃሚ አካላት መልሶ ለማደራጀት በወጣው አዋጅ መሠረት ነው በአዲስ መልክ የተደራጀው። ተቋሙ ቀደም ሲል በውሃ፤ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር ስር በነበረው የመስኖ ልማት ኮሚሽን የጀመራቸውን ሥራዎች እንደዚሁም ደግሞ በሰላም ሚኒስቴር የአርብቶአደር ዳይሬክቶሬት ስር ይሠሩ የነበሩ ሥራዎችን በማሰባሰብ በአዋጅ የተሰጡንን ኃላፊነቶችን በሚገባ በመተንተን፤ በአዲስ መልክ መዋቅሩን አዘጋጅቶ የሰው ኃይሉን አሟልቶ ወደ ሥራ ገብቷል።

ሚኒስቴሩ በመስኖ ፕሮጀክቶች ልማት እና ቆላማ አካባቢ ምርምርና ልማት በተባሉ ሁለት ዘርፎች ነው የተደራጀው። እነዚህ ዘርፎች በቅንጅት የአርብቶአደሩንና የቆላማ አካባቢውን ልማት ለማሳደግ የሚያስችሉ ሥራዎች እየሠሩ ይገኛሉ። አብዛኛው ሰፊና ሊታረስ የሚችል መሬት ያለው በቆላማ አካባቢ ትልቅ የከርሰ-ምድርና ገፀ-ምድር የውሃ ሀብት ያለበት በመሆኑ ይህንን የውሃ ሀብት ለመስኖ በማዋል፤ ለላቀ ኢኮኖሚያዊ እድገት አስተዋፅኦ ሊውል በሚችል ሁኔታ ውሃን ማዕከል ያደረገ የልማት ሥራ እንዲሰራ ጥረት አድርጓል።

በዋናነትም ቆላማ አካባቢዎች ያላቸውን እምቅ የተፈጥሮ ሀብቶችን፤ የቆዩ ሀገር በቀል እውቀቶችን ተጨባጭ በማድረግ የአስር ዓመት የልማት እቅድ መነሻ በማድረግ የሦስት ዓመት እቅድ አዘጋጅተን ወደ ሥራ ገብተናል። ይህንን እቅድ መሠረት በማድረግ በቆላማው አካባቢ ሰፋፊ የሆኑ የመስኖ ልማት ጥናትና ዲዛይን ሥራዎች ተሠርተዋል። ከእነዚህም መካከል ገናሌ 58 ሺ ሄክታር መሬት ሊያለማ የሚችል ጥናትና ዲዛይን ተጠቃሽ ነው። እንዲሁም ዋቢ ሸበሌ 27 ሺ ሄክታር ሊያለማ የሚችል ፕሮጀክት ከዚህ በፊት ተጀምሮ በተለያየ ምክንያት ጥቅም ሳይሰጥ ረጅም ጊዜ ቆይቷል። ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ውጤት እየታየበት ነው። በአዋሽ ተፋሰስም እንደዚሁ የአዋሽ ወንዝ ላይ የነበረ ሰፊ የእርሻ ልማት ‘ፕሮሶፊስ’ በተባለ መጤ እፅዋት ምክንያት ከጥቀም ውጪ የነበሩትን የመስኖ መሠረተ ልማቶች በመጠገንና በማስተካከል ሰፊ የእርሻ መሬት ወደ ልማት መግባት የሚያስችል ሁኔታ ተፈጥሯል።

በተጨማሪም አነስተኛና መካከለኛ መስኖ ልማት ሥራዎች ላይ ክልሎችን በማገዝ ጥሩ ውጤቶች እየታየ ነው። በዚህም በሀገራችን የነበረውን የመስኖ መሠረተ ልማት ሽፋን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ተችሏል። ከዚህ በፊት እንደሚታወቀው በአብዛኛው በዝናብ ላይ የተመሠረተ ግብርና የምንከተል በመሆኑ ምርታማነታችን ከእጅ ወደአፍ በሚባል ደረጃ ነበር። በአሁኑ ወቅት ይህንን አሠራር ለማሻሻል ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። በዚህ ረገድ በተለይም የበጋ ስንዴ ልማት ጋር በተያያዘ ሰፊውን መሬት ለማልማት ጥረት ተደርጎ ከፍተኛ የሆነ ለውጥ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል በቆላማ አካባቢዎች የሚኖረው ማኅበረሰብ የኑሮ መሠረት በእንስሳት እርባታ ላይ በመሆኑ የእንስሳት ምርታማነት ሊያሻሽሉ በሚችሉ የተለያዩ ሥራዎችን ለመሥራት ትኩረት ተደርጓል። ክልሎች፤ በየደረጃው ያሉ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር የተጀመሩ ሥራዎች ውጤት እያስገኙ ነው። በዋናነትም የኢትዮጵያ አርብቶአደሮች ካውንስል እንዲደራጅ በማድረግ፤ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በሙሉ የአርብቶአደር የልማት ክፍቶችን በመለየት የእቅዶቻቸው አካል አድርገው ክትትልና ድጋፍ ተደርጎ ሥራዎች እንዲሠሩ ጥረቶች ተደርገዋል።

**አዲስ ዘመን፡- የእንስሳት ሀብት ምርታማነት ለማሻሻል ስለተሠሩት ሥራዎች ቢያብራሩልን?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** የእንስሳት ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የመጀመሪያው ሥራ የእንስሳት ውሃ አቅርቦትን ማሳደግ ነው። ምክንያቱም ትልቁ ችግር ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘም የአርብቶ አደር አካባቢ በተደጋጋሚ ድርቅ ይከሰታል። ድርቅ ደግሞ የመኖ አለኝታ እንዲመናመንና የእንስሳት እልቂት እንዲከሰት ያደርጋል፤ የኅብረተሰቡ አጠቃላይ የኑሮ መሠረት እንዲናጋም ምክንያት ይሆናል። በዚህ ረገድ በእነዚህ ዓመታት በሕይወት ላይ አደጋ እንዳይደርስ መንግሥትና ኅብረተሰቡ ርብርብ አድርገዋል። የአርብቶ አደሩን የኑሮ ዘይቤ መሠረት ያደረጉ ሥራዎች ተሠርተዋል፤ በቀጣይም ከችግር መውጣት የሚችልበትን አቅም ማጎልበትን መሠረት ያደረገ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ የእንስሳት ሀብት ልማትን ለማሻሻል አንደኛ የውሃ አቅርቦትን ከፍ ማድረግ ይገባል።

ለኅብረተሰቡ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ከማቅረብ አኳያም በርካታ ፕሮጀክቶች ተነድፈው ወደ ሥራ ተገብቷል። በተለይም የከርሰ ምድር ውሃ ባለባቸው አካባቢዎች ለሕዝቡ ተደራሽ ለማድረግ ተሞክሯል። በተጨማሪም ከዚህ በፊት የነበሩ የውሃ ተቋማትን ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ተደርገዋል። ዝናብ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ደግሞ ዝናብ በኩሬ መልክ አቆይቶ ጥቅም ላይ የሚውልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የወንዞች አቅጣጫን በመቀየስ (በመጥለፍ) የመስኖ ልማት ተሠርቷል። በእርግጥ ከችግሩ ስፋት አኳያ የተሠራው ሥራ ገና ቢሆንም ጥሩና ተስፋ ሰጪ የሆኑ ውጤቶች እየተገኙ መሆኑን ማንሳት ይቻላል።

ሌላው የእንስሳት ሀብት ልማት ለማሻሻል የተፈጥሮ ግጦሽ፤ አያያዝና አስተዳደር የመኖ ልማት ሥራ ነው። እነዚህ የግጦሽ ቦታዎች ከአየር ንብረት ተፅዕኖም ሆነ ከእፅዋት ዝርያም ጋር በተያያዘ ምርታማነታቸው እጅግ እየቀነሰ ስለሆነ የተጎሳቆሉ አካባቢዎችን ከልሎ እንዲለሙ የማድረግ፤ መጤ የዕፅዋት ዝርያን የማስወገድ የመመንጠር ሥራ ሲካሄድ ቆይቷል። ምርታማና በአጭር ጊዜ የሚደርሱ ዝርያዎችን ዘር አቅርቦ ሕዝቡ እንዲያለማ የማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መኖን በትርፍ አምጥቶ እንዲሁ እንዲባክን መፍቀድ ሳይሆን ለክፉ ጊዜም ማቆየት የሚችሉበትን ባንኮች በየአካባቢው እንዲገነቡ እየተደረገ ነው። በተጨማሪም ለገበያ አውጥቶ ኅብረተሰቡ ገንዘብ ማግኘት እንዲችል ሥራዎች ተሠርተዋል። በዚህም የጋራ ፍላጎት ያላቸው መኖ አምራች አርብቶአደሮች በአፋር፤ በደቡብ፤ በኦሮሚያ በሱማሌ ክልሎች ተደራጅተው ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል።

በተመሳሳይ የተፈጥሮ ግጦሽን የማስተዳደር ሥራውን የማሻሻል፤ የአካባቢ ጥበቃውን የማጠናከርና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች የማጎልበት ሥራዎች አበረታች የሚባሉ ናቸው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ኅብረተሰቡን በየክላስተሩ አደራጅቶ በልማቱ ተሳታፊ የማድረጉ ሥራም ጥሩ ውጤት እየተገኘበት ነው። ለአብነት ያህልም በአፋር፣ በሱማሌ፣ በቦረና፤ በደቡብ ክልሎች መኖ ልማት ላይ የተሰማሩ አርብቶአደሮች ከፍተኛ ውጤት ማግኘት መቻላቸው ተጠቃሽ ነው። ይህም መኖ አለኝታን በማረጋገጥ የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነትን በማሻሻል የሚደረገውን ጥረት ያግዛል።

ከዚህ ባሻገርም የእንስሳት ሀብት ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል ከግብርና ሚኒስቴርም ጋር በቅንጅት እየተሠራ ያለው የእንስሳት ጤና አገልግሎትን የማሻሻል ሥራ ነው። እንግዲህ አርብቶአደሩ የኑሮ መሠረቱ እንስሳት እንደመሆኑ የእንስሳት ጤናን ለማስጠበቅ ክሊኒኮችን በየአካባቢው ተደራሽ እንዲሆኑ፤ የሕክምና ቁሳቁሶች እንዲሟሉ፤ የማኅበረሰብ ጤና አገልግሎት ሠራተኞችን አሰልጥኖ ከኅብረተሰቡ የኑሮ ዘይቤ ጋር ተንቀሳቅሰው የሕክምና አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረግ ሥራ በብዙ ቦታዎች ውጤት ተገኝቷል። በተጨማሪም በቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ተቀርፀው እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ።

በተጨማሪም የኅብረተሰቡን የኑሮ መሠረት ማስፋት ያስፈልጋል የሚል እምነት ተይዞ እየተሠራ ያለ ሥራ አለ። እንደሚታወቀው የአርብቶአደሩ ኑሮ በእንስሳት እርባታ ላይ ብቻ የተመሠረተ እንደመሆኑ በተለያዩ አደጋዎች ምክንያት ለከፋ ችግር የሚጋለጡበትን ሁኔታ ለመቀነስ የተለያዩ የገቢ አማራጮችን ማስፋት ያስፈልጋል በሚል የተለያዩ ሥራዎች ተጀምረዋል። በመሆኑም የጋራ ፍላጎት ያላቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማደራጀት በተለያዩ የሥራ መስኮች እንዲሰማሩና ተጨማሪ የገቢ አማራጮችን እንዲያገኙ ለማድረግ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በተጓዳኝ ሰብል፤ አትክልትና ፍራፍሬ ልማት ተደራጅተው እንዲሰማሩ ድጋፍ ተድርጎላቸዋል። በዚህም ጥሩ የሚባል ውጤት ተገኝቷል።

ከዚህም ባሻገር እንደየዝንባሌያቸው በአነስተኛ የሥራ መስክ መሰማራት እንዲችሉ የቢዝነስ ፕላን ተዘጋጅቶ፤ የፋይናንስ አቅርቦት ተመቻችቶላቸው፤ በድጋፍ መልክ ተሰጥቶቸው ወደ ሥራ የገቡ አሉ። ለአብነት በእጣንና ሙጫ፣ በእንስሳት ማድለብ፣ በንብ ማነብ፣ በወተት ግብይት ሰንሰለትም የተሰማሩትን መጥቀስ ይቻላል። በተለይ ለወጣቶች ተደራጅተው የሥራ ዕድል እንዲፈጠር ተሞክሯል። ባለፈው ዓመትም ከ50ሺ በላይ የሚሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች በአነስተኛ የሥራ መስክ እንዲገቡ ተደርጓል። አሁንም አማራጭ የገቢ ምንጮችን ለማስፋት፤ የፋይናንስ ተደራሽነት እንዲረጋገጥ ለማድረግ ከፍ ባለ ደረጃ እየተሠራ ነው።

ለምሳሌ አርብቶአደሩ እንስሳቱን አሲይዞ ከፋይናንስ ተቋማት ብድር ማግኘት እንዲችል ድጋፎች እየተደረጉ ነው። ለዚህም ይረዳ ዘንድ ብሔራዊ ባንክ አካታች የፋይናንስ ሥርዓት መመሪያ አውጥቷል። ይህም የአርብቶአደሩን ኑሮ ለማሻሻል ከፍተኛ አቅም ይሆናል ተብሎ ይታመናል።

በነገራችን ላይ፤ የቆላማና አርብቶ አደር አካባቢ የሀገራችንን 60 በመቶ ያህል የቆዳ ሽፋን የሚይዝ፤ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ማኅበረሰብ የሚኖሩበት በመሆኑ መሠረተ ልማቶችን ተደራሽ ማድረግ በእጅጉ ያስፈልጋል። በተለይ የመንገድ፣ የውሃ፣ የትምህርትና ጤና ተቋማት ተደራሽነት ከማረጋገጥ አኳያ የኅብረተሰቡን ኑሮ መሠረት ያደረገ ምቹ ለማድረግ በአርብቶአደር ካውንስል አማካኝነት በጋራ ሥራ እየተሠራ ነው። በአጠቃላይ ግን የአርብቶአደር አካባቢ የልማት ክፍተቶች ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ እንዲሟሉ ለማድረግ በቅንጅት ሥራዎች እየተሠሩ ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ከዚህ አንጻር በቆላማና አርብቶአደር አካባቢ ያለውን ሰፊ የውሃ ሀብት ጥቅም ላይ ከማዋል አኳያ የተሠራው ሥራ አመርቂ ነው ማለት ይቻላል?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** እንደተባለው የከርሰ-ምድርና የገፀ-ምድር ውሃ ሀብት በአካባቢው በስፋት ይገኛል። በተጨማሪም ከደጋማ አካባቢዎች የሚዘንበው ዝናብ ተጠራቅሞ ወደ ቆላማ አካባቢዎች ነው የሚፈስሰው። ይሁንና በእነዚህ አካባቢዎች ሰፊ ሀብት ቢኖርም ሀገሪቱ በሚፈለገው መጠን አልተጠቀመችም። ሰፊ የሆነ ማልማት የሚቻል መሬት አለ። የሕዝቡ የአሰፋፈር ሁኔታ ከጤና

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ከገጽ 7 የዞረ

# ‹‹ድርቅን በዘላቂነት ለመከላከል የአርብቶአደሩን...

አገልግሎትም፤ ከአየር ንብረትም ጋር በተያያዘ በአብዛኛው ወደ ደጋው አካባቢ የሚያመዝነው። ስለዚህ ቆላማ አካባቢ ያለው ቦታ ሰፊና ያልተነካ ነው። ከደጋማ አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር በጣም ለም የሆነ፤ ብዙ ምርት ማምረት የሚቻልበት፤ ለኢኮኖሚው ትልቅ ተስፋ የሆነ አካባቢ ነው። ስለዚህ ይህንን አካባቢ ማልማት ትልቅ የእድገት አማራጭ አድርጎ መውሰድ ያስፈልጋል። በእነዚህ አካባቢዎች ያለውን የውሃ ሀብት አልምቶ ለመስኖ፣ ለእንስሳት፣ ለሰብልና ለመኖ ልማት ማዋል ይገባል።

በዚህ ረገድ እስካሁን የተሠሩት ጅምር ሥራዎች ናቸው። የጥናትና ዲዛይን ሥራዎች እየተሠሩ ሲሆን ለምሳሌ ገናሌ ትልቅ ወንዝ ነው፤ አቋርጦ የሚሄድበት አካባቢ ሰፊ ነው፤ ይህንን አጥንቶና ኢንቨስት አድርጎ የሀገሪቱን የመስኖ ልማት መገንባት በጣም ከፍተኛ የሆነ አቅም ይጠይቃል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ስለተቋቋመ ብቻ በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚሠራ አይደለም፤ ሂደትን የሚጠይቅ ነው። አሁንም ቢሆን በርካታ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች እየተሠሩ ሲሆን ብዙዎቹ የሚዘገዩት ደግሞ ከሀገራችን የመፈፀም አቅም ጋር በተያያዘ በሚፈጠር ችግር ነው።

ይህም ሲባል የኮንትራክተሮችና የአማካሪዎች አቅም፤ የአጠቃላይ የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪያችን ገና ያላደገ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተጀመሩ ሥራዎች በፍጥነት የመጨረስ ችግሮች በመኖራቸው ነው። ሆኖም የነበሩና የተበላሹ መሠረተ ልማቶችን ጠግኖ ወደ ሥራ እንዲገባ የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው። ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል አልዌሮ ግድብ ወደ 12 ሺ ሄክታር ማልማት የሚችል ቢሆንም እስካሁን አገልግሎት ሳይሰጥ ነው የቆየው። በመሆኑም በአሁኑ ወቅት ይህንን በፕሮጀክት ይዘን ቶሎ መሠረተ ልማቱን ተሟልቶ አካባቢውን ማልማት የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

በተመሳሳይ በጎዴ አካባቢ ዋቢ ሸበሌ ወንዝን መሠረት በማድረግ 27ሺ ሄክታር ማልማት የሚችል ሰፊ አቅም አለ። ይህንን ጥቅም ላይ ለማዋል በፕሮጀክት ተደግፎ ወደ ሥራ ተገብቶ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ወደ አምስት ሺ ሄክታር መሬት ወደ ልማት ገብቷል። እንደዚህ ዓይነት ሥራዎች ውሃን ጥቅም ላይ ለማዋል የሚደረጉ ጥረቶች አሉ። በገናሌ ወንዝ ላይ 58ሺ ማልማት የሚችል የጥናትና የዲዛይን ሥራ ኮንትራት ተሰጥቶ ሥራዎች በመከናወን ላይ ናቸው። የአዋሽ ተፋሰስን ተከትሎ ተጨማሪ የመስኖ ልማት ሥራዎች እየተሠሩ ነው። በኦሮሚያም የከርሰ-ምድር ውሃ አውጥቶ ለንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦትም፤ ለመስኖም መጠቀም የሚችሉበት ሁኔታ ለመፍጠር የተጀመረ ሥራ አለ።

በሌላ በኩል ተፋሰስን ተከትሎ የኦሞ ኩራዝ ስኳር ልማት ፕሮጀክት ተጀምሮ ረጅም ርቀት ሳይሄድ ተስተጓጉሎ መቅረቱ ይታወሳል። ይህ በጣም ሰፊ ቦታ ማልማት የሚችል የመስኖ አውታር ወደ ልማት ለማስገባት የአዲስ ኮንትራት ውል ተፈራርመን ሥራ እየተሠራ ነው። ኦሞ ላይ ደግሞ ወደ 200ሺ ሄክታር ማልማት የሚችል አቅም አግኝተናል። በተጨማሪም የቆላማ አካባቢ በክልሎች አቅም የሚሠሩ አነስተኛና መካከለኛ ፕሮጀክቶችን የመደገፍ፤ የማስተባበር ሥራ እየሠራን ነው። በጥቅሉ ውጤት በአንድ ጊዜ አይመጣም፤ ግን ደግሞ ደረጃ በደረጃ ለመለወጥ እየተሠራ ነው። መካድ የማይቻለው ግን የአቅም ውስንነት መኖሩን ነው። እነዚህ ፕሮጀክቶች በመንግሥት በጀት የሚከናወኑ በመሆኑ በአንድ ጊዜ ለሁሉም ፋይናንስ ማድረግ አይቻልም። በደረጃ በደረጃ እየተጠናቀቀ ሲመጣ ብዙ ለውጥ ይታያል የሚል እምነት ነው ያለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ የመስኖ ፕሮጀክቶች ይገነባሉ ተብለው ሳይገነቡ የቆዩ፤ ሌሎች ደግሞ ተገንብተው አገልግሎት ሲሰጡ አይታዩም፤ ከሚጠበቀው በታች እያሰሙ ያሉ እንዳሉ ይታወቃል። ለምሳሌ የርብ ግድብንና አፋር አካባቢ ያሉ ፕሮጀክቶችን መጥቀስ ይቻላል። ይህ የሆነበትን ምክንያት ቢያስረዱን?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** በእርግጥ የመስኖ ፕሮጀክቶችን የሚመራ ሌላ ዘርፍ ቢኖርም እንደተቋም ግን በተወሰኑት ላይ ምላሽ ልስጥ። እነዚህ የመስኖ ፕሮጀክቶች ሚኒስቴሩ ከተቋቋመ በኋላ አዲስ የተጀመሩ አይደሉም። አዲስ ያስጀመርናቸው በጣም ጥቂት ናቸው፤ ከዚያ በላይ በስፋት የሠራነው ጥናትና ዲዛይን ነው። እንደተባለው ፕሮጀክቶቹ ተጀምረው በተለያዩ ችግሮች የሚቋረጡበት ሁኔታ አለ። ብዙ ጊዜ በቂ ጥናትና ዲዛይንም ሳይደረግ በፖለቲካ ውሳኔ ብቻ ተጀምረው የቆሙ፤ መሠረተ ድንጋይ ተቀምጦላቸው ወደ ሥራ ያልገቡ፤ ብዙ ውስብስብ ችግሮች ውስጥ የገቡ ናቸው። ለአብነት መገጭን ማንሳት ይቻላል፤ በሌሎች አካባቢ ያሉ ፕሮጀክቶችም ተመሳሳይ ችግር ውስጥ ገብተው ተደነቃቅፈው የቀሩ ናቸው። በመጀመሪያ ደረጃ የእነዚህን ፕሮክቶች ችግር ማወቅ ያስፈልጋል።

በሀገሪቱ ከፍተኛ አቅም አላቸው የተባሉ ባለሙያዎች ቀጥረን ችግሮችን እንዲለዩ የማድረግ፤ አንዳንዶቹም በአዲስ መልክ የዲዛይን ማሻሻያ የሚደረግላቸው ሲሆኑ ሌሎቹ ከመቆየታቸው ጋር ተያይዞ በአዲስ የዋጋና የጊዜ ለውጥ ያስከተሉ በመሆኑ እነዚህ ችግሮችን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው። ግን ኅብረተሰቡ እነዚህ ፕሮጀክቶች አልቀው ልማት ካልዋሉ እርካታ ሊኖር አይችልም። ከዚህ አንፃር ለምሳሌ ኦሮሚያንና ሲዳማን የሚያዋስነው ጊዳቦ ግድብ ፕሮጀክት ሳይጠናቀቅ በ2010 ዓ.ም መመረቁ ይታወሳል። ሲመረቅ ግን ውሃ ብቻ ተገደበ እንጂ የመስኖ ልማት ሥራ አልተሠራለትም ነበር። በዚህም ምክንያት ኅብረተሰቡ ተጠቃሚ ሳይሆን ቆይቷል። አሁን ግን ያሉት ችግሮች ተለይተው ወደ ሥራ ተገብቷል ፤ የቀሩት ሥራዎች ወደ መጠናቀቁ ነው ያሉት።

**አዲስ ዘመን፡- በኦሮሚያ፣ ሱማሌና ሌሎች አካባቢዎች ጭምር በተከታታይ የሚከሰተው ድርቅ የሚያስከትለውን ችግር ለመቋቋም በመስኖ ልማት ላይ መሥራት እንደሚገባ ቢታመንም ባለፈው ዓመት በቦረና፤ በደቡብ ክልልና በሱማሌ ክልሎች ድርቅ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል። ዘንድሮ ደግሞ በአማራ እና ትግራይ ክልሎች ድርቅ ተከስቷል። ይህንን ችግር በዘላቂነት መፍታት ለምን አልተቻለም?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** የድርቁ መንስኤ የአየር ንብረት ለውጥ እንደሆነ ይታወቃል። ይህም ዓለም አቀፍ ክስተት ነው። ይሁንና ከዚህ በፊትም ቢሆን እነዚህ አካባቢዎች እርጥበት አጠርና የሚያገኙትም ዝናብ ዝቅተኛ ነው። እንደተባለው ቀደም ባሉት ጊዜያት የድርቅ ክስተቱ አሁን እንደሚታየው በተደጋጋሚና በአጭር ጊዜ ልዩነት የሚከሰት አልነበረም። አሁን ላይ በየዓመቱ የሚከሰትበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። እነዚህ ቆላማ አካባቢዎች ድርቅ ብቻ ሳይሆን ለጎርፍ ተጋላጭ ናቸው። ባለፈው ዓመት ብቻ በአፋር፣ በሱማሌና በጋምቤላ ክልል የተከሰተው ጎርፍ አስከፊ ጉዳቶችን አምጥቷል።

እንደአጠቃላይ ግን ድርቅም ሆነ ጎርፍ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖ መሆናቸው እሙን ነው። በመሆኑም እንደሀገር ይህንን መከላከል የሚቻልበትን አቅም መፍጠር ያስፈልጋል። ይህንን መፍጠር የሚቻለው ደግሞ በዘላቂ ልማት ማምጣት ሲቻል ነው። በዚህ ረገድም የድርቅ አደጋ ስጋቶችን በየጊዜው እየተከታተለ የሚገመግም፤ በርካታ ባለድርሻ አካላትን ያቀፈ፤ ክልሎችንም ጭምር የያዘ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራ ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ምክር ቤት በመንግሥት መቋቋሙ ይታወሳል። ምክር ቤቱ ገምግሞ ከሚያስቀምጣቸው አቅጣጫዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ ነው።

ድርቁ የተፈጥሮ ክስተት ስለሆነ አስቀድሞ ድርቅ ሲከሰት የምናውቅበት አቅም ሊኖር ይገባል። ተከስቶ ከተገኘም ቶሎ ከችግር መውጣት የሚቻልበት የኅብረተሰቡ የኑሮ መሠረት መስፋት አለበት። በዋናነት የውሃ መሠረተ-ልማትን በተለይ መስኖ በስፋት ተደራሽ ማድረግ፤ ሕዝቡ መኖንም ከሁለት ጊዜ በላይ ማምረት የሚችልበት፤ ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን በማስፋት የግሉም ዘርፍ ማሳተፍ ይገባል። ለዚህም ሦስትና ከዚያ በላይ ዓመታትን የሚወሰድ የጥናትና ዲዛይን ሥራ መሥራት ያስፈልጋል። የአዋጭነት ጥናቶች የሚፈልግ በመሆኑ ጊዜ የሚወስድ ነው። ዘላቂ የልማት ግቦችን አስቀምጠን መሥራት ይጠይቃል። በተጨማሪም ድርቅን በዘላቂነት መከላከል የአርብቶአደሩን አደጋ የመቋቋም አቅም ማሳደግ ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ 2017ዓ.ም የሚጠናቀቅ የቆላማ አካባቢዎች የኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ድርቅና ጎርፍን ታሳቢ አድርጎ ነው የተጀመረው። ይህንን ለማሳካት የአደጋ ስጋት ኮሚሽን፤ ብሔራዊ ሜትሮሎጂ አገልግሎት ጋር ተናቦ ለመሥራት ጥረት እየተደረገ ነው። ምክንያቱም ድርቅ ከተከሰተ በኋላ መሮጥ አይጠቅምም፤ የዕለት ደራሽ እርዳታ ማድረግ ብቻ ትርጉም ለውጥ ሊያመጣ አይችልም። በእርግጥ የሰው ሕይወት ለማዳን ጠቃሚ ነው። ግን አስቀድሞ ለመከላከል መዘጋጀት ላይ ነው ትኩረት ማድረግ የሚገባው። በዚህ ረገድ በቅንጅት የተጀመሩ ሥራዎች እየተሠሩ ያሉት ሥራዎች አበረታች ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- የአርብቶአደሩ ሕይወት የተመሠረተው በአብዛኛው የከብት እርባታ ላይ እንደመሆኑ ከብቶቹን የሚያረባበትን መንገድ ከማዘመን አኳያ ምን እየተሠራ ነው?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** እንደተባለው የአርብቶአደሩ የኑሮ መሠረት በእንስሳት ላይ የተመሠረተ ነው። እንስሳቱ አብዛኞቹ ለዚህ አካበቢ የሚሆኑ ድርቅን ፤ የመኖና የውሃ እጥረትንም ተቋቁመው መቆየት የሚችሉ እንዲሆኑ ነው የሚፈለገው። አሁን ከሚከሰተው ድርቅ አኳያ ብዙ ጉዳት እየደረሰ እንደሆነ ይታወቃል። በተለይ ቦረና እና ሱማሌ ክልል ተከስቶ የነበረው ድርቅ አብነት አድርጎ ማንሳት ይቻላል። በተደጋጋሚ ድርቅ በሚከሰትባቸው በእነዚህ አካባቢዎች ውሃ መኖሩ ብቻውን ትርጉም የለውም። የመኖ ልማትም በስፋት ማከናወን ካልተቻለ የእንስሳቱ ሕይወት አደጋ ላይ መውደቁ አይቀርም።

በመሆኑም በእነዚህ አካባቢዎች ያለውን የማይቋረጥ ውሃ ተጠቅመን መኖን ብናለማ ኖሮ ድርቁን መቋቋም በቻልን ነበር። ግን ያለንን አቅም አልተጠቀምንበትም። የእንስሳት መኖ አቅርቦትን ለማሻሻል የመኖ ልማትን የማረጋገጥ፤ የተፈጥሮ ግጦሽ ምርታማነትን የማሻሻል፤ የአካባቢ ጥበቃንና የተፋሰስ ልማትን ማጠናከር ሥራዎች ድርቅን ለመቋቋም የሚያስችል አቅም ለመፍጠር ወሳኝ ናቸው። አስቀድሜ እንዳልኩት ግን ችግሮች ተከስተው ሲገኙ ከዚያ ለመውጣት የሚቻልበት አቅም በማጠናከር የሚያስችሉ ሥራዎች መሥራት ያስፈልጋል። እስካሁን በተሠሩት ሥራዎች ጅምር ውጤቶች አሉ። ግን ችግሩ በጣም ሰፊ በመሆኑ ደረጃ በደረጃ መፍታት ያስፈልጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የአርብቶአደሩ ከብቶች በሕገወጥ መንገድ ወደ ጎረቤት ሀገራት እየተወሰዱ መሆናቸው ይታወቃል። ሚኒስቴሩ ለአርብቶአደሩ ቅርብ እንደመሆኑ በከብት ግብይትና ጤና፣ በኳረንቲን አገልግሎት ማስፋፋት ላይ ምን እየተከናወነ ነው?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** ከግብይት ጋር ተያይዞ ያሉ ችግሮች በዋናነት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ከኅብረት ሥራ ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ነው። ሆኖም የካውንስሉ አባልና አርብቶአደሮችን ጉዳይ እንደሚመራ ተቋም አይመለከተንም ማለት አይደለም። ምክንያቱም የቁም እንስሳት ሕገወጥ ግብይት አርብቶአደሩን ሕይወት በቀጥታ የሚነካ መሆኑ ግልፅ ነው። አንዱ ችግር የገበያ ማዕከላት ያለመኖር ሲሆን በተጨማሪም አርብቶአደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ የሚሸጥበት ሁኔታዎች ምቹ ያለመሆናቸው ነው። በእኛ በኩል የገበያ ማዕከላቱን የማስፋት ጉዳይ ትኩረት የተሰጠው ነው። ጎን ለጎንም የግብይት ሥርዓቱን የማሳለጡ፤ ቀጣናዊ ትስስሩ የበለጠ ሕጋዊ እንዲሆን የሚመለከተው አካል ይሠራል። ግን በእኛ በኩል ጉድለቱ የት ጋር ነው ያለው? የሚለውን ጥያቄ መፍታት ያስፈልጋል። የእሴት ሰንሰለቱ የተጠናከረ ሥርዓት መፍጠር ይገባል። ሕገወጥ ንግዱን ከመከላከል አኳያ የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን፤ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር በጋራ በመሆን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ።

በእኛም በኩል ከእንስሳት ግብይት ጋር በተያያዘ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የተጀመረ ሥራ አለ። የእንስሳት ግብይቱ ሲከናወን የነበረው መደበኛ ባልሆነ መንገድ ነበር። አርብቶአደሩ ከእንስሳቱ ማግኘት የሚገባውን ጥቅም በአግባቡ ማግኘት የማይችልበት፤ ለሕገወጥ ንግድ የሚዳረግበት፤ ድንበር አቋርጦ ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድበት ሁኔታ ስለነበር በተረጋጋ ሁኔታ የመደራደር አቅም አልነበረውም።

በመሆኑም አርብቶ አደሩ የእንስሳት ውጤቶችን መሸጥና ገቢ ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ውስን መሆን እንደአንድ ችግር ተለይቷል። ይህንንም ለመፍታት ዘመናዊ የእንስሳት ግብይት ማዕከላት ግንባታ በበርካታ አካባቢዎች ተከናውኗል፤ እየተገነቡም ነው። በእነዚህ ማዕከላት መኖና ውሃ ማግኘት የሚችል በመሆኑ በተረጋጋ ሁኔታ ከተረካቢዎች ተደራድሮ በአጥጋቢ ዋጋ መሸጥ የሚችልበትን ሁኔታ ፈጥሯል።

**አዲስ ዘመን፡- ዘንድሮ ለ19ኛ ጊዜ በሚከበረው የአርብቶአደሮች ቀን የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራትን ተሳታፊ ማድረግ ያስፈለገበት ምክንያትና ስለተደረገው ዝግጅት ቢያብራሩልን?**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** ዘንድሮ ለ19ኛ ጊዜ በሚከበረው የአርብቶ አደሮች ቀን በዓል ከወትሮው በተለየ መልኩ የምሥራቅ አፍሪካ አርብቶ አደሮች የሚሳተፉበት ሲሆን በዚህም የሀገራቱን ኢኮኖሚያዊ፤ ማኅበራዊና ዲፕሎማሲያዊ ትስስር ይበልጥ እንዲጠናከር ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ ነው። ከዚህ ቀደም በሀገር አቀፍ ደረጃ ይከበር የነበረው የአርብቶአደሮች ቀን ዘንድሮ በተለየ ሁኔታ በሁሉም የምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት አርብቶአደሮች፤ ከፍተኛ ባለሥልጣናት እና ዲፕሎማቶች ባሳተፈ መልኩ ይከበራል። በበዓሉ በዋናነትም የሀገራቱን የቀደመ ታሪካዊ ፤ ባህላዊ ፤ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ይበልጥ የሚያጠናክሩ አውደ ትዕይንቶች፤ ኤክስፖና የፓናል ውይይቶች ይካሄዳሉ።

የአርብቶ አደር በዓል እንደሀገር መከበር መጀመሩ አርብቶአደሩ ሕይወቱን ለማሻሻል ትልቅ አቅም ፈጥሯል። በተለይ ማኅበረሰቡ በተደጋጋሚ የሚያነሳቸውን ጉዳዮች ትኩረት እንዲያገኙ ብሎም በፖሊሲና ስትራቴጂ ማዕቀፍ እንዲደገፉ አወንታዊ ሚና ተጫውቷል። የሚኒስቴሩም መቋቋም የዚሁ ትኩረት አካል ሲሆን፤ ተቋሙ የአርብቶአደሩን ሕይወት ከማሻሻል ባለፈ በአካባቢዎቹ ያሉ የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት እምቅ አቅሞች ለሀገር ልማት በተገቢው መልኩ እንዲውሉ ለማድረግ የተሰጠውን ተልዕኮ እየፈፀመ ይገኛል።

በየሁለት ዓመቱ በሚከበረው የአርብቶ አደር ቀን በዓልም በዋናነት የአርብቶ አደሩ ጉዳይ እንደመንግሥት እውቅና እንዲሰጠው፤ ያሉበት ውስብስብ ችግሮች እንዲፈቱና ተግባራዊ የመፍትሔ አቅጣጫዎች እንዲቀመጡ ከማድረግ አኳያ አበረታች ሥራዎች ተከናውነዋል። በዘንድሮውም በዓል በተለይ የአርብቶአደር ሕይወት ድንበርና ወሰን የማያግደው እንደመሆኑ፤ በቀጣናው ያሉ አርብቶአደሮች ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረ ማኅበራዊ ግንኙነት ለላቀ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ታሳቢ ተደርጎ ዝግጅት ተደርጓል።

የአፋር ክልላዊ መንግሥት 19ኛውን የአርብቶአደሮችን ቀን በዓል አዘጋጅ የነበረ ቢሆንም በዓሉ ቀጣናዊ ትስስር በሚፈጥር መልኩ እንዲከበር በመንግሥት አቅጣጫ መሰጠቱን ተከትሎ ዘንድሮ ‹‹አርብቶአደርነት የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም›› በሚል መሪ ሃሳብ ከጥር 17 እስከ ጥር 23 በሚሊኒየም አዳራሽ እንዲካሄድ ተወስኗል።

በእነዚህ ቀናትም የሁሉንም አርብቶአደር አካባቢዎች ባህላዊ፤ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቱፊቶች የሚያንፀባርቁ አውደ ትዕይንቶች፤ ኤክስፖና የፓናል ውይይቶች ይካሄዳሉ። ከእነዚህም መካከል የግመል ግልቢያና የግመል ወተት የመቅመስ ትዕይንቶች ተካተዋል። በፓናል ውይይቶቹም በኢጋድ በኩል የተጋበዙና ቁጥራቸው ከ250 የሚልቁ የየሀገራቱ አርብቶ አደር ተወካዮች፤ ዲፕሎማቶችና የግብርና ባለሙያዎች ይሳተፋሉ።

መሪ ሃሳቡ አርብቶአደርነት ሁሉም ሀገራት ሕዝቦች የሚያዋህድና ኅብረቀለም የሚፈጥር መሆኑን ለማሳየት ታሳቢ ተደርጎ ነው የተቀረፀው፤ በበዓሉ የሚታደሙ አርብቶ አደሮች ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸውን ከማጠናከር ጎን ለጎን የጋራ በሆኑ እንደ ድርቅ፤ የጎርፍ አደጋ እንዲሁም ኮንትሮባንድ ንግድ በመሰሉ ችግሮች ዙሪያ እንዲሁም የልማት አማራጮች ላይ ይበልጥ ተቀራርበው እንዲሠሩ ምቹ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይታመናል።

በመክፈቻው ዕለት ብቻ ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ ከ500 በላይ አርብቶአደሮች ተሳታፊ የሚሆኑ ሲሆን በየአካባቢያቸው የሚገኙ የተፈጥሮ ፀጋዎች ለታዳሚው የሚያሳዩበት መድረክ ተመቻችቷል። በበዓሉ የአፋር አርብቶአደሮች ከጅቡቲ፤ በሱማሌ ክልል አርብቶአደር ከሱማሌ ላንድና ከሱማሌ፤ በኦሮሚያና ደቡብ ያሉት ከኬንያ፤ ጋምቤላ ያሉት ከደቡብ ሱዳን እንዲሁም ቤኒሻንጉል አርብቶአደሮች ጋር የባህል፣ የታሪክ፣ የኢኮኖሚ፣ የገበያ ትስስራቸውን ይበልጥ የሚያጠናክሩበት መንገድ ውይይት ያደርጋሉ።

የአርብቶአደር አካባቢዎችን የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት አማራጮች ለማሳየት ጥረት ይደረጋል። የቀጣናው አርብቶአደሮች ልምድና ተሞክሮቻቸውን በመለዋወጥ የንግድ ትስስራቸውን ይበልጥ እንዲያሳልጡ፤ ብሎም የሚያጋጥሟቸውን የጋራ ችግሮች በጋራ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያገለብቱ ዕድል ይፈጥራል።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ሥም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ዶክተር እንድሪያስ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የባሕር በር ስምምነቱ - ለአምራች ዘርፉ ፈጣን እድገት

**አንተነህ ቸሬ**

በአምራች ዘርፉ እድገት ላይ ከተጋረጡ መሰናክሎች መካከል አንዱ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ በፍጥነት የተሳለጠ አለመሆኑና በዚህም ምክንያት የሚፈጠረው የዋጋ ውድነት ነው። የሎጂስቲክስ ሥርዓት ከአምራች ዘርፍ ውጤታማነት ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው። ፈጣንና ቀልጣፋ የምርት ግብዓቶችና የምርቶች ዝውውር በአምራች ዘርፉ ውጤታማነት ላይ ያለው ተጽእኖም ቀጥተኛ ተፅዕኖ ነው። ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ምርት እንዲጨምር እንዲሁም የምርት ስርጭት ፈጣንና የተሳለጠ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። ግብዓቶችንና ምርቶችን በፍጥነት የማያገኙ አምራቾችና ምርት አከፋፋዮች፣ በምርት ሰንሰለት ውስጥ ውጤታማ ሆነው ሊቀጥሉ አይችሉም።

ከሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ 40 በመቶ ድርሻ ያለው የሎጂስቲክስ ዘርፍ፣ በርካታ ውስብስብ ችግሮች አሉበት። ከእነዚህ ሰንኮፎች መካከል የጭነት ዓይነቶችንና ብዛትን የሚያስተናግድ አቅም አለመኖር፤ መርከቦች በወደቦች አካባቢ ጭነት ለማራገፍ የሚያጠፉት ጊዜና በዚያም ሳቢያ የሚፈጠረው የወደብ መጨናነቅ፤ የተጓተተ የመርከቦች ኦፕሬሽን፤ የማከማቻና የኀተራዎች እጥረት፤ የጭነት መኪኖች በወደብ፣ በኬላዎች፣ በድንበርና በጭነት ክብደት መመዘኛ ጣቢያዎች የሚያጠፉት ጊዜ መብዛት ጥቂቶቹ ናቸው።

ብሔራዊ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ (National Logistics Strategy) እንደሚያመለክተው፣ የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ ሥርዓት የሎጂስቲክስ ሥርዓት ውጤታማነት መለኪያ በሆኑት የሎጂስቲክስ ጊዜና ወጪ መመዘኛዎች ሲመዘን በእጅጉ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። በትራንዚት ጊዜ፣ በዕቃዎች እና በመርከቦች የወደብ ላይ ቆይታ፣ ጭነት ከወደብ በማንሳት አቅምና በመሰል የሎጂስቲክስ የአፈጻጸም መለኪያዎች በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የሎጂስቲክስ ሥርዓቱ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ ነው። በችግሩ ውስጥ ዘርፉ የሚመራበት ሕግና ፖሊሲ፣ የተዘረጋው መሠረተ ልማት፣ ዘርፉን የሚመሩና የሚቆጣጠሩ ተቋማት አሠራር፣ የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጪዎችና አገልግሎት ተጠቃሚዎች ብቃት እና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች የየራሳቸው ድርሻዎች አሏቸው።

የዓለም ባንክ የሎጂስቲክስ አፈፃፀም ሪፖርት እንደሚያሳየው፤ ኢትዮጵያ በዋና ዋና የሎጂስቲክስ ክዋኔ መለኪያዎች (የጉምሩክ አገልግሎት፣ መሠረተ ልማት፣ ዓለም አቀፍ ጭነት፣ የሎጂስቲክስ ብቃት፣ ክትትል እና ጭነትን በወቅቱ ማድረስ) ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላት ሀገር ናት። ጉዳዩን የበለጠ አሳሳቢ የሚያደርገው ብዙ ሀገራት የሎጂስቲክስ አፈፃፀማቸው እየተሻሻለ ሲሄድ የኢትዮጵያ ግን የበለጠ ማሽቆልቆሉ ነው።

ሀገሪቱ ላለፉት ተከታታይ ዓመታት ያስመዘገበችውን አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ተከትሎ የገቢና የወጪ ዕቃዎችና የሀገር ውስጥ የንግድ እንቅስቃሴ በመጠንና በዓይነት በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። በመሆኑም የሀገሪቱን የወጪ ንግድ ልማት ለመደገፍ መከናወን ካለባቸው ቁልፍ ተግባራት መካከል አንዱ ቀልጣፋና ውጤታማ የሎጂስቲክስ ሥርዓት መዘርጋት ነው።

ቀልጣፋ የሎጂስቲክስ ሥርዓትን እውን ለማድረግ በብዛትና በጥራት ያደገ ውጤታማ የወደብ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን እጅግ አስፈላጊ ተግባር ነው። ይህ ዓይነቱ የወደብ አጠቃቀም ከላይ ለተጠቀሱት የሎጂቲክስ ሥርዓቱ ችግሮች ሁነኛ መፍትሔ ይሰጣል። በቀደመው ታሪኳ የብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ፣ ባለፉት 30 ዓመታት በወደብ እጦት ምክንያት ለከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጫና ተዳርጋለች። ለወደብ ኪራይ ከፍተኛ ገንዘብ እያወጣች ነው፤ የጭነት አገልግሎት ሥርዓቱ ፈጣንና ቀልጣፋ ባለመሆኑ የሀገሪቱ የአምራች ዘርፍ የምርት ግብዓቶችን በሚፈለገው ፍጥነት እንዳያገኝና በሀገር ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች በአጭር ጊዜ ለዓለም ገበያ እንዳይደርሱ ትልቅ መሰናክል ሆኗል።

በሎጂስቲክስ ሥርዓቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚፈጥረው የወደብ ጉዳይ፣ በአምራች ዘርፍ እድገት ላይ የሚኖረው ሚና በሌሎቹ ዘርፎች ላይ ካለው ተፅዕኖ ይበልጣል። የወደብ ተጠቃሚነት ለአምራች ዘርፍ ወሳኝ እድገት መሠረታዊ ግብዓት/መደላድል ነው። የበርካታ ባለሙያዎች የጥናት ግኝቶችም ይህን እውነት በብርቱ ይደግፋሉ። የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ሰር ፖል ኮሊየር፣ ድህነት በተንሰራፋባቸው አካባቢዎች የሚገኙ ወደብ አልባ ሀገራት በወደብ አልባነታቸው በእጅጉ እንደሚፈተኑ አስረድተዋል። ወደብ ያላቸው ሀገራት ሰፊና በርካታ የገበያ አማራጮች ሲኖራቸው ወደብ አልባዎቹ ግን የገበያ ሸርክናቸው ከጎረቤቶቻቸው ጋር ብቻ እንደሆነ ገልፀዋል።

ፕሮፌሰር ጄፍሪ ሳክስ የተባሉ የምጣኔ ሀብት ምሁር፣ የወደብ ተጠቃሚነት ፈጣን የምጣኔ ሀብት እድገት ላስመዘገቡ የእስያ ሀገራት ባለውለታ እንደሆነ በስፋት አብራርተዋል። ቻይና፣ ደቡብ ኮሪያ፣ ጃፓን፣ ኢንዶኔዥያ፣ ሲንጋፖር... በወደብ ተጠቃሚነታቸው ምክንያት የማምረቻ ዘርፋቸው አስገራሚ የሆነ እድገት ማስመዝገቡንና ይህ እድገትም ለጥቅል ሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገት ዋና ድርሻ እንዳለው ገልፀዋል።

ያዕቆብ ኃይለማርያም (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ ‹‹አሰብ የማን ናት?›› በተሰኘው መጽሐፋቸው ላይ ‹‹... በ2008 ዓ.ም. በዓለም 44 ወደብ አልባ ሀገሮች ሲኖሩ ከእነዚህ ውስጥ ሠላሳ አንዱ ድሃ ሲሆኑ፣ አሥራ ሦስቱ ደግሞ የድሃ ድሃ የሚባሉ ናቸው። እነዚህ አሥራ ሦስት የድሃ ድሃ ሀገሮች በአፍሪካ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ኢትዮጵያም ከእነዚሁ አሥራ ሦስቱ ሀገሮች ተርታ ትሰለፋለች። እነዚህ ወደብ አልባ ድሃ ሀገሮች ወደ ውጭ የሚልኳቸው ምርቶች በአንድና በሁለት ሰብሎች ወይንም በአንድና በሁለት የኢንዱስትሪ ውጤቶች ወይም ጥሬ ዕቃ የተወሰኑ ናቸው። ስለሆነም ከድህነት የመላቀቅ ዕድላቸው በጣም የመነመነ መሆኑን ሊቃውንት ይናገራሉ...›› ብለዋል።

እነዚህ ሁሉ የባለሙያ ጥናቶች የሚያረጋግጡት የወደብ ተጠቃሚነት በሀገራዊ ምጣኔ ሀብት፣ በተለይም በአምራች ዘርፉ፣ እድገት ላይ ከፍ ያለ ተፅዕኖ እንዳለው ነው። የኢትዮጵያ አምራች ዘርፍም ከዚህ ነባራዊ ሁኔታ ውጪ አይደለም። ኢትዮጵያ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን ባከበረ መልኩ የወደብ ተጠቃሚ ለመሆን በቅርቡ ከሶማሊላንድ ጋር የተፈራረመችው የመግባቢያ ስምምነት፣ የአምራች ዘርፉ በሎጂስቲክስ ሥርዓቱ ደካማ አፈፃፀም ምክንያት የሚያጋጥሙትን ችግሮች የሚያቃልል እንደሚሆን ተስፋ ተጥሎበታል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ እንደሚሉት፣ ወደብ ለማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ እድገት ልዩ ሚና አለው። ማኑፋክቸሪንግ ከሚቀላጠፍባቸውና ውጤታማ ከሚሆንባቸው መንገዶች መካከል አንዱ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ነው። የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ ሥርዓት ውድና ጊዜ የሚፈጅ ነው፤ የወደብ ባለቤት መሆን ፈጣን የወጪና ገቢ ንግድ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ የሎጂስቲክስ ሥርዓቱን ችግሮች ይፈታል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈፃሚው ማብራሪያ፣ የወደብ ተጠቃሚነት በኢንዱስትሪ ፓርኮችና በድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ያለው የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ያስችላል። አምራች ኩባንያዎች ምርቶቻቸውን ለውጭ ሀገር ገበያ እንዲያቀርቡ ብሎም ለአምራች ኢንዱስትሪው የሚረዱ ግብዓቶች በፍጥነት እንዲደርሳቸው መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል። ስለሆነም በወጪ ገቢ ንግድ ፍሰት ላይ ጉልህ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

የምርት ግብዓቶችንና ምርቶችን ወደ ሀገር ለማስገባት የሚፈጀውን ረጅም ጊዜና የተንዛዛ ቢሮክራሲ ለማሳጠር፤ የተመረቱ ምርቶችን በሚፈለገው ፍጥነትና መጠን ያለመድረስ አሁናዊ ችግርን በዘላቂነት ለመቅረፍ ብሎም በወደቦች አካባቢ ያሉ አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪዎችንና መጉላላቶችን ለማስቀረት የወደብ ባለቤት መሆን ምርጫ የሌለው መፍትሔ ነው።

‹‹ኢትዮጵያ የባሕር በር ለማግኘት እና ለማልማት የሚያስችላትን የመግባቢያ ስምምነት ከሶማሊላንድ ጋር መፈፀሟ ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች እና ነፃ ንግድ ቀጣና ውስጥ የሚገኙ አምራች ኩባያዎች የወጪ ንግዶቻቸውን እንዲያቀላጥፉ ብሎም ሀገራችን ለዘመናት የባህር በር በማጣቷ ያላገኘቻቸውን ግዙፍ ሀገራዊ ጥቅሞች እንድታገኝ የሚያስችል ነው›› ይላሉ።

‹‹የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት የሆነች፣ በቀደመው ታሪኳ የብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረች፣ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ... ሀገር፣ አሁን ወደብ አልባ መሆኗ ፍትሐዊ አይደለም›› የሚሉት አቶ አክሊሉ፣ ስምምነቱ ሁሉንም ወገን አሸናፊና ተጠቃሚ የሚያደርግ፣ የጋራ ተጠቃሚነት መርህን ያከበረ(Win-Win) እና ለአምራች ዘርፉ እድገት ትልቅ ሚና ያለው ስምምነት መሆኑንም ያስረዳሉ።

በተጨማሪም ‹‹ኢትዮጵያ የባህር በር ለማግኘት ያደረገችው ስምምነት የ120 ሚሊዮን ሕዝብ የህልውና ጥያቄ እንጂ የቅንጦት ጉዳይ አይደለም፤ ኢትዮጵያ የባሕር በር በእጅጉ የሚያስፈልጋት፤ የሚገባትና ለስኬታማነቱም በፅናት የሚቆም ሕዝብና መንግሥት ያላት ሀገር ናት›› በማለት ይገልፃሉ።

የ"ጽንኤል ኢንዱስትሪያል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር" መሥራችና ባለቤት ወይዘሮ ብርቱካን አበበ፣ "ስምምነቱ ትልቁን ባዶነታችንን የሚዘጋ እርምጃ ነው" ይላሉ። እሳቸው እንደሚናገሩት፣ የወደብ ክፍተቱ ሁሉም አምራች በብዙ ነገሮች እንዲቸገር አድርጎታል። የሎጂስቲክስ ክፍያው ውድ ስለሆነ አምራቹ ምርቱን ለገበያ የሚያቀርበው በውድ ዋጋ ነው። የወደብ ተጠቃሚ መሆን ይህን ችግር ለማቃለል ይረዳል። ለአምራች ዘርፉ እድገት በጎ አስተዋፅዖ የሚኖረውን ይህን ስምምነት፣ በተቻለ ፍጥነት ወደ ተግባር መቀየር ይገባል።

ዶክተር ዮሐንስ ብርሃነ ወደ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብቶ ለመሰማራት በቅርቡ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር የሥራ ስምምነት የፈፀመው የ‹‹ተርትል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር›› ባለቤት ናቸው። ‹‹የስምምነቱ ዜና በተለይ ለአምራች ዘርፉ መልካም ብስራት ነው›› ይላሉ። በሀገሪቱ በኢንቨስትመንት መስክ ካሉ ችግሮች አንዱ የወደብ ችግር እንደሆነ የሚናገሩት ዶክተር ዮሐንስ፣ ስምምነቱ ምርቶችን ወደ ውጭ በፍጥነት ለመላክ የሚደረገውን ጥረት እንደሚያሳልጠው ይገልፃሉ።

በዓለም ላይ ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ኖሯት ወደብ የሌላት ትልቋ ሀገር ኢትዮጵያ የመሆኗ መራራ ሃቅ፣ የወደብ ተጠቃሚነት ጉዳይ ለኢትዮጵያ የህልውና ጉዳይ ስለመሆኑ አመላካች ነው። የወደብ ተጠቃሚነት ጉዳይ ከወጪና ገቢ ንግድ ጋር የተቆራኘ ነው፤ የወጪና ገቢ ንግድ ደግሞ በአምራች ዘርፉ ውጤታማነት ላይ የሚወሰን ነው። ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት ለወደብ ተጠቃሚነት ጉዳይ ላቅ ያለ ትኩረት በመስጠት የአምራች ዘርፉን አፈፃፀም ማሻሻልና መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ማሳካት ይገባል ሲሉ ዶክተር ዮሐንስ ብርሃነ ተናግረዋል።

**በቀደመው ታሪኳ የብዙ ወደቦች ባለቤት የነበረችው ኢትዮጵያ፣ ባለፉት 30 ዓመታት በወደብ እጦት ምክንያት ለከፍተኛ ምጣኔ ሀብታዊ ጫና ተዳርጋለች። ከፍተኛ ገንዘብ እያወጣች ነው**

# ጎሜ

## መንግሥትን ከሀገሩ መለየት ያቃተው . . .!

**ፌኔት ኤሊያስ**

‹‹መንግሥት ሥራውን ይሠራል፤ ሕዝብን ይመራል። ጊዜው ሲያልቅ በየትኛውም መንገድ የሚቀየርበት አጋጣሚ ይፈጠራል። በጣም የሚደንቀኝ ግን በሥልጡን ዓለም የሚኖሩ አንዳንድ ዲያስፖራዎች ይህንን አያውቁም። ወይም ድርጊታቸው በሙሉ ይህን እንደማያውቁ አስመስሏቸዋል። ›› ሲል ተሰማ መንግሥቴ በተደጋጋሚ የሚያበሳጨውን ጉዳይ ተናግሮ በረዥሙ ተነፈሰ።

ዘውዴ መታፈሪያ በበኩሉ፤ ‹‹በእርግጥ ሀገር እና መንግሥት ፍፁም የተለያዩ ናቸው። ሀገር አጠቃላይ ሕዝብን፣ ሉዓላዊነትን፣ ድንበርን የሚያካትት ብቻ አይደለም፤ ሀገር የጋራ ማንነትን፣ ባሕልን፣ የጋራ ኢኮኖሚን እና ሌሎች በቃል ሊገለፁ የማይችሉ ብዙ ጉዳዮችን ዓምቆ የያዘ መገለጫው ብዙ የሆነ ነው። ሀገር የአንድ ሰሞን መንግሥት አይደለም። መንግሥት ሀገርን የሚያስተዳድር ሥርዓት ነው። ሀገር ለዘላለም ሲኖር፤ መንግሥት ግን ለዘላለም አይኖርም። ›› ሲል የሀገር እና የመንግሥትን ልዩነት ተናገረ።

ገብረየስ ገብረማሪያም ከት ብሎ እየሳቀ፤ ‹‹ ባለምጡቅ አዕምሮ ባለቤት ነን ባዮቹ ከመጽሐፍ መደርደሪያ ፊት ለፊት መነፅራቸውን እያስተካከሉ ቁጭ ብለው ሲናገሩ፤ በተደጋጋሚ መንግሥትን አምርረው እንደሚጠሉ ሳይሆን ባለማስተዋል ሀገራቸውን አምርረው እንደሚጠየፉ አልፈው ተርፈው እንድትጠፋ የሚፈልጉ መሆኑን ሲናገሩ ታዝቤአቸዋለሁ። ተከታዮቻቸውም ለምን ይህን ትላላችሁ? ብለው አይጠይቋቸውም። ›› ሲል እርሱም እንደተሰማ አንዳንድ ዲያስፖራዎችን እየታዘበ መቆየቱን ተናገረ።

ዘውዴ እንደለመደው የእነተሰማን ንግግር በጽኑ ለመቃወም አልሞከረም። ነገር ግን ከእነርሱ የሚለይበትን፤ አንዳንድ ዲያስፖራዎችን የሚቃወምበትን እና የሚደግፍበትን እውነተኛ እምነቱን ተናገረ። ‹‹በእርግጥ ሁልጊዜ ነገርን በቅጡ ሳያዩ ፍፁም መጥፎ ጎኑን ብቻ ለማየት ራስን ማዘጋጀት ስህተት ነው። በሌላ ጎን አንድን ውሳኔ መጠራጠር ደግሞ መብት ብቻ ሳይሆን የሚደገፍ ነው። ዲያስፖራው መንግሥት የሚወስደውን እርምጃም ሆነ የሚሠራውን ማንኛውንም ሥራ ፍፁም ደጋፊ መሆን አለበት ብሎ መደምደም ተገቢ አይደለም። መጥፎ ጎኑን ብቻ ሳይሆን ደግ ጎኑንም መመልከት ይገባዋል። ካላችሁ ግን እስማማለሁ።

በእርግጥ ለኢትዮጵያ ወደብ የሕልውናዋ ጉዳይ ነው። ይህንን ተከትሎ በመንግሥት በኩል ለዘለቄታው የወደብ ችግርን ለማቃለል እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች አሉ። ከሥራዎቹ መካከል ለጊዜው የተሻለ ነው ተብሎ የታመነበትን ከሶማሌ ላንድ ጋር በወንድማማችነት እና በትብብር ወደብ የማግኛ ድርድሮች ስለመካሔዳቸው ሲነገር፤ አንዳንድ ዲያስፖራዎች ‹ሙሉ ለሙሉ ትክክል አይደለም። ኢትዮጵያ በሶማሌላንድ በኩል ወደብ ማግኘት የለባትም። ከዚህ በኋላ ከንቱ ጥረት ነው፤ ኢትዮጵያ ፍፁም ወደብ ማግኘት አትችልም። › ብለው በየክርክር መድረኩ እና በተለያዩ የማኅበራዊ የትስስር ገፆች ላይ መናገራቸውን እቃወማለሁ። በጉዳዩ ላይ ጥርጣሬ እንዳላቸው መግለፃቸው ግን ምንም የሚያስከፋ ነገር የለውም። ነገር ግን መንግሥትን እና ሀገርን ባለመለየት የመንግሥትን ሥራ ለመቃወም በሚመስል መልኩ ሀገር ላይ ጉዳት የሚያስከትል ንግግር ማድረግ ፍፁም ተገቢ አይደለም›› ሲል ተናገረ።

ተሰማ በበኩሉ፤ ‹‹ በእርግጥ ኢትዮጵያ ያለችበትን ተጨባጭ ችግር የማያውቁ ይኖራሉ። ጅቡቲ ላይ ከአስር በላይ ኃያላን ሀገራት የባሕር ኃይላቸውን እያሠፈሩ ነው። በሆነ አጋጣሚ እርስ በእርስ ቢጋጩ እንኳ የኢትዮጵያ ጉሮሮ ሙሉ ለሙሉ ተዘጋ ማለት ነው። ኢትዮጵያ አንዲት የጅቡቲ ወደብ አማራጭን ብቻ ይዛ መቆየት በዓለም እየታየ ካለው ፖለቲካዊ ሁኔታ አንፃር እጅግ አደገኛ እና አስጊ ነው። ይህንን አስቀድሞ ለመከላከል አማራጭ በሮችን ለማግኘት ማማተር የግድ ነው።

ይህ አሁን መግባባት ላይ የተደረሰበት ከሶማሌ ላንድ ለሃምሳ ዓመት በሊዝ ይዘን የምንጠቀምበት ወደብ ደግሞ በከፍተኛ ጥንቃቄ በጦርነት ሳይሆን፤ የዓለምን ሕግ መሠረት ባደረገ መልኩ በሰጥቶ መቀበል መርሕ በብልሃት በጣም የሚያጓጓ ጥቅምን በማሳየት ለማግኘት መሞከርን ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም አንፃር አይቶ ማሞገስ እንጂ በዘይላ እና በበርበራ መሐል ያለችው ሎጋያ የሶማሌ ናት። የሎጋያን አካባቢ ኢትዮጵያ ከያዘች የሶማሌ መንግሥት ይከፋል፤ የሶማሌ ሕዝብ ኢትዮጵያ ላይ ቂም ይይዛል፤ ብሎ መመፃደቅ አገር ወዳድነት አይደለም።

> **ኢትዮጵያ አንዲት የጅቡቲ ወደብ አማራጭን ብቻ ይዛ መቆየት በዓለም እየታየ ካለው ፖለቲካዊ ሁኔታ አንፃር እጅግ አደገኛ እና አስጊ ነው**

እኛም እያልን ያለነው ይህንኑ ነው። አንተ እንደምትለው አንዳንድ ዲያስፖራዎች የሚሰጡት ሃሳብ ፍፁም ያሳፍራል። ለችግሮች መፍትሔ የሚገኘው ያለፈውን በደንብ በመመርመር እና አሁን ያለውን ሁኔታ በማጥናት መሆን ሲገባው አስቀድሞ ማጥላላት ላይ ሲያተኩሩ ይታያሉ። በጥናት ላይ የተመረኮዘ ሥራ ሲሠራ እነርሱ ግን በተቃራኒው፤ ዓሣ ለመያዝ እንደሚደናበር ዓይነስውር ወይም ዓይኑን በጨርቅ አስሮ ጥንቸል ለመያዝ እንደሚሯሯጥ ጅል በስሜት በደመነፍስ ነገሮችን በአንድ ወገን በማየት አዋቂ መስለው ለመታየት ይሞክራሉ።

ሀገራቸውን በተመለከተ የሚሰጡት አስተያየት ያስደነግጣል። ከምንም በላይ በጣም ያበሳጨኝ አንድ ተንታኝ ነኝ ባይ "ኢትዮጵያ ፍፁም ወደብ ማግኘት አትችልም።› ሲል የተናገረው የሃሳብ ገበታ ተሳታፊው ፕሮፌሰር እጅግ አሸማቆኛል።" ሲል ተናገረ።

በእለቱ ዘውዴ ከመቼውም ቀን በላይ ከነተሰማ ጋር ተግባብቷል፤ እርሱም በበኩሉ፤ ‹‹አትፍረድባቸው፤ ዋነኛው ችግር አንተ እንደገለጽከው መንግሥት እና ሀገርን የመለየት ስላልቻሉ ነው። አሁን ያለውን መንግሥት የመጥላት ዝንባሌ በአንዳንድ ዲያስፖራዎች ዘንድ ይታያል። ይህ የተለመደ ነው። በፊትም እንዲህ ነበር። ወደፊትም እንዲሁ ይሆናል።›› ሲለው፤ ተሰማ ከተል አድርጎ ‹‹ራስን አድኖ ጠላትን ማጥፋት በሚመስል መልኩ መንግሥት እና መሪን መጥላት፤ ሀገርን ከመንግሥት መነጠል አለመቻል አልፎ ተርፎ የሀገርን ችግር ለማቃለል ወይም ለማስወገድ በሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ላይ የሚሠነዘሩ ትችቶች ያስነውራሉ። አንዳንዱ ደግሞ እነርሱን ተከትሎ ይሳሳቃል። ›› አለ።

‹‹የጨው ክምር ሲናድ የሚያውቅ ያለቅሳል፤ የማያውቅ ግን ይልሳል እንደሚባለው፤ አንዳንዱ ዲያስፖራ ደንታ ቢስ ነው። ኢትዮጵያ ላጋጠማት ችግር መፍትሔ ከማፈላለግ ይልቅ በሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች ላይ ያሾፋል። ሀገሩን ለሌሎች አሳልፎ ይሰጣል። ለሀገር ጠቃሚ ነገር ሲሠራ አድንቆ እንደመቆም፤ ለሌሎች ተቆርቋሪ ይሆናል። በአንድ የሃሳብ ገበታ ላይ ኢትዮጵያ ከሶማሌላንድ ጋር መስማማቷን ተከትሎ ግብፅ እያበደች የሶማሌን ጥቅም ለማስከበር ከጎኗ ነኝ እያለች እንደደነፋችው ሁሉ፤ ደንታ ቢስ ዲያስፖራዎችም ለሶማሌ ተቆርቋሪ መሆናቸውን ለማሳየት መሽቀዳደማቸው ከመቅለል መጠቅለልን ያስመኛል።

ቀላል ወይም ፍሬ ቢስ ሆኖ በሕዝብ ግምት ላይ ከመውደቅ መሞት እና በከፈን መጠቅለል ይሻላቸው ነበር። ሀገርን፣ ሕዝብንም ሆነ መንግሥትን አጠቃለው እንደጠላት መቁጠራቸው እና የጠላትን አቋም መውሰዳቸው፤ አልፈው ተርፈው የሌሎች ሀገሮችን አጀንዳ የሚያራምዱ መሆናቸው ሲታሰብ፤ ለኢትዮጵያ ከሚለፋው ሰው እኩል እነርሱም ኢትዮጵያዊ መባላቸው በቁጭት ያንገበግባል። እንደእኔ ሃሳብ ከሆነ እነዚህ ሰዎች በፍፁም ኢትዮጵያዊ መባል የለባቸውም። የሀገሩ ጠላት የሆነ ሰው የሀገሩ ባለቤት እንደሆነ ሰው መጠሪያው ሊሆን አይገባም። በጣም የሚያሳዝነው ደግሞ የእነርሱን ንግግር የሚደግፈው ሰው ነው። በድርጊታቸው ማዘን ቢቻል ትክክል አለመሆናቸውን ነግሮ መገሰፅ ሲገባ እያጨበጨቡ መሳቅ አሳፋሪ ነው።›› ሲል የልቡን ተናገረ።

ገብረየስ ትንሽ የተሰማን ሃሳብ ለማለሳለስ የፈለገ በሚመስል መልኩ፤ ‹‹ የመንግሥትንም ሆነ የሕዝብን ስህተት መንቀስ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ይህ ሲሠራ ትክክለኛውን የሕዝብን እና የመንግሥትን ሥራ ክፍተት ከማወቅ ውጤቱንም ከመረዳት የመነጨ መሆን አለበት። በተጨማሪ የሚሰጠው አስተያየት ሀገርን ምን ያህል እንደሚጎዳ መረዳት እና ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው። በስሜት መመራት እና ሁኔታዎችን ሳያገናዝቡ እና ከብዙ አቅጣጫዎች ሳይመለከቱ የነገሩን ምንነት፣ ውስጣዊ ግንኙነትን ሳያጤኑ ሃሳብ መሰንዘር፤ አልፎ ተርፎ ከሀገር ፍላጎት በላይ የሌሎች ሀገሮችን በተለይም የኢትዮጵያን ጥቅም የሚቃረኑትን ማስቀደም፤ በሀገር ላይ መጨከን ነው።

በሁሉም ነገር ላይ ቀድሞ ቸኩሎ ከመቃረን ይልቅ እርስ በእርስ መግባባትን የመሰለ ነገር የለም። መደጋገፍ እና ወንድማማችነት ይቀድማል። በደንብ ልብ መባል ያለበት በዚህ ዓለም ብዙ ነገሮች የተወሳሰቡ እና የተመሰቃቀሉ ናቸው። ችግሮች ሲያጋጥሙ ከብዙ አንፃር መመልከት እንጂ፤ በአንድ በኩል ብቻ እያዩ ዕድሎች በሙሉ የተዘጉ መሆናቸውን ማስተጋባት ከንቱነት ነው። በእርግጥም አንዳንዴ ከሀገራቸው በላይ ስለሌላ አገር ተቆርቁረው ደጋግመው መናገራቸው እጅግ ያበሳጫል። ›› ሲል ተናገረ።

ዘውዴም በበኩሉ፤ ‹‹በተደጋጋሚ አንዳንድ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን ነገሮችን የሚያዩበት መንገድ ለምን በተደጋጋሚ የተሳሳተ እንደሚሆን ጥያቄ ይሆንብኛል። መኖሪያዋን ትታ መዞሪያዋን እንዳይባሉ ዘላለማዊ መኖሪያቸው መጠሪያቸው ከሆነችው ከኢትዮጵያ በላይ ኢትዮጵያ በምትሠራው ሥራ ሌሎች ተጎጂ እንደሚሆኑ ማስተጋባታቸው አስከፍቶኛል። አልፈው ተርፈው ለሀገራቸው የበለጠ ጠቃሚ የሆነውን ጉዳይ ማየት መለየት እና በጥንቃቄ ነገሮችን ለመለወጥ ጥረት ማድረግ ሲኖርባቸው፤ ሁልጊዜም የሚያዩት ዋናውን ሳይሆን ተቀፅላውን ነው። በሚሠሩ ሥራዎች ላይም የሚገኘውን መልካም ውጤት ሳይሆን በሥራው ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮች እና ወደ ፊት ሊያጋጥም ይችላል ብለው የሚያስቡትን በስጋት መልክ ያስቀምጣሉ።

ፍፁም ወደብ ሊኖራት አይችልም ብሎ በመደምደም የተጣደፈ ሃሳብ በመሰንዘር በአጉል ችኮላ ከመናገር አልፈው፤ የኢትዮጵያ ድርጊት ቀጣናውን የሚበጠብጥ እንደሆነ የማስመሰል ዝንባሌ የሚታይባቸው መሆኑ ያሳዝናል። ‹‹በከንቱ ኩራት እየተሰቃዩ ለኢትዮጵያ የሚያስቡ መስለው ከኢትዮጵያ ጥቅም ይልቅ የሌላ ሀገር ጥቅም የሚያሳስባቸው መሆኑን ማሳየታቸው ያስከፋል።›› አለ።

በመጨረሻ ተሰማ፤ ‹‹ ኢትዮጵያ ዲያስፖራውን ‹መታጠቂያዬን አጥብቁልኝ አጠንክሩኝ› እያለች እየተማፀነች ባለችበት በዚህ ጊዜ፤ መልሚያዋን ያቅዳሉ ለዛም ይሠራሉ ተብሎ ሲታሰብ በተቃራኒው መጥፊያዋን ለማመቻቸት ለሌሎች መሣሪያ ሲሆኑ መመልከት ያሳዝናል። እኔ በበኩሌ አንዳንድ ዲያስፖራዎች እንኳን ሊያለሙን የሚፈፅሙት ድርጊት ሊያጠፉን ፍላጎት ያላቸው ይመስላል። የምታደርገውን ሁሉ የሰውን አገር ሉዓላዊነት ለመድፈር እንዳሰበች፤ የሰውን ግዛት ለመውረር እየተዘጋጀች እንደሆነ የማስመሰል አካሔዳቸው ያበሳጫል።

ኢትዮጵያ ግን ቀድሞም ቢሆን ባላት የዘመናት ታሪክ ወራሪን ድል መንሳት እንጂ፤ አንዴም በታሪኳ ሌሎች ሀገሮችን ወራ የማታውቅ የራሷን መብት ስታከብር የሌላውንም አገር መብት የምታከብር ለዓለም ምሳሌ የሆነች ድንቅ አገር ነች።›› ሲል እርሱም በበኩሉ የሚያምንበትን ተናግሮ ሃሳቡን ጠቀለለ።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ሎሚ ለሽታ ጥምቀት ለትውስታ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

**"እነሆ ጥምቀት ደረሰ፤**
**ነጭ እና መብሩቅን እየለበሰ"**

ብለን ገና መጣ መጣ ከማለታችን በጊዜ የተሳፈረው ጥምቀት፤ እንደ ታክሲ ቆሞ አይጠብቅምና ትዝታውን ብቻ ጥሎልን እብስ አለ። ለመሆኑ ጥምቀት እንዴትስ አለፈ? መቼም የዋዛ አይደለምና ጥሎብን የማያልፈው የትዝታ መዓት የለም። በሀገራችን ኢትዮጵያ፤ በቅድስቷ ምድር የማይከበር በዓል የለም። አንዱን ከአንዱ ማስበለጥ ባይቻልም እንደ ጥምቀት ያለ ደማቅ ክብረ በዓል ለማግኘት ግን ያዳግታል። አብዛኛዎቹ በዓላት በገጠርና ከተማ አሊያም እንደየአካባቢው፤ የአከባበር ሥርዓትና ድምቀታቸው ይለያያል። በጥምቀት ምድር ግን በመላው ኢትዮጵያ ከገጠር እስከ ከተማ አቧራው ይጨሳል። ጭፈራው ... ድለቃው ... ዳቦና ጠላው፤ ብቻ ምኑ ቅጡ ... ከወዲያ መንፈሳዊ የአምልኮ ሥርዓቱ፤ ከወዲህ ደግሞ የባሕል ድግሱ፤ ላይና ታቹ በአጀብ የተሞላ ነው። "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" የሚለው ፉከራዊ አባባል ውስጣዊ ወኔውን እየቀሰቀሰው በአንድ እግሩ ቆሞ ጥምቀትን ፍለጋ የማይወጣ የለም። ጥምቀትም በእኩልነት ያምናል፤ ምንም ባይኖረን ካላቸው እኩል በደስታና ፌሽታ እናከብራለን። "ደም ካልፈሰሰ፤ ደም ካላየሁ" አይልም። በእለተ ጥምቀት እንዲሁ ዝም ብለን ወደ አደባባይ ብንወጣ፤ በባዶ ኪስ ወጥተን በገንዘብ ሊተመን የማይችል ደስታና እርካታ ሸምተን እንገባለን። ምክንያቱም ጥምቀት የነብስ እንጂ የሥጋ ብቻ አይደለም። የበዓሉን ደስታ የምናገኘው በአደባባይ ተሰባስበን በኅብረት ያለንን ስሜት በማዋጣት እንጂ፤ ስላለን ብቻ በተናጠል የምንሸምተው ባለመሆኑ ነው። ከምንም በላይ ኅብራዊ የመንፈስ ትስስርን ይሻል። ቢኖርም ባይኖርም ጥምቀት አያስጨንቅም። ትዝታም ሳይጥል አያልፍም። አብዛኛዎቻችን የጥምቀቱን ቀሚስና ጃኖ አውልቀን ካስቀመጥን ቀናት ተቆጥረው ሳምንት ለማስቆጠር ሁለት ያህል ቀናት ቢቀሩትም፤ የሞቀው ውሃ ግን ገና አልቀዘቀዘም። በተለይ በአንዳንድ አካባቢዎች ዛሬም ድረስ ዘልቋል።

በጥምቀት ምድር፤ "ለጥምቀት ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ" እያለ ባለው ሁሉ አጊጦ፤ አምሮ እንዲሁም አሸብርቆ የሚወጣው ሰው ብቻ አይደለም። ጥበብም ልክ እንደ ሰው ሁሉ በኪነ ጥበባት ድግስ ደመቅ ብላ፤ ከወትሮው በተለየ እምር ትላለች። የሚያብለጨልጨውንም የውብ ቀሚሷን ጥለት አዘቅዝቃ፤ እንደ ማለዳ ጀንበር ትወጣለች። ለጥምቀት የማይነሳ ብዕር የለም። ከያለበት ተጠራርቶ የማይሰባሰብ የሙዚቃ መሣሪያም እንዲሁ። ባለቅኔው ይቀኛል። አዝማሪው ያንጎራጉራል። ተወዛዋዡም ይወዛወዛል። ሠዓሊው በሥዕሉ፤ የቅርጽ ንድፍ ጥበበኛውም በቅርጻ ቅርጹ፤ ሁሉም ያለውን ይዞ ወደ አደባባይ ይወጣል። በዓሉ የአንዲት ቀን ብቻ ባለመሆኑ የአከባሪው የተዝናኖት ፍላጎት መጠኑ የገዘፈ፤ ዳርቻውም የሰፋ ይሆናል። ይህን ፍላጎት ተከትሎም በየስፍራው የሚቀርቡ የኪነ ጥበብ ሥራዎች የበዓሉ ዋነኛ ድምቀት ናቸው። በጥምቀት ብዙ ትዝትና ትውስታዎች "አሉኝ" ብንል፤ የትዝታዎቻችን ጥፍጥና ከእነዚሁ የጥበብ ጓዳዎች የራቀ አይደለም። ከሚከወኑ መንፈሳዊ ሥርዓቶች በተጨማሪ የክብረ በዓሉን ውበት የምንለካው፤ ተገኝተን ከተቋደስናቸው ኪናዊ የባሕልና የጥበብ ትርዒት አንጻር ነው። የጥምቀት ውበቱ ከምኑ ላይ ይሆን? ስንልም፤ ከአልባሳት፣ ከሚበላና ከሚጠጣው ብቻ እንዳልሆነ እንገነዘባለንና።

በጥምቀት የሚታዩ ባህላዊና ኪናዊ ቱርፋቶች ሁሉ ይማርካሉ። በዚህ ጊዜ የማይከውን ምንስ አለ፤ ውበት ከውበት ይለካል። ፍቅር በፍቅር ይታጨዳል። ከሁሉም ለመብለጥ ሁሉም አሸብርቆ ይመጣል። የቆነጃጅቱ አለባበስና የጸጉር አሠራር የወንዱም እንዲሁ ማራኪ እይታን ያጎናጽፋል። የጎበዙ የከዘራ አያያዝ ወንድነቱን ይናገራል። ሸንቀጥ እያለ ከውስጡ የጀግንነትን መንፈስ ለመላበስ ይታገላል። ጀግንነቱ ቢኖርም ባይኖርም፤ መስሎ መታየቱ ግን ግድ ነው። ምክንያቱም ከብዙዎች መሐል በዓይኑ አይቶ የወደዳትንና የተመኛትን፤ የሕይወቱ አጋር ልትሆን የምትችለዋን ሴት በዚህ ሁሉ አማሎ የራሱ ማድረግ አለበት። ልክ እንደ እርሱው አይቶ የሚመኛትም ብዙ ነውና `ሳይቃጠል በቅጠል` ነው ነገሩ። በተባረከው እለት የርሷ የሆነውን ልበ ሙሉ



የምትጠብቀዋም ሴት አትጠፋም። ሴቶቹም፤ ከሁሉም ሴቶች በላይ ቆንጅና ውብ ሆኖ ለመታየት ከጌጣ ጌጡ እስከ አልባሳቱ ባለው ሁሉ ይጠበቡበታል። በዓይኑ እያየ በልቡ ሲከጅላት የነበረው ጎበዝም እንዲህ ሲል ይጫወትላታል፤

**አሞራው በሰማይ ሲያይሽ ዋለ፤**
**የአንገትሽን ንቅሳት ውበትሽን እያለ።**

እንግዲህ አሞራው እርሱ እራሱ መሆኑ ነው። ልቧን አሸፍቶ ለመዝረፍ ሲል አስቀድሞ ቅኔውን በግጥምና በዜማ መዝረፍ የወጉ ነው።

ጥምቀትን በጣፋጭ ትዝታ ከሚያስናፍቁን ነገሮች አንደኛው ሙዚቃ ስለመሆኑ ክርክር የለም። በጥምቀት ኪነ ጥበብን በጥበብ፤ ጠቢባኑን በትውስታ ዓይነ ሕሊና አሻግረን መመልከታችን አይቀርም። በሙዚቃ ሥራዎቻቸው የልብ ትርታችንን ቀስቅሰው ጥምቀት በደረሰ ቁጥር ትዝ፣ ትውስ የሚሉን በርካታ ድምፃውያንና ሥራዎቻቸው ከፊታችን ድቅን ይላሉ።

**"ሎሚ ብወረውር ፤**
**ደረቱን መታሁት።**
**አወይ ኩላሊቱን**
**ልቡን ባገኘሁት"**

ስትል በቻቺ እስክስታ ድምፃዊቷ የወጉን አድርሳ ነበር። የዘንድሮን ጥምቀት ግን በዚህ ታዘብኩት። በዕለተ ጥምቀቱ ይህን መሳጭ ውብ ባሕል ለመመልከት ላይ ታች ብልም፤ ሎሚው ይሁን ልብ ጠፍቶ ይህን ግን ለማየት ሳልታደል ቀረሁ። አልፎ አልፎ ከአንዳንዶቹ እጅ ላይ የሚታይ ቢሆንም ነገረ ግን፤ 'ሎሚ ለሽታ' እያለ ከአፍንጫው ስር ሽታውን መማግ የመረጠ ይመስላል። ይሁና ... ብለን ወደ ሙዚቃው ስናልፍ፤ በጥምቀት ሰሞን የምንወደውንና ትውስታችን ያረፈበትን ሙዚቃ አለማድመጥ፤ ውስጣዊ ድባባችንን ቀዝቀዝ ከማድረጉም በላይ ቅር ቅር ያሰኘናል። ለአብነትም ይሁኔ በላይ፤

**እዮ ዘገሊሳ ዕለት**
**እቴ ዘገሊሳ ዕለት**
**ነይልኝ በኔ ሞት**
**ለአስተርዮ ማርያም (2 ጊዜ)**
**እመጣለሁ እኔም።**

በጥምቀት የወደዳት ቆንጆ ድንገት ከዓይኑ ሸው ብትል የፍቅሩን ቀጠሮ በአስተርዮ ማርያም ይሁን ይላል። ወትሮም የምናዳምጣቸው ሙዚቃዎች፤ ጥምቀት በመጣና በሄደ ቁጥር የትዝታና ትውስታን ድፍድፍ ጥለውብን፤ ዳግም የማይመለሱ እስኪመስለን ይናፍቁናል። ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) "ጎንደርና ኢትዮጵያ"፤ ሰማኸኝ በለው "ደቦት እንሥራ"፤ አቦነሽ አድነው "ባላገሩ" አዲስ አበባንና የዘንድሮውን ጥምቀት አዋደው፤ እኛንም ለትዝታና ናፍቆት ከዳረጉን ሙዚቃዎች መካከል ነበሩ። ለጥምቀት የሚሆን ግሩም የዜማ ገጸ በረከት ይዞልን የመጣ ድምፃዊም ነበር። ከዚህ ቀደም "ኧረ ጉዴ ኧረ ጉዴ፤ ይህ መወደድ ያኮራል እንዴ" በሚለው ሥራው አድናቆትን ለማትረፍ የቻለው ሚኪያስ ንጉሤ (ሚኪ ላላ) ከሦስት ሳምንታት በፊት ደግሞ 'ኩንስንሷ' እያለ የሚገልጻትን ሸጋ ልጃገረድ "ቆየን ካየን" እያለ በነጠላ ዜማ አድማጩን ከነስሜቱ ቁጭ ብድግ አስደርጎበታል። "እንዲህ አይነት ሙዚቃ ካየን እኛም ቆየን" ያሉ ብዙ ናቸው። እነዚህን ጨምሮ በርካታ ሙዚቃዎች የዘንድሮውን ጥምቀትን ሞቅ ደመቅ አድርገውልናል።

ከፀደይ መልስ ውሃ ጠምቶት ላንቃው በደረቀው በጥር ወር፤ የጥምቀት ሰሞን ላይ፤ ሰማይ ሳይጠቁር ደመናም ሳናይ ቅኔ ይዘንባል። በዚያ ሰሞን ቅኔን ለባለቅኔው የሚተውለት የለም። ገበሬውም በጓሮና በመስኩ ሁሉ ቅኔን ዝረፍ ዝረፍ ያሰኘዋል። ባለውለታውን የሚረሳ አይደለምናም የሕይወቱ መሠረት የሆነውን በሬውንም እንዲህ ሲል በቅኔ ዜማ ያዜምለታል፤

**አለኝ አንድ በሬ እንደኔው የከፋው**
**የሆዴን ብነግረው የጉንጩን ሳር ተፋው!**

...

**በሬ እንደ አንተ የሚሆን የሚሸከረከር፤**
**ጎኔ እንደ አንተ የሚሆን የሚሽከረከር**
**እንዝርትም አይገኝ ከፈታይ መንደር።**

...

**በሬ አንተን የጠላ ጎኔ አንተን የጠላ፤**
**የገና የጥምቀት ይለምናል ጠላ።**

ይሄ ገበሬ "ጎኔ" እያለ የሚጠራው የሚያርስለትን በሬውን ነው። ቃሉን ቅኔ አልብሶ በሬው የእርሱ ማረፊያ ጎኑ ስለመሆኑ ይነግረናል። ለበሬው የሚገባውን ነፍጎ ለጠላውማ በገና በጥምቀቱ ምንም ተስፋ እንደሌለው ጭምር እቅጩን ይነግረዋል። በክረምቱና በዝናቡ ወቅት መሥራት የነበረበትን ለዘነጋ ሰነፍ ዓመቱን ሙሉ በዓል ብሎ ነገር የለውም። የሰው እጅ እንዳየ ጾሙን ውሎ ጾሙን ያድራል። ጥምቀትን ሌላ ምን ያስናፍቃል፤ ስንል የወጣቶቹ ጨዋታ ነው። በየጎዳናውና መንደሩ በሠፈርም ሆነ በአጋጣሚ በአንድ ተሰባስበው በባሕል ጭፈራ፤ እንዲሁም፣ ልዩ ልዩ ጨዋታ ያደምቁታል። በወሎ፣ ላሊበላ፤ በላስታና ሰቆጣ እስክስታ ይንቀጠቀጣል። በዜማ በቅኔው አንዱ ከአንዱ ብሽሽቁ ሁሉ ተናፋቂ ነው። ውስጣዊ ስሜታቸውን ያንጸባርቁበታል። አድናቆትን፣ ፍቅርን፣ ውዳሴን አንዳንዴም ቅኔ አዘል ተረብን የመሰለ ነገር እናስተውልባቸዋለን። እንኳንስ የሀገሩን ሕዝቦች ቀርቶ፤ ከባሕር ማዶ ሳይቀር በአንዲት ጥላ ስር ባሰባሰበው የጥምቀት በዓል፤ በዕለቱ መስቀል አደባባይ የተለየ ነበር። በብሔር ብሔረሰቦች የባህል ጭፈራ ደምቆ፤ ኪነ ጥበብ አንድነት፤ አንድነትም የውበት ጌጣችን መሆኑን ያሳየ ትርዒት ነው። ጃንሜዳም የተዋበውን የሸሮሜዳ ቀሚሷን ለብሳ ነበር። ዘንድሮም ይህን ከመሳሰሉት ትውፊቶቻችን ጋር ከወዲህና ወዲያ `ጢው ጢው` የሚለው የሃርሞኒካ፤ የሙዚቃ መሣሪያ ድምፅ ትዝታ ጣይ ድምቀት ነበር። ምናልባትም ከአዋቂው ይልቅ በሕጻናቱ እጅ ላይ በዛ ብሎ ይታይ ነበር። ከሀርሞኒካው ባሻገር በተወሰኑ ስፍራዎች በየአጥሩ ተከልለው ያሉትን ባሕላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎቻችንን ይዘን ብንወጣ ከምንም በላይ ለሙዚቃችን ዳግም ትንሳኤ ይሆን ነበር።

በጥምቀት ምድር የኢትዮጵያን አፈር ለመርገጥ የሚመኝ ብዙ ነው። ጥቁር ቢሆን ነጭ፤ ከምዕራብ ቢሆን ከሩቅ ምሥራቅ ያየ የሰማው ሁሉ ናፍቆ መምጣቱ የማይቀር ነው። በጥምቀት ሰሞን፤ የጥበብ አብዮት ተቀስቅሶ ጥበባት ለማበባቸው አንድም ከዚሁ ነው። የባሕላዊ ጭፈራ ቤቶች ከአፍ እስከ ገደፍ ሞልተው ይፈሳሉ። የአዝማሪዎች ቅላጼ እየተስረቀረቀ፤ ግጥምና ዜማው ይኸጎደጎዳል። ከወዲህ ጥግ ጭብጨባ፤ ከወዲያ ጥግ ተቀበል ነው። እስክስታው አወራረዱ ፉከራና ሽለላው እንዲሁ በደስታ አስክሮ፤ ሲለዩት በትዝታና ናፍቆት የሚንጥ ስለመሆኑ ይረዱታልና ዓመት ዓመት እየጠበቁ ለዚሁ የሚመጡም ብዙ ናቸው። እነዚህ እንግዶች እንደ ሌላው ዓመት በገፍ ሆነው ባይታዩም ዘንድሮም በሀበሻ ቀሚስና በጃኖ ሱሪ ሲምነሸነሹ ነበሩ። ብዙ ትርዒቶችን ብመለከትም አንዲቷ ግን፤ ግርምትን ጭራብኝ ነበር።

እሁድ ከሰዓት፤ ከደጃች ውቤ መንደር አለፍ ብሎ፤ ከአንደኛው ጎዳና ዳር ካለ መዝናኛ ሥፍራ፤ በርከት ያሉ ወጣቶች ተሰባስበው በጭፈራ አቧራውን ያጨሱታል። ድንገት በዚያ ሲያልፉ የነበሩ አራት ነጮች ይህን ይመለከቱና ቀልባቸውን ቢስበው ጊዜ መጥተው ወጣቶቹን ተቀላቀሉ። ከአራቱ ሁለቱ ወንዶችና አንደኛዋ ሴት በጭፈራው ለመንቀጥቀጥ ሲውተረተሩ፤ አንደኛዋ ሴት ግን በዚያና በዚህ እየተሽከረከረች በያዘችው የቪዲዮ ካሜራ፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በስልኳ እያፈራረቀች ትቀርጽ ጀመር። በጭፈራ ላይ ያሉትን፤ ወጣቶቹ በፍቅር ተቀብለው ከመሐል በማስገባት እስክስታ በየአይነቱ ያስወርዷቸዋል። ድንገት መብራቱ ጠፋና ሲያንባርቅ የነበረው ግዙፍ ቴፕ ጸጥ እረጭ አለ።

መብራቱ ቢሄድ ቅኔውን ማን ዘርፎ፤ ማን ሊቀኘው ነው፤ ያለው ወጣት ወዲያው በድምፁ ማስጨፈሩን ቀጠለ። እዚህ ጋር ነበር ግርምቱ፤ እንግዳ ነው ያሉት ፈረንጅ ከልጁ ድምፅ አስታኮ ድምጹን በማስገባት፤ ቅኔውን ይዘርፍ ጀመረ። ባሕላዊ ሙዚቃዎችን እያቀያየረ ያስጨፍራል። በአንዳንዱ ቃላት ቢሰናከልም ጭፈራና ሙዚቃ አያያዙን ከሰውነት እንቅስቃሴው ጋር ላየውማ፤ አንድ የፒያሳ 'ጨላጣ' ነው የሚመስለው። ነገሩ ሁሉንም ሳያስገርም አልቀረም። ከጎኔ የነበረው ልጅ መወዛወዙን አቁሞ ፈዞ እየተመለከተው "ይሄስ ምኑ ፈረንጅ ነው፤ የጎጃም እረኛ ነው እንጂ" አለ። በመሐል ቀድሞ ሲያስጨፍር የነበረው ወጣት፤ እጁን ወደ ኪሱ ሰዶ ድፍኗን የሁለት መቶ ብር ኖት አውጥቶ እፈረንጁ ግንባር ላይ ለጠፈለት። ሌላ ሁለት ልጆችም ሀምሳና መቶ ደገሙት። ለካስ ኢትዮጵያ ሀገሩ ብቻም ሳትሆን ቤቱም ጭምር የሆነች ቤተኛ ኖሯል። ኋላ ላይ ከድካሙ የተነሳ ትንፋሽ አጥሮት እያለከለከ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለአስር ዓመታት ያህል እንደኖረና ሁሉንም ነገር በደንብ እንደሚያውቅ በመናገር፤ ልጆቹ በሸለሙት ብር ላይ ስድስት ያህል ባለ ሁለት መቶ ኖቶችን ጨምሮ ለወጣቶቹ ሰጠና ሦስቱን እንግዶቹን ይዞ ተሰናብቶ ሄደ።

በጥምቀት ጥበብ ከባሕላዊ ትውፊቶቻችን ጋር ብቻም እንዳልሆነች መቸም እንዳልዘነጋነው ተስፋ አደርጋለሁ። ኪነ ጥበብ በሁሉም ሥፍራ፤ በየትኛውም ጊዜና ቦታ እፁብ የማጣፈጫ ቅመም ነውና። ከጥምቀተ ባሕር እስከ ልዩ ልዩ ጎዳናዎች ድረስ የነበረው መንፈሳዊ የሆነው የክብረ በዓሉ ሥነ ሥርዓት፤ በኪነ ጥበባዊ መዓዛ እንዳወደ ነበር። ወረቡ፣ ሽብሸባው፣ ለነብስ ሲሳይ የሆኑት ዝማሬዎች በበገናና መለከቱ፤ እንዲሁም በመሰንቆና ክራሩ ተዋሕደው ውብ ድባብን ሲያጎናጽፉት ነበር።

**ዕጣን ዕጣን ሸተተኝ መሬቱ፤**
**አባቴ ሚካኤል ያደረበቱ።**

በስተመጨረሻዋ ስንኝ ውስጥ "አባቴ ሚካኤል" የምትለዋን እንደየታቦታቱ ስም በመቀያየር በተመሳሳይ ዜማ ቅኔው ይወርዳል። የከርሞውን እየናፈቅን ለዛሬው የትዝታ ማጎደር የሆነን የዘንድሮውን የጥምቀት በዓላችንን ብናይ፤ ብዙ የትዝታ ስንቅ የሚቋጥርልን ነበር። ግን በአንዴ ከሁሉ ተገኝቶ ሁሉን ለማየት አይቻልምና ያየሁ የተሰማኝን ይቺን ታህሷን ካልኳችሁ፤ ያለውን የሰጠ ንፉግ አይባልምና፤

**ከርሞ እንገናኝ በዓመት፤**
**ከርሞ እንገናኝ በአመት፤**
**አንተም ደህና ብትሆን፤**
**እኛም ባንሞት።**

መባባሉ ወትሮም ልማዳችን ነውና እኔም የወጉን አድርሼ አበቃሁ።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የሥጋ ደዌ በሽታ እንዳይዘነጋ




**እየሩስ ተስፋዬ**

በሀገራችን የሥጋ ደዌ በሽታ ታማሚዎች ከጤና እክል ባሻገር ዘርፈ ብዙ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ችግሮች ከሚገጥሟቸው መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሥጋ ደዌ በእርግማን የሚመጣ እና በዘር የሚተላለፍ በሽታ አይደለም። ይልቁንም ማይኮ ባክትሪየም በሚል በሽታ አምጪ ህዋስ የሚመጣ እንደሆነ የህክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ። ህመሙ እንደማንኛውም በሽታ ታክሞ የሚድን ሲሆን፤ ነርቭን ቆዳን የሚያጠቃ በመሆኑ በወቅቱ ተገቢ ህክምና በአግባቡ ካልተወሰደ የእጅ እና የእግርን ስሜት በማደንዘዝ ለተለያዩ የአካል ጉዳቶች ይዳርጋል።

የኢትዮጵያ ሥጋ ደዌ ተጠቂዎች ብሔራዊ ማህበር ከተመሠረተ 27 ዓመት ሆኖታል። ማህበሩ ‹‹የሥጋ ደዌ ተጠቂዎች እንደ ሌላው ማህበረሰብ እኩል ተጠቃሚ መሆን አለባቸው።›› የሚል ዓላማን አንግቦ ነው የተቋቋመው። በተጨማሪም፣ የግንዛቤ ሥራዎችን መሥራት፣ ታማሚዎቹን እና ቤተሰቦቻቸውን የሙያ ባለቤቶች እንዲሆኑ ማስቻልም ከኃላፊነቶቹ መካከል የሚመደቡ ናቸው።

አቶ ዐቢይ አባተ የብሔራዊ ማህበሩ ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት ስለ ሥጋ ደዌ እና ታማሚዎች በሕብረተሰቡ በኩል ያለው አመለካከት የተሳሳተ እና የተዛባ መሆኑ በስፋት የሚታይ ነው። ችግሩ በመኖሩ ሳቢያ በርካታ ታማሚዎች እና ቤተሰቦቻቸው አድሎ፣ እንዲሁም መገለል ይደርስባቸዋል። በዚህም ምክንያት ለከፋ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነ ልቦናዊ ጫናዎች ይዳረጋሉ።

ብሔራዊ ማህበሩ በእስከ ዛሬ ጉዞው ብዙ ሥራዎችን ሰርቷል። ከዛሬ 20 ዓመታት በፊት አብዛኛው ሕብረተሰብ ስለ ሥጋ ደዌ ግንዛቤው አልነበረውም። ባስ ሲልም ታማሚዎችን የሚያገል እንደነበር የሚያወሱት ሥራ አስኪያጁ፤ ችግሩን ለመቅረፍም የሥጋ ደዌ ቀንን ታሳቢ በማድረግ ስለ በሽታው አመጣጥ እና እንዴት መከላከል እንደሚቻል በተለያዩ አማራጮች የግንዛቤ ሥራ ተሠርቷል። በተለይም በቴሌቪዥን በድራማ መልክ የሚተላለፉ መልዕክቶች ውጤት ማምጣታቸውን ይጠቅሳሉ። ምንም እንኳን መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም በርካታ ሥራዎች የተሠሩ ቢሆንም፣ ዛሬም ድረስ ብዙ ክፍተቶች እንደሚስተዋሉ በመግለፅ፤ መንግሥት ግንዛቤን ከመፍጠር አኳያ የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ይናገራሉ።

ማህበሩ በተለያዩ መድረኮች ችግሩን ለመቅረፍ የግንዛቤ ሥራዎች ይሠራል። የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የሥጋ ደዌ ቀን ምክንያት በማድረግ የችግሩን አሳሳቢት ለማሳየት ይሞከራል። ‹‹የሥጋ ደዌ በሽታን አንዘንጋው›› በሚል መሪ ቃል በሀገራችን ለ25ተኛ ጊዜ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ደግሞ ለ70ኛ ጊዜ ይከበራል። ጥር 18 እና 19 ቀን 2016 ዓ.ም በሀረር ከተማ በተለያዩ ዝግጅቶች የሚከበር ሲሆን፤ ከጤና ሚኒስቴር፣ ከሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የፓናል ውይይት ይደረጋል። በሀገር እና በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለው የህመሙ ይዞታ ምን እንደሚመስል ዝርዝር መረጃዎች ቀርበው ውይይት እንደሚደረግባቸው ሥራ አስኪያጁ ያስረዳሉ።

አቶ ዐቢይ እንደሚገልጹት፤ ቀኑን ማክበር ያስፈለገው ሕብረተሰቡ ሥጋ ደዌ ላይ ያለውን የተሳሳተ እና የተዛባ አመለካከት ለማስተካከል እንደሚያግዝ በማመን ነው። በህመሙ የታያዙ ሰዎችን ‹‹በሽታው የአምላክ ቁጣ ነው። በዘር ይመጣል።›› በሚል የተሳሳተ አመለካከት ከማህበረሰቡ ተገልለው ይገኛሉ። በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎችም ታማሚዎች በአንድ አካባቢ ላይ ብቻ ተወስነው የሚኖሩ ሲሆን፤ ከሕብረተሰቡ ጋር ባለመቀላቀላቸው ምክንያት እነርሱም ሆኑ ሌሎች ስለ ሥጋ ደዌ በቂ ግንዛቤ እንዳያገኙ አድርጓቸዋል ይላሉ።

ሌላው ቀኑን ማክበር ያለው ፋይዳ ችግሩን አስመልክቶ መንግሥት ጋ ያለውን ክፍተት ለማመልከት የሚያግዝ ሲሆን፤ እ.አ.አ "በ2030 በዓለም አቀፍ ደረጃ በሥጋ ደዌ ታማሚዎችን የማግለሉ እና መድሎ የማድረጉን ደረጃ ወደ ዜሮ እናደርሳለን። የሚለውን የዓለም የጤና ድርጅት እቅድ ታሳቢ በማድረግ፤ እቅዱን እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ዓለም ለማሳካት ይረዳ ዘንድ ምክክሮች ለማድረግ ያግዛል። አሁን እየታየ ያለውን ቁጥር ለመቀነስም የመፍትሄ ሃሳቦች እንዲነሱ፣ ብሎም ተግባራዊ እንዲሆኑ ያግዛል ይላሉ።

ከዚህ ጋር በተያያዘ አሁን ላይ በስጋ ደዌ የሚያዙ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ፤ እንዲሁም ቁጥሩን ለመቀነስ ታማሚዎቹ በብዛት የት አካባቢ እንዳሉ ጥናት በማድረግ በሽታውን መቆጣጠር እንደሚገባ የሚገልጹት ሥራ አስኪያጁ፤ አሁን ያለው ቁጥር ለወደ ፊት ያሰጋልና ችግሩ ሳይባባስ በቁጥጥር ሥር መዋል እንዳለበትም ይናገራሉ።

የሥጋ ደዌ ተማሚዎች በሁለት መንገድ ይገለላሉ። አንደኛው ራሳቸውን በራሳቸው ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ማህበረሰቡ ይተላለፍብኛል በሚል ስጋት ያገላቸዋል። ወደ ሕብረተሰቡ ያለምንም ፍራቻ እንዲቀላቀሉ ለማድረግ ብሔራዊ ማህበሩ እየሠራበት ይገኛል። አቅማቸውን ለማብቃት ባሉት 80 ቅርንጫፍ ማህበራት አማካኝነት አቅማቸውን የማጎልበት ሥራም ይሠራል። እንዲሁም ራሳቸውን በኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ በተለያዩ የሀገራችን ክልሎች ወፍጮ በመገንባት ራሳቸውን እንዲችሉ አድርጓል። እንዲሁም በቡና ማሽግ እና መቁላት ሥራ ላይ ተሠማርተው በኢኮኖሚ ራሳቸውን ብሎም ቤተሰቦቻቸውን እንዲደገፉ ለማድረግ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን አቶ ዐቢይ ይናገራሉ።

ብሔራዊ ማህበሩ ከመንግሥት ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር በመረከብ ለስጋ ደዌ ታማሚዎች የሚሆን ማዕከል ገንብቷል። ማዕከሉ ያለ ውጭ ሀገራት እርዳታ ተረጂዎችን ይደግፋል ተብሎ እንደሚጠበቅ የሚናገሩት ሥራ አስኪያጁ፤ የሥጋ ደዌ ታማሚዎችን ተጠቃሚ ለማድረግ አዳዲስ ፕሮጀክቶችን ነድፎ መሥራት እንደሚገባም ያስረዳሉ።

የአካል ጉዳተኞች ጉዳይ የተጎጂዎች ጉዳይ ብቻ አይደለም። የሁለም ጉዳይ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ መንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን በሚገባ መወጣት እንደሚገባቸው አቶ ዐቢይ ይናገራሉ። በቀጣይም የግንዛቤ ሥራዎችን ለመሥራት የታቀደ ሲሆን፤ በተለይም መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም ብዙ ሥራዎችን መሥራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። ሕብረተሰቡም ታማሚዎችን ከማግለል ይልቅ ለተጠቃሚነታቸው እገዛ ማድረግ እንደሚኖርበት አስረድተዋል።

# ዓለም አቀፍ




## የቱርክ ፓርላማ ስዊድን የኔቶ አባል እንድትሆን ድጋፉን ሰጠ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ስዊድን ኔቶን ለመቀላቀል ያቀረበችው ጥያቄ በቱርክ ፓርላማ አባለት ድጋፍ አገኘ። ስዊድን እአአ በ2022 ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረች በኋላ ኔቶን ለመቀላቀል ጥያቄ ማቅረቧ ይታወሳል።

ስዊድን ለኩርድ ተገንጣዮች ድጋፍ ትሰጣለች በሚል ቱርክ ኅብረቱን የመቀላቀል ጥያቄዋን አዘግይታው ቆይታለች። የቱርኩ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ታይፕ ኤርዶሃን በቀናት ውስጥ ውሳኔውን በፊርማቸው ያረጋግጣሉ ተብሎ ይጠበቃል። ከዚህ በኋላ ለስዊድን አባልነት ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡት ብቸኛ የኔቶ አባል ሀገር ሃንጋሪ ትሆናለች።

የስዊድን ጠቅላይ ሚኒስትር ኡልፍ ክሪስተርሰን በማህበራዊ ድረ-ገጽ ላይ "የኔቶ ሙሉ አባል ለመሆን የሚቀረን አንድ ርምጃ ነው" ብለዋል።

የኔቶ ዋና ጸሐፊ የንስ ስቶልተንበርግ የቱርክን ውሳኔ በደስታ ተቀብለው ሃንጋሪ በፍጥነት አዎንታዊ ምላሿን እንድትሰጥ ጠይቀዋል።

ቱርክ ከስዊድን ጋር ባለፈው ሐምሌ ከስምምነት እስከትደርስ ድረስ የስቶክሆልምን ጥያቄ ውድቅ አድርጋ ቆይታለች። ያለፈው ማክሰኞ ዕለት የሀገሪቱ ሕግ አውጪዎች የስዊድን አባልነት 287 ለ 55 በሆነ ድምጽ ደግፈዋል። ፕሬዚዳንት ሬሲፕ ጣይብ ኤርዶሃን ሕጉን ይፈርማሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ስዊድን ለኩርድ ታጣቂዎች ከለላ እየሰጠች ነው ስትል ቱርክ ትከሳለች። በአሸባሪነት የፈረጀችውን እንደ ኩርዲስታን የሠራተኞች ፓርቲ (ፒኬኬ) ያሉ አማፂ ቡድኖችን ለመመከት የበለጠ መሥራት አለባትም ብላለች። የአውሮፓ ህብረትና አሜሪካም ፒኬኬን በአሸባሪነት ፈርጀውታል።

እንደ 31ዱም የኔቶ አባል ሀገር ቱርክ አዳዲስ ሀገራት ወደ ቡድኑ እንዳይቀላቀሉ የማገድ ስልጣን አላት። ስዊድን ያለፈው ሰኔ ወር ጠንከር ያለ የፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ አውጥታለች። አዲሱ ሕግ ለአሸባሪ ቡድኖች የገንዘብ እና የሎጂስቲክስ እርዳታ መስጠትን ህገወጥ አድርጎታል።

ስዊድንና ጎረቤቷ ፊንላንድ በወታደራዊ መስክ ገለልተኛ ሆነው ቆይተዋል። ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረች ከበርካታ ወራት በኋላ ሁለቱም ኔቶን ለመቀላቀል ፍላጎት እንዳላቸው አስታውቀዋል። ፊንላንድ በሚያዝያ ወር ኔቶን በይፋ ተቀላቅላለች። በዚህም ምክንያት ህብረቱ ከሩሲያ ጋር የሚጋራው ድንበር በእጥፍ ጨምሯል።

## የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት በሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ የተጠረጠሩትን አማካሪ አሰናበቱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


ታቢ ሌኦካ

የደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ የዶክትሬት ዲግሪያቸው ሐሰተኛ ነው በሚል የተጠረጠሩትን የምጣኔ ሀብት አማካሪን ከሥራ አሰናበቱ።

ታቢ ሌኦካ በዶክትሬት ዲግሪ ከለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ ተመርቄአለሁ ቢሉም የቢዝነስ ደይሊ እና ደይሊ ማቭሪክ ጋዜጠኞች የፕሬዚዳንቱ አማካሪ ዲግሪን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልቻሉም።

ቢቢሲ በበኩሉ ሌኦካ ከለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ ስለመመረቃቸው ትምህርት ቤቱን ጠይቋል። ትልቅ ስም ያለው ዩኒቨርሲቲም አማካሪዋ ከዩኒቨርሲተው አለመመረቃቸውን አረጋግጧል።

በዚህ ሳምንት መጀመሪያ ላይ ሌኦካ ትልቅ ስም ካላቸው ሁለት ኩባንያዎች የቦርድ አባልነት እራሳቸውን አግልለዋል።

ከኩባንያዎቹ መካከል አንዱ የሆነው አንግሎ አሜሪካን ፕላቲኒየም ሌኦካ በጤና እና የትምህርት ማስረጃቸውን በተመለከተ እየተነሱባቸው ባለው ጥያቄ ከቦርድ አባልነታቸው ተነስተዋል ብሏል።

ሌላኛው የቴሌኮም ኩባንያ ኤምቲኤን ተመሳሳይ ይዘት ያለው መግለጫ አውጥቷል።

የፕሬዚዳንት ራማፎሳ ቃል አቀባይ ቪንሰንት ማግዌኛ ከትምህርት ማስረጃቸው ጋር በተያያዘ በተነሳው ጥያቄ ምክንያት ሌኦካ "ከፕሬዚዳንቱ የምጣኔ ሀብት አማካሪ ምክር ቤት አባልነት በአስቸኳይ እንደተነሱ ተነግሯቸዋል" ሲሉ ለቢቢሲ ገልጸዋል።

የፕሬዚዳንቱ የምጣኔ ሀብት አማካሪ ካውንስል ለደቡብ አፍሪካ ሁለንተናዊ ዕድገት የሚጠቅሙ ፖሊሲዎችን ለማርቀቅ የማማከር ሥራን ይሠራል።

ቀደም ሲል የደቡብ አፍሪካው ዴይሊ ማቭሪክ ሌኦካ የትምህርት ማስረጃቸውን እንዲያቀርቡ ሲጠይቃቸው አማካሪዋ በጤና እና በሥራ ምክንያት የትምህርት ማስረጃቸውን የሚያቀርቡበት ጊዜ እንደሌላቸው መልስ መስጠታቸውን ዘግቦ ነበር።

"አሁን ሀገር ውስጥ አይደለሁም። ግላኮማ ስላለብኝ ማያሚ የዓይን ሆስፒታል ነው የምገኘው፤ አሁን ላይ የቀኝ ዓይኔን ብርሃን አጥቻለሁ" ሲሉ ምላሽ ሰጥተው ነበር።

ሌኦካ የትምህርት ማስረጃ ሐሰተኛ ነው ከተባለ በኋላ የቀረበባቸውን ክስ ለመከላከል አንድ የሬዲዮ ጣቢያ ላይ ቀርበው ነበር።

ሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ስለማቅረባቸው ጥያቄ ሲቀርብላቸው፤ "ይህ እውነት አይደለም" ከማለት ውጪ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ ተስኗቸዋል።

# ስፖርት



# ሀገርን የሚወክሉ አትሌቶችን የሚያፈራው የኢትዮጵያ ቻምፒዮና ከቀናት በኋላ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ



53ኛው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ከቀናት በኋላ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ይካሄዳል። በቻምፒዮናው የተሻለ ብቃት የሚያሳዩ የሩጫ፣ ውርወራ እና ዝላይ አትሌቶችም በአህጉርና ዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ተካፋይ እንደሚሆኑ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል።

በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አዘጋጅነት ከሚካሄዱ ዓመታዊ ውድድሮች መካከል ትልቁ የሆነው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ነው። ከ1963 ዓም የጀመረው አንጋፋው ውድድር ዘንድሮ ለ53ኛ ጊዜ በኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚ ይደረጋል። ከጥር 21 እስከ 26/2016 ዓ.ም በሚዘልቀው ውድድር ላይም 5 ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች፤ እንዲሁም 27 ክለቦች 1ሺህ 102 የሚሆኑ አትሌቶቻቸውን፤ ከአጭር እስከ ረጅም ርቀት የመም ሩጫ፣ የውርወራ እና ዝላይ ስፖርቶች ያፎካክራሉ። በተለያዩ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ የአትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከላት እና አካዳሚ የሚሰለጥኑ ተተኪ አትሌቶችም የውድድር እድል ያገኛሉ። ውድድሩን ለማካሄድም ከ3 ነጥብ 4 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገ ሲሆን፤ 160 በሚሆኑ ባለሙያዎች የሚመራም ነው።

ተተኪና ምርጥ ብቃት ያላቸው አትሌቶች የሚካፈሉበት ይህ ውድድር ሀገርን የሚወክሉ ብርቅዬ አትሌቶች የሚፈሩበት ነው። በዚህ ውድድር ላይም የላቀ ብቃታቸውን የሚያስመሰክሩ አትሌቶች በአህጉር እና ዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ኢትዮጵያን የሚወክሉ ይሆናል። በሚያዚያ ወር ይካሄድ የነበረው ውድድሩ ወደ ጥር እንዲመጣ የተደረገውም ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚካሄዱበትን መርሀ ግብር መሰረት በማድረግ እንደሆነም ነው ፌዴሬሽኑ የጠቆመው። በቀጣዩ ወር በጋና (አክራ) በሚካሄደው 13ኛው የመላ አፍሪካ ጨዋታዎች ላይ ተካፋይ የሚሆኑ አትሌቶች ሚኒማ የሚያሟሉበት ሲሆን፤ ኢትዮጵያዊያን ከአጭር ርቀት እስከ ሜዳ ተግባራት የሚሳተፉበትም ይሆናል። ሌላው ደግሞ ከወራት በኋላ የሚደረጉት 23ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና እና ለፓሪስ 2024 ኦሊምፒኮች ናቸው።

የሁሉም አትሌቶች መዳረሻ የሆነው ኦሊምፒክ ከወራት በኋላ ፓሪስ ላይ የሚካሄድ፤ አትሌቶች ሀገራቸውን ለመወከል የሚያስችላቸውን ዝግጅት የሚያደርጉ እንደመሆኑ እነዚህን መሰል ሀገር አቀፍ ውድድሮች አቋማቸውን ለመለካት፤ እንዲሁም ለምልመላ ምቹ ናቸው። በመሆኑም ከተተኪ አትሌቶች ባሻገር ከተለያዩ ክለቦች የተወጣጡ አትሌቶች የውድድሩ ተሳታፊ መሆናቸው ተረጋግጧል። ለአብነት ያህል በወንዶች የኦሮሚያ ፖሊስ አትሌቲክስ ክለብ አትሌቶቹ ታምራት ቶላ፣ ሲሳይ ለማ፣ ሌሊሳ አራርሳ እና ለሜቻ ግርማ፤ ከፌዴራል ማረሚያ ያሲን ሃጂ፣ አእምሮ ይሌ እና ሀይለማርያም አማረ፤ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ ታደሰ ወርቁን የመሳሰሉ አትሌቶች በሩጫ ይሳተፋሉ። በሴቶችም በተመሳሳይ አሽቴ በከሬ ከኦሮሚያ ፖሊስ፣ ብርቄ ኃየሎም፣ ፎቴን ተስፋይ እና አሪያት ዲቦ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ሃብታም ዓለሙና ሂሩት መሸሻ ከኢትዮ ኤሌክትሪክ፣ አክሱማይት እምባዬ ከፌዴራል ማረሚያ፣ … በውድድሩ ተካፋይ የሚሆኑ ታዋቂና ውጤታማ አትሌቶች ናቸው።

በኢትዮጵያ አስቸጋሪ የሆነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ማነስ በአትሌቲክስ ስፖርትም ከፍተኛ ራስ ምታት በመሆኑ ቻምፒዮናው ከወጣቶች አካዳሚው ባሻገር የውርወራ ስፖርቶች ሱሉልታ በሚገኘው የቀነኒሳ በቀለ የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ እንደሚደረግም ነው ፌዴሬሽኑ ያስታወቀው።

በተያያዘ ዘገባ የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ለ2024ቱ የፓሪስ ኦሊምፒክ ጨዋታዎች ንቅናቄ መድረክ ዛሬ እንደሚጀመር የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ አስታውቋል። የቴክኒክና ሕዝብ ግንኙነት ኮሚቴ ካለፈው ዓመት አንስቶ የተለያዩ እቅዶችን በማዘጋጀት ከሀገር ውጪ በአምስተርዳምና ፓሪስ የሚኖሩ ትውልደ ኢትዮጵያዊያንን ግንዛቤ የማስጨበጥና የንቅናቄ ስራዎችን ያከናወነ መሆኑን አስታውቋል። በሀገር ውስጥ ደግሞ የተለያዩ ቴክኒክ ኮሚቴዎች የተዋቀሩ ሲሆን፤ ዛሬ ሀገር አቀፍ ንቅናቄው ይጀመራል። በዚህም ዛሬ በሚኖረው የንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር ላይም በኦሊምፒኩ ላይ ሀገራቸውን የሚወክሉ አትሌቶች የሚለብሱትን መለያ የሚያስተዋውቅ ይሆናል።

የስፖርቱን ቤተሰብ ጨምሮ የባለድርሻ አካላት በሚካተቱበት በዚህ መድረክም መልእክት ይተላለፋል። ከነገ በስቲያ ጥር 18/2016 ዓ.ም ደግሞ የኦሊምፒክ ችቦ ቅብብል በመቀሌ የሚደረግ ሲሆን፤ ጎን ለጎንም ጉባኤ፣ የብስክሌት እንዲሁም የሩጫና እርምጃ ውድድሮች ይከናወናሉ። በቀጣይ ደግሞ ችቦው ተረኛ ወደ ሆነው ቤኒሻንጉል ክልል፤ ከዚያም ወደ ቀጣዩ ተረኛ ቅብብሎሹ እየተደረገ ሐምሌ 6/2016 ዓ.ም አዲስ አበባ ላይ በማጠናቀቅ የብሄራዊ ቡድኑ ሽኝት የሚደረግ እንደሚሆንም ኮሚቴው በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ አስታውቋል።


## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት በኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ባቲ ከተማ አስተዳደር ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ለባቲ ከተማ ልማት አገልግሎት ጽ/ቤት ለUIIDP በጀት እና ለባቲ ከተማ አስ/ግብርና ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ማለትም
ሎት 1. የጽህፈት መሳሪያ ሎት 2. ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ሎት 3. ቋሚ የቢሮ እቃዎች ሎት 4. የግብርና ዘር ግዥ ሎት 5 የእንስሳት መድሃኒት ግዥ ሎት 6 የግብርና እቃዎች /ፖሊቲን ትዩቦች በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል። ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን

1. በዘመኑ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፣
2. የግብር መለያ ቁጥር ወይም TIN NO ተመዝጋቢ የሆኑ፡
3. ተጫራቾች እሴት ታክስ ቫት ተመዝጋቢ ከሆኑ ቫት ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
4. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ ከተራ ቁ. ከ1-3 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ አድርጎ ማቅረብ የሚችል።
5. የሚገዙ እቃዎችን አይነትና ዝርዝር መግለጫ /ስፔስፊኬሽን/ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ለእያንዳንዱ ሰነድ የማይመለስ 100 ብር በመክፈል ሰነዱን ቢሮ ቁ.6 ከረዳት ገ/ያዥ ላይ መግዛት ይችላሉ። ፖስታውን በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባችሁ።
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለሚወዳደሩት ቁርጥ ዋጋ ሎት1. 5,000 /አምስት ሺ ብር/ ሎት2. 5,000 /አምስት ሺ.ብር/ ሎት3. 5,000 /አምስት ሺ ብር/ ሎት4. 1,000/አንድ ሺ ብር/ ሎት5. 2,000 /ሁለት ሺ ብር/ ሎት 6 2,000/ሁለት ሺ ብር/ ብቻ በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ ወይም CPO ወይም ቢድ ቦንድ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባቲ ከተማ ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት በመሂ1. ገቢ አድጎ ከዋና ጨረታ ሰነድ ጋር ፖስታ ውስጥ አስገብተው ማቅረብ አለባቸው፣ በእጅ cpo ወይም ጥሬ ገንዘብ ይዞ መቅረብ አይቻልም።
7. ይህ ግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ቀን ከ16 /05/2016 እስከ 7 /06/2016 የሚቆይ ሲሆን የጨረታ ሰነድ ዘወትር በስራ ሰዓት ከ2፡30 እስከ 11፡30 ድረስ ከጽ/ቤቱ ረዳት ገ/ያዥ መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።
8. ይህ ግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን በ16ኛው ቀን ላይ በ7/06/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሁሉም ሳጥን ታሽጎ በዚሁ ቀን ሎት 1 እና ሎት 2 ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ሎት 3 እና ሎት 4 5፡30 ሎት 5 እና ሎት 6 8፡30 ሰዓት ላይ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ጨረታው ሲከፈት ሳይገኙ ቢቀሩ ጨረታውን ከመክፈትም ሆነ የጨረታውን ሂደት ለሚወስነው ውሳኔዎች ተገዥ ናቸው።
9. ጨርታውን መ/ቤቱ በሎት ድምር ማወዳደር እንደሚችል ታውቆ በሰነዱ ላይ የተዘረዘሩት እቃዎች ሁሉ ዋጋቸው መሟላት አለባቸው።
10. አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉትን እቃዎች በባቲ ከተማ አስ/ገን/አ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት በራሳቸው ትራንስፖርት ንብረት ክፍል ድረስ ማቅረብ አለባቸው።
11. በባለሙያ መታየት ያለባቸው እቃዎችን ጽ/ቤቱ በሚያቀርበው በባለሙያ አረጋግጠን የምንረከብ መሆኑን ተጫራቾች ማወቅ አለባቸው። ተገጣጣሚ ለሆኑ እቃዎች አሸናፊው ድርጅት ገጣጥሞ ማስረከብ ይኖርበታል።
12. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው ይህ ሲባል ጨረታው በመሰረዙ ተጫራቾች በጨረታው ለማወዳደር እና ላወጡት ወጪ መ/ቤቱ ሃላፊነት የማይወስድ መሆኑን እንገልፃለን።
13. መ/ቤቱ 20% መቀነስ እና መጨመር መብቱ የተጠበቀ ነው።

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 09 13 40 06 23 መደወል ይችላሉ**

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ባቲ ከተማ አስተዳደር ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት**

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ባቲ ከተማ አስተዳደር ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት ለባቲ ከተማ አስተዳደር /ከተ/መሰ/ልማ/ቤ/ኮ/አገ/ጽ/ቤት በ UIIDP በጀት ለሚመራው የተለያዩ ግንባታ ስራዎችን ማለትም፡-
ሳይት 1. 01 ቀበሌ ሰኞ ገበያ ፣02 ቀበሌ ጅዳ ሰፈር መፀዳጃ ቤት ግንባታ፤
ሳይት 2. 03 ቀበሌ ጉልት አካባቢ እና ግሪነሪ አካባቢ፣ 04 ቀበሌ ፋጦ ይማም ወፍጮ ቤት አካባቢ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፤
ሳይት 3. 03 ቀበሌ ቁጥር 2 ት/ቤት፤ Part 2 ቀሪ ግንባታ ፤
ሳይት 4. ባቲ TVET ኮሌጅ ግንባታ፤
ሳይት 5 01 ቀበሌ ሰኞ ገበያ ሼድ ግንባታ፤
ሳይት 6. 03 ቀበሌ ቁጠባ ቤት ግንባታ፤
በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ማሰራት ይፈልጋል። ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ መወዳደር የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን፡-

1. በዘርፉ የታደሰ የንግድ ፍቃድ ያላቸው
2. የግብር መለያ ቁጥር ወይም TIN NO ተመዝጋቢ የሆኑ
3. ተጫራቾች እሴት ታክስ ቫት ተመዝጋቢ ከሆኑ ቫት የተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
4. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ ከተራ ቁ. ከ1-3 የተጠቀሱትን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ አድርጎ ማቅረብ የሚችል።
5. የሚሠሩ የግንባታ ዓይነትና ዝርዝር መግለጫ / ስፔስፊኬሽን/ በጨረታ ሰነዱ ላይ ማግኘት ይችላሉ። ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ለእያንዳንዱ ሰነድ የማይመለሰ 200 /ሁለት መቶ /ብር በመክፈል ሰነዱን ቢሮ ቁ.6 ከዋና ገ/ያዥ ላይ መግዛት ይችላሉ። ፖስታውን በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባችሁ።
6. ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ለሚወዳደሩት ቁርጥ ዋጋ ሳይት1. 20,000/ሃያ ሺ ብር/ ሳይት2. 30,000/ሰላሳ ሺ ብር/ ሳይት3. 45,000/አርባ አምስት ሺ/ ሳይት 4. 35,000/ሰላሳ አምስት ሺ/ሳይት 5. 20,000/ሃያ ሺ/ ሳይት 6. 45,000/አርባ አምስት ሺ/ በባንክ በተረጋገጠ ትዕዛዝ ወይም cpo ወይም ቢድ ቦንድ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባቲ ከተማ ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት በመሂ1. ገቢ አድርጎ ከዋና ጨረታ ሰነድ ጋር ፖስታ ውስጥ አስገብተው ማቅረብ አለባቸው በእጅ cpo ይዞ መቅረብ አይቻልም።
7. ይህ ግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በተከታታይ ቀን ከ16 /05/2016 እስከ 07 /06/2016 የሚቆይ ሲሆን የጨረታ ሰነድ ዘወትር በስራ ሰዓት ከ2፡30 እስከ 11፡ 30 ድረስ ከጽ/ቤቱ ገ/ያዥ መግዛት የምትችሉ መሆኑን እንገልጻለን።
8. ይህ ግልጽ ጨረታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን 22ኛው ቀን ላይ በ7 /06 /2016 በ3፡30 ሁሉም ሳጥን ታሽጎ በዚሁ ቀን ሳይት 1 እና ሳይት 2 ከጠዋቱ 4፡00 ሳይት 3 ሳይት 4 ከጠዋቱ 5፡30 ሳይት 5 እና ሳይት 6 ከቀኑ 8፡30 ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ባቲ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ ይከፈታል። ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ጨረታው ሲከፈት ሳይገኙ ቢቀሩ ጨረታውን ከመክፈትም ሆነ የጨረታውን ሂደት ለሚወስነው ውሳኔዎች ተገዥ ናቸው።
9. ግንባታው በባለሙያ መታየት ስላለበት ጽ/ቤቱ በሚያቀርበው በባለሙያ አረጋግጠን የምንረከብ መሆኑን እና ተጫራቾች የሚሞሉት የጨረታ ሰነድ ላይ ምንም አይነት ስርዝ ድልዝ መኖር የለበትም ።
10. መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው። ይህ ሲባል ጨረታው በመሰረዙ ተጫራቾች በጨረታው ለመወዳደር ላወጡት ወጭ መ/ቤቱ ኃላፊነት የማይወስድ መሆን እንገልጻለን።
11. የጨረታ መክፈቻው የስራ ቀን ካልሆነ ጨረታው ቀጥሎ ባለው የስራ ቀን የሚከፈት መሆኑን መታወቅ አለበት።
12. ጨረታ ላይ ለመሳተፍ ደረጃ 9 እና ከዛ በላይ የሆነ ጠቅላላ ግንባታ ስራ GC ንግድ ፍቃድ ያለው ወይም ያላት እና በዘርፉ የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ ማቅረብ እና መሳተፍ የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን።

**ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር 09 13 40 06 23 መደወል ይችላሉ**

**በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በኦሮሞ ብሄረሰብ ዞን ባቲ ከተማ አስተዳደር ገን/አካ/ኢኮ/ል/ጽ/ቤት**